# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

## የ1996 ዓ.ም.
## የግብርና ናሙና ጥናት
## የመረጃ ሰብሳቢዎች መመሪያ

ሐምሌ 1995
አዲስ አበባ

# ማ ው ጫ


| ተ.ቁ | ር ዕ ስ | ገጽ |
|---|---|---|
| I. | መግቢያ | 1 |
| II. | አጠቃላይ መመሪያ | 2 |
| | 2.1 የመረጃ ሰብሳቢው ተግባርና ሃላፊነት | 2 |
| | 2.2 መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ዘዴዎች | 3 |
| III | የ1996 ዓ.ም. የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት አላማዎች | 5 |
| IV | የ1996 ዓ.ም. የግብርና ናሙና ጥናት አላማዎች | 7 |
| V. | ጽንሰ ሃሳቦችና ፍችዎቻቸው | 8 |
| VI | በጥናቱ የሚሸፈኑ ሰብሎች ዝርዝር | 18 |
| VII | ለሰብል ብልሽት ወይም ምርታማነት መቀነስ ምክንያቶች | 19 |
| VIII | የቅጾች አሞላል መመሪያ | 21 |
| | • የቅጽ ግ.ና.ጥ 96/0 አሞላል መመሪያ | 21 |
| | • የቅጽ ግ.ና.ጥ 96/1 አሞላል መመሪያ | 27 |
| | • የቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሀ አሞላል መመሪያ | 31 |
| | • የቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ለ አሞላል መመሪያ | 41 |
| | • የቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሐ አሞላል መመሪያ | 47 |
| | • የቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3መ አሞላል መመሪያ | 54 |
| | • የቅጽ ግ.ና.ጥ 96/4 አሞላል መመሪያ | 61 |
| | • የቅጽ ግ.ና.ጥ 96/2 አሞላል መመሪያ | 69 |
| | • የቅጽ ግ.ና.ጥ 96/5 አሞላል መመሪያ | 81 |
| | • የቅጽ ግ.ና.ጥ 96/6 አሞላል መመሪያ | 93 |
| | • የቅጽ ግ.ና.ጥ 96/7 አሞላል መመሪያ | 96 |
| | • የቅጽ ግ.ና.ጥ 96/8ሀ አሞላል መመሪያ | 122 |
| | • የቅጽ ግ.ና.ጥ 96/8ለ አሞላል መመሪያ | 131 |
| | • የቆጠራ ቦታ ካርታ አጠቃቀም | 139 |
| | • ዋና ዋና ታሪካዊ ድርጊቶች ዝርዝር | 145 |
| | • መረጃ የሚሞላባቸው ቅጾች መረጃ መሰብሰቢያ እና ወደ ዋናው መስሪያ ቤት መመለሻ ወቅት | 147 |

## የኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ጥናት
## የመረጃ ሰብሳቢዎች መመሪያ

### I. መግቢያ

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መሠረት የሆነው ግብርና በአብዛኛው በግል ባለይዞታ ይካሄዳል። በሀገሪቱ ኤኮኖሚና ማህበራዊ ኑሮ ዕድገትም ከፍተኛውን ድርሻ ያበረክታል።የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ለዚህ ክፍለ ኢኮኖሚ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ገጠሩን ማዕከል ያደረገ የልማት ስትራቴጂ በመንደፍ በአሁኑ ወቅት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ፣ ምርታማነቱ በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኘውን ግብርና ለማሻሻልና የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ከፍ ለማድረግ የተለያዩ ጥናቶችን በማካሄድና ተገቢ እርምጃዎችንም መውሰድ ላይ ይገኛል። ወደፊትም መንግስት ለሀገሪቱ ዕድገት ለሚያወጣቸው ዕቅዶችና ፖሊሲዎች የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚጠቁሙ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ያስፈልጋሉ።

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ለዚሁ ዓላማ የሚሆን መረጃ ለመሰብሰብ በየዓመቱ የግብርና ናሙና ጥናት በናሙና ማካሄዱ የሚታወስ ነው። በዚሁ መሠረት ለ1996 ዓ.ም. የግብርና ናመና ጥናት መረጃዎችን በቀላልና በተሻለ ሁኔታ ለመሰብሰብ ይቻል ዘንድ የመረጃ መሰብሰቢያ ቅጾችንና መመሪያዎችን አዘጋጅቷል። ጥናቱም በገጠር የግል የግብርና ይዞታዎችን ብቻ ይመለከታል።

በዚህ ጥናት የሚሰበሰቡት ዋና ዋና የመረጃ ዓይነቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

1. የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ✓
   - ሀ. የዘር አጠቃቀም በሰብል ዓይነት ✓
   - ለ. የመስኖ አጠቃቀም በሰብል ዓይነት ✓
   - ሐ. የማዳበሪያ አጠቃቀምና መጠን በሰብልና በማዳበሪያ ዓይነት ✓
   - መ. ፀረ-ሰብል ተባይ ፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ሰብል በሽታ መድኃኒት ✓ አጠቃቀም በሰብል ዓይነት።
2. የመሬት አጠቃቀም ✓
   - ሀ. በጊዜያዊ ሰብል የተያዘ የመሬት ስፋት
   - ለ. በቋሚ ሰብል የተያዘ የመሬት ስፋት
   - ሐ. በግጦሽ የተያዘ የመሬት ስፋት
   - መ. በእዳሪ መሬት የተያዘ የመሬት ስፋት
   - ሠ. በደን ... ወዘተ የተያዘ የመሬት ስፋት

3. የተመረተ ምርት መጠን በሰብል ዓይነት

4. የቤት እንስሳት ብዛት (በአገልግሎት ዓይነት፣ በዕድሜና በፆታ)

5. ንብ የያዙ ቀፎዎች ብዛት፣ በዓይነትና የማር ምርት መጠን

በዚህ መሠረት በግብርና ናሙና ጥናት አማካይነት የሚሰበሰቡትን መረጃዎች ደረጃና ጥራት ለመጠበቅና የሚገኙትን ውጤቶች አስተማማኝ ለማድረግ ይቻል ዘንድ በሥራው ላይ ለሚሰማሩ ሠራተኞች አንድ ዓይነት መመሪያ ማዘጋጀት በማስፈለጉ ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል። በመሆኑም በመረጃ አሰባሰቡም ሆነ በቁጥጥሩ ሥራ የሚሰማሩ የመስክ ሠራተኞች በሙሉ በዚህ መመሪያ ውስጥ በዝርዝር የቀረቡትን፣

ሀ/ አጠቃላይ መመሪያ

ለ/ የቅጾች አሞላል መመሪያንና ሌሎች

በሚገባ አስቀድሞ ማንበብና መረዳት ይኖርባቸዋል። በሥልጠናው ወቅት ከውይይት የሚገኙ ጠቃሚ ሃሳቦች ስለሚኖሩ የተገኙትን ሃሳቦች በማስታወሻ መመዝገብ ያስፈልጋል። ከዚህም በተጨማሪ መረጃ በሚሰበሰብበት ጊዜ በመመሪያው ላይ የሰፈሩትን ሃሳቦች በሙሉ ማስታወስ ስለሚያስቸግር መመሪያውን መያዝ ተገቢ ይሆናል።

## II. አጠቃላይ መመሪያ

### 2.1 የመረጃ ሰብሳቢው ተግባርና ኃላፊነት

በግብርና ናሙና ጥናት የተሠማራ መረጃ ሰብሳቢ ለጥናቱ መሳካት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። መረጃ ሰብሳቢው የመረጃ አሰባሰቡን ተግባር በቅንነት፣ በታማኝነትና በታታሪነት ማከናወን ይገባዋል። መረጃ ሰብሳቢው ከተመደበበት ቦታ ነዋሪ ሕዝብ ጋር ተግባብቶ የሕዝቡን ትብብር ለማግኘትና የመረጃ አሰባሰቡን ተግባር ለማከናውን ከማያስፈልጉ ድርጊቶች ሁሉ እንዲርቅ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ማንኛውም መረጃ ሰብሳቢ በሥራው ወቅት ከሥራው ጋር ግንኙነት በሌላቸው ተግባራት /በንግድ፣ በፖለቲካ ወይም በሐይማኖት ቅስቀሳዎች እና በመሳሰሉት /በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ መሰማራት በሥራው ላይ ተፅዕኖ ስለሚኖረው አጥብቆ የተከለከለ መሆኑን ማወቅ ይኖርበታል።

መረጃ ሰብሳቢው ተግባሩን ለማካሄድ በየቤተሰቡ በሚደርስበት ወቅት ሰላምታ በመስጠት እራሱን ማስተዋወቅና ስለመጣበት ዓላማ ገለፃ ማድረግ አለበት፡፡ በጥናቱ የሚጠየቅ ማንኛውም ጥያቄ በመመሪያው መሠረት መሆን እንዳለበት በመገንዘብ ለጥናቱ አግባብ የሌለውን ጥያቄ መጠየቅ አይኖርበትም፡፡ በአጠቃላይ ሥራው ጥንቃቄ የሚጠይቅ ስለሆነ መረጃ ሰብሳቢው ታታሪ፣ ትሁት፣ ቀልጣፋና ተግባቢ መሆን ይኖርበታል፡፡

መረጃ ሰብሳቢው የተለያዩ መጠይቆችንና ቅጾችን በመሙላት መረጃዎችን ሲመዘግብ ጽሑፉ ንፁሕ፣ የሚታይና የሚነበብ መሆን አለበት፡፡ እንደዚሁም መረጃ የተሞላባቸውን ቅጾች ሁሉ በመመርመር አስፈላጊውን ዕርማት ማድረግ ያለበት ከመሆኑም በላይ ካስፈለገ ወደ ቤተሰቡም በመመለስ በስህተት የተመዘገቡ፣ የማይመሳሰሉ፣ እርስ በእርስ የማይጣጣሙ፣ ለማንበብ የሚያስቸግሩ ...ወዘተ መልሶችን ማስተካከል ይገባል፡፡ ለጥናቱ የሚሰጡትን ዶክመንቶችና ሌሎች ዕቃዎች በጥንቃቄ መያዝ አለበት፡፡ በመረጃ አሰባሰቡ ወቅትም የሚሰበሰቡትን መረጃዎች በሚስጥር መጠበቅና ከተቆጣጣሪውና አስተባባሪው በስተቀር ለማንም ግለሰብ ማሳየት አይገባውም፡፡ ከዚህም ሌላ በሥራ ወቅት ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ዶክሜንቶችና ቁሳቁሶች (መጠይቆች፣ መመሪያዎች፣ ኮምፓስ፣ ሚዛን፣ ሜትር፣ እርሳስ፣ መቅረጫ ... ወዘተ) ከመረጃ ሰብሳቢው እጅ ሊለዩ አይገባቸውም፡፡

## 2.2 መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ዘዴዎች

### ሀ. መልስ ሰጪውን ስለመቅረብ

በቅድሚያ መረጃ ሰብሳቢው ለመልስ ሰጪው እንግዳ ስለሆነ ጥሩ የመግባባትና የመተማመን ሁኔታ እንዲፈጠር ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ ሰላምታ ከተለዋወጠና በትህትና ከቀረበ በኋላ ስሙንና የላከውን መሥሪያ ቤት በመንገር መታወቂያውን በማሳየት የመጣበትን ምክንያት ማስረዳት አለበት፡፡ መልስ ሰጪዎች ብዙውን ጊዜ ለምን እነሱ እነደተመረጡ ስለሚጠራጠሩና ስጋት ሊያድርባቸው ስለሚችል የተመረጡት በአጋጣሚ መሆኑንና የተሰበሰበውም መረጃ በሚስጥር እንደሚጠበቅ መግለጽ ያስፈልጋል፡፡

### ለ. በግል ስለማነጋገር

መረጃ ሰብሳቢው ለጥያቄዎች ሁሉ ትክክለኛ መልስ ማግኘት የመጀመሪያ ዓላማው ሲሆን መልስ ሰጪው የሚሰጠው መልስ ለጥናቱ አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ መልስ እንዲሰጥ ማግባባት ያስፈልጋል፡፡ መልስ ሰጪውም ፈቃደኛ ከሆነ በኋላ ቃለ መጠይቁ በግል ሆኖ ሊመለስ በሚችልበት ቦታ መደረግ አለበት፡፡ ምክንያቱም በቃለ መጠይቁ ወቅት የሌሎች ሰዎች መገኘት በመልሶች ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር ስለሚችል ነው፡፡

ሐ. የቃለ መጠይቁን ሁኔታ ስለመቆጣጠር

አንዳንድ ጊዜ መልስ ሰጪው ጥያቄዎችን በቀጥታ መመለስ ሳይችል/ሳይፈልግ ይቀርና ወደ ሌላ አርዕስት በመግባት ለመመለስ ይሞክራል በሌላ በኩል ደግሞ የማይስማማ መልስ ይሰጥ ይሆናል፡፡ በዚህ ጊዜ ወጺያውኑ ማስቆም ወይም ኃይለቃል መናገር አያስፈልግም፣ የሚለውን ማዳመጥና ዘዴ በተሞላበት መንገድ ተገቢውን ጥያቄ በመጠየቅ ትክክለኛውን መልስ እንዲሰጥ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

መ. ጥያቄዎችን ስለመጠየቅ

የጥያቄዎቹን አቀራረብ መለወጥ አሻሚ ትርጉም ሊያስከትል ስለሚችል ጥያቄዎቹ በተሰጠው መመሪያ መሠረት መጠየቅ አለባቸው፡፡ ስለዚህ ጥያቄዎችንም እንደቅደም ተከተላቸው በመጠየቅ መልሶቹ በንፅህናና በጥንቃቄ መሞላት አለባቸው፡፡

ሠ. ጥያቄዎችን ስለመድገም

መልስ ሰጪው፦

1. አላውቅም ቢል፣
2. የማይስማማ መልስ ቢሰጥ፣
3. ጥያቄውን አልመልስም ቢል

መረጃ ሰብሳቢው ጥያቄውን እንዳለ ዝግ ብሎና ጥርት አድርጎ በመድገም መልስ ሰጪው እንዲያስብ ጊዜ መስጠት አለበት፡፡ በተደጋጋሚ ከተጠየቀ በኋላ መልስ ሰጪው ካቃተው ሁኔታው ተመዝግቦ ወደሚቀጥለው ጥያቄ ማለፍ ይገባል፡፡ የተለያዩ ባለይዞታዎች ሲጠየቁ አንድ የተወሰነ ጥያቄ ላይ ተመሳሳይ ችግር ካሳዩ ጥያቄው በትክክል ያልተቀመጠ ሊሆን ስለሚችል ይህ ሁኔታ ለተቆጣጣሪው ወዲያውኑ ሪፖርት መደረግ አለበት፡፡

ረ. የማውጣጣት ጥያቄ ስለማቅረብ

የማውጣጣት ጥያቄ ማለት መልስ ሰጪው ለቀረበለት አጠቃላይ ጥያቄ በሰጠው መልስ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ እንዲሰጥ የሚደረግበት ዘዴ ነው፡፡ መረጃ ሰብሳቢው የማውጣጣት ጥያቄ የሚጠቀመው፣

1. መልስ ሰጪው ከተጠየቀው ጥያቄ ጋር የማይስማማ መልስ ሲሰጥ፣
2. መልሱ ግልጽ ሳይሆን ሲቀር፣
3. መልሱ ያልተሟላ ሲሆን፣
4. መልሱ ትክክል መሆኑ ሲያጠራጥር ነው፡፡

ሆኖም የማውጣጣት ጥያቄዎች መልሶችን መጠቆም የለባቸውም:: ይህንንም ለማስወገድ መልስ ሰጪው በሰጠው መልስ ላይ እንዲመረኮዝ ማድረግ ያስፈልጋል:: የማውጣጣት ጥያቄዎች የሚከተሉትን ይመስላሉ::

1. በተጨማሪ ሊያስረዱኝ ይሞክራሉ?
2. ይቅርታ ስላልሰማሁዎ ሊደግሙልኝ ይችላሉ?
3. በምን ዓይነት መንገድ?
4. ስለማያስቸኩል እስቲ ቀስ ብለው አስበውበት ይንገሩኝ?
5. እስቲ ሌላ ምን እንዳሰቡ ይንገሩን? ...ወዘተ

መጠየቅ የሌለባቸው ጠቋሚ የጥያቄ ዓይነቶች ደግሞ የሚከተሉትን ይመስላሉ::

1. ያለዎት ማሣ ይህ ብቻ ነው አይደል?
2. እዚህ ማሣ ላይ ማዳበሪያ አይጠቀሙም መሰለኝ ይጠቀማሉ?
3. ያሉዎት በጎች እነዚህ ብቻ ናቸው አይደል? ...ወዘተ

ሰ. ቃለ መጠይቁን ስለማጠናቀቅ

ቃለ መጠይቁ ከተፈጸመ በኋላ መልስ ሰጪው ባለበት መረጃ ሰብሳቢው መጠይቁን እንደገና በማየት የተዘለሉ ጥያቄዎች ካሉ ለነሱ መልስ ለማግኘት መሞከር አለበት:: በመጨረሻም መልስ ሰጪው ላደረገው ትብብር በማመስገን ለሌላ ተመሳሳይ መጠይቆች ወይም ተግባሮች ለምሳሌ:- ለማሣ ስፋት ልኬ፣ ለሰብል አጨዳ፣ ለቤት እንስሳት ጥናት ...ወዘተ ሌላ ቀን የሚመለስ መሆኑን ነግሮ መሰናበት ያስፈልጋል::

## III. የ1996 ዓ.ም. የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት አላማዎች

በ1996 ዓ.ም. በመስከረም ወር መጀመሪያ ጀምሮ እስከወሩ መጨረሻ ለአንድ ወር የሀገሪቱን ክልሎች በሙሉ በሚሸፍኑ በናሙና በተመረጠ የቆጠራ ቦታዎች የሚካሄደው የሰብል ትንበያ ጥናት የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል::

1. የዚህ ጥናት መሠረታዊ አላማ በ1996 ዓ.ም. ሊገኝ የሚችለውን ምርት በመገምገም በምርት ዘመኑ ሊመረት የሚችለውን ጠቅላላ ምርት መጠን (Total Production Forecast) ከወዲሁ በመገመትና ወደፊት በሀገሪቱ ሊመረት የሚችለውን የምርት መጠን መተንበይ እንዲሁም፤

2. በ1996 ዓ.ም. ምርት ዘመን ትርፍ ምርት ሊያመርቱ የሚችሉትንና የምርት እጥረት ሊደርስ የሚችልባቸውን ክልሎች መለየት የሚያስችሉ የትንበያ መረጃዎችን ማቅረብ ናቸው።

በሰብል ትንበያ ጥናት የሚገኙ የትንበያ መረጃዎች ከሚሰጡት በዛ ያሉ ጥቅሞች መሃል በተለይ መንግስት ለሚነድፋቸው አዳዲስ ፖሊሲዎችና የረዥምና የአጭር ጊዜ ዕቅዶች ከሚሰጡት ጥቅም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. በሀገር ውስጥ ለምግብ ፍጆታ የሚውል ሰብል በቂ ወይም አነስተኛ መሆኑን በቅድሚያ በመገመት በሰብል ምርት ወደፊት በሃገሪቱ ሊደርስ የሚችለውን ዕጥረት ወይም ትርፍ ለመገምገም ወደ ሃገር ውስጥ ለማስገባትም ሆነ ከሃገር ውስጥ ወደ ውጭ ለመላክ (Import - Export) ወቅታዊ እርምጃዎችን ለመውሰድ መንግስት አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርግ የወደፊቱን በቅድሚያ የማሳወቅ የትንበያ መረጃዎች ትልቁን ሚና ይጫወታል።

ለ. የትንበያ መረጃዎችን በምርት ዘመኑ በሃገሪቱ ትርፍ ምርት ሊያመርቱ የሚችሉ ክልሎችን በመጠቀም በክልሎቹ የሚገኘውን ትርፍ ምርት ምክንያት ሊደርሱ የሚችሉ የተለያዩ ችግሮችን ለምሳሌ የሰብል ማከማቻ ችግር ምክንያት የምርት ብክነት እንዳይኖር ጊዜያዊ ማከማቻዎች ለመስራት እንዲሁም ትርፍ ምርት በመኖሩ ምክንያት ሊደርስ የሚችለውን የሰብል ዋጋ መውደቅ ገበሬው እንዳይጎዳ መንግስት ሊወስድ የሚገባውን እርምጃ በቅድሚያ መንደፍ፤

ሐ. በአንጻሩ የምርት እጥረት ሊደርስባቸው የሚችሉ ክልሎችን በመጠቀም መንግስት በክልሎቹ ሊደርስ የሚችለውን የሰብል ምርት እጥረት ከወዲሁ በመረዳት እጥረቱ ሊወገድ የሚችልበትን መንገድ ለመተለም ቅድመ ሁኔታዎችን እንዲያመቻች በማስጠንቀቅ ሊገጥም የሚችለውን ችግር በማስወገድ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ለመንደፍ ይጠቁማሉ ወዘተ

በመሆኑም ከላይ የተዘረዘሩትን የጥናቱን አላማዎች ለማሟላት የሚከተሉት የመረጃ አይነቶች በተጨባጭ (objective) የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን በመጠቀም ጥናቱ በሚካሄድባቸው ቆጠራ ቦታዎች ይሰባሰባሉ።

ሀ. የታረሰ የመሬት ስፋት በሰብል አይነት

ለ. የሚጠበቀው የምርታማነት ለውጥ ከአለፈው ዓመት ጋር ሲወዳደር በመቶኛ

በዚህም መሠረት ከላይ የተዘረዘሩት መረጃዎች ከመስክ ከተሰበሰቡና ከተቀነባበሩ በኋላ ከዋናው መኸር ወቅት አስቀድሞ በሃገር አቀፍ በክልልና ዞን (National Regional Zonal) ተተንትነው ይዘጋጃሉ::

## IV. የ1996 ዓ.ም. የግብርና ናሙና ጥናት ዓላማዎች

በመላ ሀገሪቱ በናሙና በተመረጡ የቆጠራ ቦታዎች የሚካሄደው የግብርና ጥናት የሚከተሉት ዋና ዋና ዓላማዎች ይኖሩታል::

ሀ. በሀገሪቱ የተመረተውን አጠቃላይ የሰብል ምርት መጠንና በሰብል የተያዘ መሬት ስፋትን ለማወቅና በክልሎችና ዞኖች ደረጃ ያለውን ሁኔታ ለማወዳደር የሚያስችል መረጃ ለማግኘት፣

ለ. አንድ ሄክታር ላይ የሚገኘውን ምርት /Yield/ ምን ያህል እንደሆነና በክልሎችና በዞን ያለውን ልዩነት ለማወዳደር የሚረዳ መረጃ ለማግኘት

ሐ. ከአመት ወደ ዓመት ያለውን የምርት መጠንና የታረሰ መሬት ስፋት ለውጥ ለመገምገም የሚያስችል መረጃ ለማግኘት፣

መ. የተገኘውን የሰብል ምርት ከፍላጎት አንፃር በመገምገም በክልልና በዞኖች ደረጃ ትርፍ አምራች የሆኑና በሰብል ምርት ራሳቸውን ያልቻሉትን አካባቢዎች ለይቶ ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ለማግኘት፣

ሠ. የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታን /ጥቅም ላይ የዋለ የማዳበሪያ ፣ ምርጥ ዘር፣ የአካባቢ ዘር የፀረ ሰብል መድህኒት ፣ ዓይነትና መጠን እንዲሁም የመስኖ አጠቃቀም / ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ለማግኘት ፣

ረ. በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን የመሬት አጠቃቀም ለማወቅ ፣ /በሰብል የተያዘ፣ ዕዳሪ ፣ የግጦሽ መሬትና ሌሎች/

ሰ. በሀገሪቱ ያሉትን የቤት እንስሳትና ዶሮዎች ብዛት በዓይነት ፣ በዕድሜ ፣ ጾታና በአገልግሎት ለማወቅ ፣

ሸ. ንብ የያዙ ቀፎዎች ብዛት በዓይነትና የማር ምርት መጠን መረጃ ለማግኘት ይሆናል፡

በአጠቃላይ የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚያደርገውን አስጸዋጽኦ ለመገምገም ሀገሪቱ ለምታዘጋጀው የአጭርና የረዥም ጊዜ የልማት ዕቅድ የሚረዱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው፡፡

## V. ጽንሰ ሃሳቦችና ፍችዎቻቸው

መረጃዎች ደረጃቸውና ጥራታቸው ተጠብቆ እንዲሰበሰቡ ለማድረግ አንድ ዓይነት ጽንሰ ሐሳብና ፍች መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ በግብርና ናሙና ጥናት የምንጠቀምባቸው ዋና ዋና ጽንሰ ሃሳቦችና ፍችዎቻቸው ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡ መረጃ ሰብሳቢዎችም ሆኑ ሌሎች በጥናቱ የሚሳተፉ ሁሉ መመሪያውን በዝርዝር ማጤንና መረጃዎቹም በመመሪያው መሠረት መሰብሰባቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

### 1. ቤተሰብ

ቤተሰብ ማለት በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች ውስጥ አብረው የሚኖሩትንና ምግባቸውን በአንድ ላይ አብስለው በአንድነት የሚመገቡትን ሰዎች ያጠቃልላል፡፡ የቤተሰብ አባላት በሥጋ ወይም በጋብቻ የሚዛመዱትንና የማይዛመዱትን ሊያጠቃልል ይችላል፡፡ በሥጋ ወይም በጋብቻ የሚዛመዱት ባል፣ ሚስት፣ ልጆች፣ የባል ወይም የሚስት አባት፣ እናት፣ እህት፣ ወንድም፣ ... ወዘተ ናቸው፡፡ በሥጋ ወይም በጋብቻ የማይዛመዱ ሌሎች የቤተሰብ አባላት ለምሳሌ በቤት ሠራተኝነት፣ በዘበኝነት የሚያገለግሉ ግለሰቦች ከቤተሰቡ ጋር አብረው የሚኖሩና የሚመገቡ ከሆነ እንደቤተሰብ አባል ይቆጠራሉ፡፡

የቤተሰብ አባላት ብዛት ሊለያይ ይችላል፡፡ ይኸውም አንድ ሰው ብቻውን እንደ አንድ ቤተሰብ ሊቆጠር ይችላል ወይም ሌሎች ሰዎች እንደዘበኞች፣ ጥገኞች ... ወዘተ ከላይ ከተጠቀሱት ጋር የሚኖሩና በአንድነት የሚመገቡ ከሆነ እንደ አንድ ቤተሰብ ይቆጠራሉ፡፡ ነገር ግን ከጥናቱ በፊት ቤተሰቡን ትቶ በእንግድነት ወደሌላ ቤተሰብ ሄዶ ለስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ ከተቀመጠ አሁን ለሚገኝበት ቤተሰብ እንግዳ መሆኑ ቀርቶ የቤተሰብ አባል ይሆናል ማለት ነው፡፡

ጋብቻው በአንድ ሚስት ብቻ የተመሠረተ ከሆነ ቤተሰብ ባልን፣ ሚስትን፣ ልጆችን፣ የጉዲፈቻ ልጆችን፣ ሌሎች ዘመዶችንና ዘመድ ያልሆኑትን (የቤት ሠራተኞችን... ወዘተ) ሊያጠቃልል ይችላል፡፡ ነገር ግን ጋብቻው ከብዙ ሚስቶች ጋር የተመሠረተ ከሆነ (ከአንድ በላይ ሚስቶች ካሉት) የሰውዬው ሚስቶች

ከነልጆቻቸውና ዘመዶቻቸው... ወዘተ በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች የሚኖሩና ምግባቸውንም በአንድነት አብስለው የሚይበሉ ከሆነ ባልየው አሁን በሕይወት ካሉት ውስጥ በቅድሚያ ካገባት ሚስቱ ጋር እንደ አንድ ቤተሰብ ተቆጥሮ ሌሎች የሰውዬው ሚስቶች የየራሳቸው ቤተስብ እንዳላቸው ሆነው ይወሰዳሉ::

2. <u>መደበኛ የቤተሰብ አባል</u>

አንድ ሰው መደበኛ የቤተሰብ አባል ነው የሚባለው ቢያንስ ስድስት ወር ሙሉ ያለማቋረጥ ከቤተሰቡ ጋር የኖረ እንደሆነ ነው:: ከቤተሰቡ ጋር ለዘለቄታው ለመኖር የመጡ ሁሉ ከቤተሰቡ ጋር መኖር ከጀመሩ ስድስት ወር ባይሞላቸውም እንደቤተሰቡ መደበኛ አባል ይቆጠራሉ:: ከስድስት ወር በታች ከቤተሰቡ ለጊዜው ተለይተው የቆዩ የቤተሰብ አባላት የዚሁ ቤተሰብ አባል ሆነው መቆጠር አለባቸው:: ነገር ግን ከቤተሰቡ ተለይተው ከሄዱ ስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ የሆናቸው ወይም ከስድስት ወር በላይ ለመቆየት አቅደው የሄዱ ከቤተሰቡ ከወጡ ስድስት ወር ባይሞላቸውም እንደቤተሰቡ መደበኛ አባል አይቆጠሩም::

<u>የሚከተሉት የቤተሰብ አባላት እንደመደበኛ የቤተሰብ አባል መቆጠር ይኖርባቸዋል</u>

ሀ. ጥናቱ በሚካሄድበት ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር ቢያንስ ለስድስት ወር የኖሩ ሁሉ፣

ለ. ከቤተሰቡ ጋር መኖር ከጀመሩ ስድስት ወር ባይሞላቸውም ከቤተሰቡ ጋር ለስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ ለመቆየት ዕቅድ ያላቸው ሁሉ ለምሳሌ ባል አግብታ ከወላጆቿ ቤት ወደ ባሏ የሄደች ስድስት ወር ባይሞላትም የባሏ ቤተሰብ መደበኛ አባል ትሆናለች ማለት ነው:: እንዲሁም ሥራ አግኝቶ ለዘለቄታው ለመኖር ወደ ሌላ ቤተሰብ የሄደ ስድስት ወር ባይሞላውም በጥናቱ ጊዜ የተገኘበት ቤተሰብ አባል ይሆናል፣

ሐ. የቤት ሠራተኞች አብዛኛውን ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር የሚያድሩና ሌላ መኖሪያ የሌላቸው ሁሉ፣

መ. ጥናቱ በሚካሄድበት ጊዜ ከስድስት ወር ላነሰ ከቤተሰቡ ለጊዜው የተለዩ ለምሳሌ በዕረፍት ላይ ያሉ፣ ለዓመት በዓል ወደ ሌላ ቦታ የሄዱ፣ ሆስፒታል የገቡ፣ ዘመድ ለመጠየቅና ከሥራቸው ጋር በተያያዘ ጉዳይ ወደ ሌላ ቦታ ለጊዜው የሄዱትን አባላት ሁሉ ያጠቃልላል፣

ሠ. ሌላ መኖሪያ ሥፍራ የሌላቸውና ጥናቱ በሚካሄድበት ወቅት ከቤተሰቡ ጋር የሚኖሩ አባላት ሁሉ ለምሳሌ የተለያዩ ቤቶችን እያቀያየሩ የሚኖሩና መደበኛ መኖሪያ የሌላቸው ግለሰቦች በጥናቱ ወቅት በሚገኙበት ቤተሰብ እንደመደበኛ አባል ተቆጥረው ይመዘገባሉ፡፡

ረ. ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸው፣ ከወላጆቻቸውና ከመደበኛ መኖሪያቸው ተለይተው በመደበኛ ትምህርት ቤቶች፣ በኮሌጆች፣ በዩኒቨርሲቲዎች፣ ... ወዘተ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ በሙሉ ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት አካባቢ (ከተማ) መደበኛ ነዎሪዎች ሆነው መቆጠር አለባቸው:: በአዳሪ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች እንዲሁም ከወላጆቻቸው ተለይተው ቤት ተከራይተው ወይም ከዘመድ ተጠግተው እየኖሩ የሚማሩ ተማሪዎች ምንም እንኳን በየሣምንቱ ወይም በየአሥራ አምስት ቀኑ ስንቅ ለማምጣት ወይም ወላጆቻቸውን ለመጠየቅ ወደ ቤተሰቦቻቸው ቢሄዱም በሚኖሩበት አካባቢ መቆጠር አለባቸው:: ነገር ግን ከመደበኛ መኖሪያቸው በየቀኑ ወደ ትምህርት ቤት እየተመላለሱ የሚማሩ ተማሪዎች ሁሉ የሚኖሩበት ቤተሰብ መደበኛ አባል ሆነው መቆጠር አለባቸው::

3. <u>የቤተሰብ ኃላፊ</u>

የቤተሰብ ኃላፊ ማለት የአንድ ቤተሰብ መደበኛ አባል የሆነ/ች በቤተሰቡ አባላት እንደ ኃላፊ የሚቆጠር/የምትቆጠር ማለት ነው:: ከአንድ በላይ ሚስቶች ያሉት ሰው ሚስቶቹ በተለያየ ቤተሰብ የሚኖሩ ከሆነ እሱ የቤተሰብ ኃላፊ ሆኖ የሚመዘገበው አሁን በሕይወት ካሉት ውስጥ <u>በቅድሚያ ካገባት (አንጋፋ) ሚስቱ</u> ጋር ይሆናል:: ለሌሎቹ ሚስቶች ግን የቤተሰብ ኃላፊ ማን እንደሆነ ተጠይቆ ይመዘገባል::

4. <u>የግብርና ይዞታ</u>

ይዞታ ማለት በግለሰብ ወይም በማሕበር ወይም በድርጅት <u>ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል</u> <u>ለግብርና ምርት ማግኛ የሚውል መሬት፣ የቤት እንስሳት፣ ቀፎ፣ ... ወዘተ</u> ነው:: ይዞታ <u>የሰብል ብቻ</u> ወይም <u>የቤት እንስሳት ብቻ</u> ወይም <u>የሁለቱም በቅንጅት</u> መሆን ይችላል:: <u>በተጨማሪም ይዞታ የመሬት ስፋት ማነስ ወይም መብዛት እንዲሁም የቤት እንስሳት ቁጥር ማነስ ወይም መብዛት አይወስነውም::</u>

የባለይዞታው መሬት ወይም የቤት እንስሳት ወይም ሁለቱም በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ የተለያዩ ቦታዎች ሊኖሩ ይችላሉ:: ሆኖም በተለያየ ቦታ ያለው መሬት በአንድ ባለይዞታ ሥር የሚያደርገው <u>በገንዘብም ሆነ በቴክኒክ በበላይነት የሚቆጣጠረው አንድ አስተዳደር መኖሩ ነው::</u>

አንድ ይዞታ ከአንድ በላይ በሆኑ ባለይዞታዎች ቁጥጥር ሥር ሊሆን ይችላል:: ይህም ማለት አንድ ይዞታ ላይ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ባለይዞታዎች ሊያዙበት ይችላሉ::

5. የግብርና ባለይዞታ

ባለይዞታ ማለት የእርሻ መሬት ወይም የቤት እንስሳት ወይም የሁለቱም ባለቤት የሆነ ወይም በንብረቱ አጠቃቀምና አያያዝ ሙሉ ኃላፊነት ያለው ግለሰብ፣ ማህበር ወይም ድርጅት ነው::

ባለይዞታው በመሬት ላይ የሚዘራውን የሰብል ዓይነት እንዲሁም የሚያረባቸውን የቤት እንስሳት ዓይነት እንደአስፈላጊነቱ በሚያመችና በሚጠቅም መንገድ ለማስተዳደር ሙሉ መብት ሊኖረው የሚችል ነው:: ይህም ማለት ባለይዞታው መቼ የት ምን ዓይነትና እንዴት ሰብል ማምረትና የቤት እንስሳት ማርባት እንዲሁም ውጤቱን እንዴት መጠቀም እንዳለበት የመወሰን መብት ያለው ነው::

ባለይዞታው በይዞታው ላይ በሌሎች ሠራተኞች የሚሠራውን ሥራ በበላይነት ለመቆጣጠርም ሆነ ትዕዛዝ ለመስጠት ይችላል:: በተጨማሪ አንድ ይዞታን በጋራ የሚያስተዳድሩ ከአንድ በላይ ሰዎች ቢኖሩ ይዞታው በአንደኛው ስም ተመዝግቦ በአስተያየት መልክ ይዞታው በጋራ በስንት ባለይዞታዎች ቁጥጥር ሥር መሆኑን መግለጽ አስፈላጊ ነው:: አንድ ባለይዞታ የይዞታው ባለቤት /Owner/ ሊሆን ወይም የይዞታው ባለቤት ላይሆን ይችላል::

6. ፓርስል

ፓርስል ማለት የአንድ ይዞታ አካል ሆኖ ከይዞታው ውጭ በሆኑ እንደ መሬት፣ ውሀ፣ መንገድ፣ ደንና በመሣሰሉት ሙሉ በሙሉ የተከበበ መሬት ነው:: አንድ «ፓርስል» አንድ ማሣ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ማሣዎች /መሬት አጠቃቀም ሊይዝ ይችላል:: በተጨማሪም በአንድ ፓርስል የተለያዩ ሰብሎች ሊዘሩ ይችላሉ:: ለበለጠ ማብራሪያ ገጽ 58 እና 59 ይመልከቱ::

7. ማሣ

ማሣ ማለት በአንድ የሰብል ዓይነት ወይም በድብልቅ ሰብሎች የተያዘ አንድ ሙሉ ፓርስል ወይም የአንድ ፓርስል ክፋይ ወይም አካል ነው:: ለበለጠ ማብራሪያ ገጽ 58 እና 59 ይመልከቱ::

8. ሌላ የመሬት አጠቃቀም
በሰብል ከተያዙ ማሣዎች ውጭ ያሉት የመሬት አጠቃቀሞች (ለምሣሌ፦ እዳሪ፣ በደን፣ በግጦሽ ... ወዘተ የተያዘ) በጥቅል የሚጠሩበት ነው።

9. ሰብል
በዚህ ጥናት ሰብል የምንላቸው ለምግብና መጠጥ የሚሆኑትን፤ ትምባሆን፤ ጥጥና ቅመማ ቅመሞችን ያጠቃልላል።

10. የመኸር ሰብል
ለዚህ ጥናት የመኸር ሰብል ማለት ከመስከረም 1 እስከ የካቲት 30 የሚሰበሰብ ማንኛውም ጊዜያዊ ሰብል ነው። የሰብሉ የዘር ወቅት ግን ከተጠቀሰው ጊዜ ውጭ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል።

11. የበልግ ሰብል
ለዚህ ጥናት የበልግ ሰብል ማለት ከላይ ከተጠቀሰው የመኸር ጊዜ ውጪ የሚሰበሰብ ማንኛውም ጊዜያዊ ሰብል ነው።

*ማስታወሻ፦*

*የመኸርና የበልግ ሰብሎች ከላይ በተጠቀሱት ጊዜያት ውስጥ በዝናብ፣ በውሃ ሽሽ፣ በመስኖ ... ወዘተ የሚመረቱ ሰብሎችን እንደሚያጠቃልሉ መገንዘብ ያስፈልጋል። ይሁንና ቋሚ ሰብሎች የመኸርና በልግ ተብለው እንደማይከፋፈሉ ማስታወስ ይገባል።*

12. ጊዜያዊ ሰብል
ጊዜያዊ ሰብል ማለት ተዘርቶ ወይም ተተክሎ ከአንድ ዓመት ባነሰ ጊዜ ምርቱ የሚሰበሰብና ከተሰበሰበ በኋላም ተክሉ የሚከስም ማንኛውም የሰብል ዓይነት ነው። ለምሣሌ ጤፍ፣ በቆሎ፣ ...ወዘተ ወይም ተተክሎ ከአንድ ዓመት በላይ ቢቆይም ምርቱ ሲሰበሰብ ተክሉ የሚከስም ሰብል ጊዜያዊ ሰብል ይባላል ለምሳሌ ጎመንና ካሳቫ ... ወዘተ

13. ቋሚ ሰብል
ቋሚ ሰብል ማለት የተተከለበትን ወይም የተዘራበትን መሬት ከአንድ ዓመት በላይ የሚይዝና ፍሬው ከተለቀመ በኋላ መዘራት ወይም መተከል ሳያስፈልገው በርከት ላሉ ዓመታት ፍሬ በመስጠት የሚቆይ የሰብል ዓይነት ነው። ለምሣሌ ቡና፣ ብርቱካን፣ ሻይ ...ወዘተ

14. ድብልቅ ሰብል

ድብልቅ ሰብል ማለት በአንድ ማሣ ላይ የሚገኙ የጊዜያዊና የጊዜያዊ ሰብል ወይም የጊዜያዊና የቋሚ ሰብል ወይም የቋሚና ቋሚ ሰብል ድብልቅ ማለት ነው።

15. የዘር ዓይነት

የዘር ዓይነቶች በሁለት ይከፈላሉ። እነርሱም በአካባቢ ከሚመረተው ሰብል ገበሬዎች ለዘር የሚጠቀሙበትና ከፍ ያለ ምርት የሚያስገኝ ጥራት ያለው የተሻሻለ /ምርጥ/ ዘር ናቸው።

በኢትዮጵያ አብዛኛውን ጊዜ የተሻሻለ ወይንም /ምርጥ ዘር/ የሚቀርበው በኢትዮጵያ የግብርና ግብአቶች ባለሥልጣን በኩል ነው። በተጨማሪም መንግሥታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ለምሣሌ ከግብርና ሚኒስቴር፣ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን፣ ከዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ... ወዘተ የሚገኙ ጥሩ ምርት የሚሰጡ እንደምርጥ ዘር ይቆጠራሉ።

ምርጥ ዘር የምንለው ለአንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ ለማዋል በቀጥታ ከላይ ከተጠቀሱት ምንጮች የተገኘውን ብቻ ነው።

16. ፀረ-ተባይ

ፀረ ተባይ ማለት ሰብልን በመብላት ምርት እንዲቀንስ ወይም እንዲጠፋ የሚያደርጉ ተባዮችን ለማጥፋት የሚጠቅም ማንኛውም ዓይነት የኢንዱስትሪ ውጤት የሆነ መድኃኒት ነው። ለምሳሌ ፀረ-ተምች፣ ፀረ-አንበጣ ... ወዘተ።

17. ፀረ-በሽታ

ፀረ-በሽታ ማለት የሰብል ልዩ ልዩ ክፍሎችን /ቅጠል፣ ግንዱን ወይም ሥሩን/በማጥቃት ምርት እንዲቀንስ ወይም እንዲጠፋ የሚያደርግ ማንኛውንም የሰብል በሽታ ሊከላከል የሚችል የኢንዱስትሪ ውጤት የሆነ መድኃኒት ነው።

18. ፀረ-አረም

ፀረ-አረም ማለት ከባለይዞታው ቁጥጥር ውጪ በሰብል በተያዘው ማሣ ውስጥ ሳይፈለግ በመብቀልና ለሰብሉ ምርታማነት አስፈላጊ የሆኑትን ሁሉ በመሻማት ሰብሉ እንዲጠፋ ወይም ምርቱ እንዲቀንስ የሚያደርጉትን ዕጽዋት የሚያጠፋ የኢንዳስትሪ ውጤት የሆነ መድኃኒት ነው።

19. <u>መስኖ</u>

መስኖ ማለት ምርትን ለማምረት ወይም ለመጨመር ሆነ ተብሎ በሰው ሠራሽ ዘዴ ማለትም በቦይ፣ በቦቴ ውኃ በማጋዝ፣ በኩሬና በመሳሰሉት በመጠቀም ማሣው በቂ ውሃ እንዲያገኝ ማድረግ ነው:: ሆኖም በዝናብና በጎርፍ መጥለቅለቅ የሚገኘው ውኃ እንደመስኖ አይቆጠርም::

20. <u>ሰብል ማምረት</u>

በእርሻ ሥራ ተሰማርቶ ቋሚ፣ ጊዜያዊ ወይም ድብልቅ ሰብሎች የማምረት ተግባር ነው::

21. <u>የቤት እንስሳት ማርባት /ከብት ማርባት/</u>

የዳልጋ ከብት፣ የጋማ ከብት፣ በግ፣ ፍየል፣ ዶሮዎችና ንብ በተናጠል ወይም በጣምራ የማርባት ወይም የማደለብ ወይም በፀጉራቸው የመጠቀም ተግባር ነው:: <u>ሆኖም የእርሻ በሬ ወይም ለመጓጓዣ የሚጠቀሙ የቤት እንስሳት ብቻ መኖር</u> የከብት እርባታ ሥራ እንዳለ አያስቆጥርም:: የቤት እንስሳት ቆጠራ በሚደረግበት ጊዜ ግን መረጃ በሚሰበሰብበት ቅጽ ላይ እነዚህ እንስሳት እንደሚመዘገቡ /እንደሚቆጠሩ መገንዘብ ያስፈልጋል::

22. <u>የቤት እንስሳት</u>

በዚህ ጥናት የቤት እንስሳት የዳልጋ ከብቶችን፣ በጎችን፣ ፍየሎችን፣ ፈረሶችን፣ በቅሎዎችን፣ አህዮችን፣ ግመሎችን፣ አሳማዎችን፣ ዶሮዎችንና ንቦችን ያጠቃልላል::

23. <u>ዕድሜ</u>

አንድ ሰው ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ ጥናቱ እስከሚካሄድበት ቀን ድረስ ያለው የዓመት ብዛት ነው:: ዕድሜ የሚመዘገበው በሙሉ ዓመት ሲሆን በሙሉ ዓመት ማለት ከሙሉ ዓመት በተጨማሪ ያሉትን ወሮችና ቀኖች በመተው የሚገኘው ዓመት ነው::

የቤተሰብ አባላትን ዕድሜ በትክክል ለማወቅ የሚያስችሉ ዘዴዎች አንዱ ከቤተሰቡ አባላት መካከል የአንዱን ዕድሜ በትክክል በማወቅ የሌሎችን ዕድሜ ለመገመት ማስቻሉ ነው:: በተለይ የሥጋ ዝምድና ያላቸው አባላት በስንት ዓመት እንደሚበላለጡ ስለሚታወቅ የአንዱን ዕድሜ ማወቅ የሌላውን ዕድሜ ለማስላት ያስችላል:: በተጨማሪም አንዳንድ ሴቶች ዕድሜያቸውን በትክክል ባያውቁም ካገቡ በኋላ ለስንት ዓመት በትዳር ላይ እንደቆዩ ስለሚያውቁ ሲያገቡ የስንት ዓመት ዕድሜ እንደነበራቸው በመጠየቅ አሁን ያላቸውን ዕድሜ ማወቅ ይቻላል:: በትዳር ላይ ስንት ዓመት እንደቆዩ የሚገልጸው መረጃም የልጆቻቸውን ዕድሜ ለማወቅ ያስችላል:: በተጨማሪም አንዳንድ የቤተሰብ አባላት ዕድሜያቸውን

ከአንዳንድ ካለፉና ከሚታወሱ ድርጊቶች ጋር በማነፃጸር መናገር ይችሉ ይሆናል። እነዚህ ድርጊቶች ከተፈጸሙ ስንት ዓመት እንዳለፈ ማወቅ የአባላቱን ዕድሜ ለማወቅ ይረዳል። በዚህ መመሪያ መጨረሻ ዕድሜን በስሌት ለማወቅ እንዲረዳ አንዳንድ ታሪካዊ ድርጊቶች የተፈጸሙበትን ወቅት የሚገልጽ መረጃ ተዘርዝሯል። ብዙ ግለሰቦች ዕድሜያቸውን በዜሮ ወይም በአምስት በሚያልቁ አሀዞች መናገር ስለሚቀላቸው ትክክለኛውን ዕድሜ ለማወቅ ተገቢውን ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል።

24. ኩንታል

ኩንታል ማለት መቶ ኪሎ ግራም የሚመዝን ክብደት ማለት ነው።

25. ሄክታር

ሄክታር ማለት 10,000 (አሥር ሺህ) ሜትር ካሬ ስፋት ያለው መሬት ነው።

26. የወተት ላሞች

የወተት ላሞች በጥናቱ ወቅት ወተት በመስጠት ላይ ያሉትን፣ እርጉዝ የሆኑትን በተጨማሪም ከጥናቱ በፊት ወተት ሲሰጡ የነበሩና ወደፊት ይሰጣሉ ተብለው የሚገመቱትን ያጠቃልላል።

27. የግጦሽ መሬት

የግል ይዞታ አካል ሆኖ ጥናቱ በሚካሄድበት ወቅት ግለሰቡ ለግጦሽ የሚገለገልበት መሬት ማለት ነው።

28. እዳሪ መሬት

እዳሪ መሬት ሰብል ሲመረትበት ቆይቶ መሬትን ለማዳበር ሆን ተብሎ ቢያንስ ለአንድ የሰብል ዘመን ሳይታረስ የሚቆይ መሬት ነው።

29. በኮንትራት ወይም በኪራይ የተያዘ መሬት

የሌላ ሰው የሆነና ባለይዞታው ኪራይ (በገንዘብ ወይም በዓይነት) እየከፈለ የሚጠቀምበት መሬት ማለት ነው።

30. በግል የተያዘ መሬት

ባለይዞታው ለመንግስት ግብር እየከፈለ የግብርና ሥራ የሚያከናውንበት የግሉ (የራሱ) የሆነ መሬት ማለት ነው።

31. ብስባሽ ማዳበሪያ

የተለያዩ ዕፅዋትና፥ ቅጠላ ቅጠሎች ሆን ተብሎ በጉድጓድና በሌሎች ቦታዎች እንዲብላሉ ከተደረገ በኋላ በማዳበሪያነት እንዲውሉ ሲደረግ ነው።

32. <u>ዓምድ</u>
ዓምድ ማለት በቅጹ ወይም በመጠይቁ ለሚሰበሰቡት መረጃዎች አርዕስት የአርዕስቱ ማብራሪያና በአርዕስቱ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልሶች መፃፊያ የተሰጠ ክፍት ቦታ ነው:: በዓምዶቹ መረጃዎች በፊደል ወይም በአኃዝ ብቻ ወይም በሁለቱም እንደአስፈላጊነቱ ሊሰፍሩ ይችላሉ:: በቁጥር የሚገለጹ መረጃዎች በዓምዱ ውስጥ ከቀኝ በመጀመር ወደ ግራ ይሞላሉ:: ይህ አሠራር በሙሉ ቁጥርና በዴሲማል ለሚገለጹ መረጃዎች በሙሉ ያገለግላል:: የሚከተለውን ምሣሌ ይመልከቱ:: 198 ኪሎ ከ760 ግራም 6 ኪሎ ከ75 ግራምና 20 ኪሎ ከ5 ግራም በሚከተለው ሁኔታ በተገለጸው የቁጥሮች አጻጻፍ ይሰፍራሉ::

| ኪ.ግ | ግራም |
|---|---|
| 198 | 760 |
| 6 | 075 |
| 20 | 005 |

33. <u>ቢረንግ</u>
በማግ ልክትሽ ወቅት የሰሚንን አቅጣጫ መነሻ በማድረግ ከአንዱ ማዕዘን ወደ ሌላው ማዕዘን ከምፓስ በማንበብ የሚገኘው ዲግሪ ቢረንግ ይባላል::

34. <u>የማብርና ናሙና ጥናት</u>
ከአጠቃላይ የማብርና ስብስብ /Population or Universe/ ውስጥ የስብስቡን ባህሪዮት ሊይዝና ሊወክል የሚችል በሳይንሳዊ የአመራረጥ ዘዴ የሚመረጥ የስብስቡ አካል ናሙና ሲባል ይህን የአመራረጥ ዘዴ በመጠቀም የሚካሄደው ጥናት ደግሞ የማብርና ናሙና ጥናት ይባላል::

35. <u>የእርሻ ሥራ</u>
የእርሻ ሥራ ማለት ማረስ፣ መጠቅጠቅ፣ ማበራየት፣ ማጨድ ...ወዘተ ማለት ነው:: የቤት እንስሳት የእርሻ ሥራ ሰርተዋል የሚባለው የማረስ ወይም የመጠቅጠቅ ወይም የመውቃትና ሌሎች ለእርሻ አጋዥ የሆኑ ሥራዎችን ለምሣሌ የማጓጓዝ ሥራ የሰሩ እንደሆነ ነው::

36. የተፈጥሮ ማዳበሪያ

ከፍግ፣ ከብስባሽ ወይም ከሌሎች ተፈጥሮ ሰራሽ ነገሮች የሚገኝና የሰብል ምርትን ለማሻሻል የሚረዳ የማዳበሪያ ዓይነት ነው።

37. ኬሚካል ማዳበሪያ /ብስባሽ/

በኢንዱስትሪ ወይም በፋብሪካ የተመረተና የሰብል ምርትን ለማሻሻል የሚረዳ የማዳበሪያ ዓይነት ነው።

38. ኤክስቴንሽን ከምርምር ተቋማት ወይንም ከአካባቢ በቀል ዕውቀትና ልምድ የተገኙትን ጠቃሚ መስለው የሚታዩትን ማናቸውንም ምክር፤ ሃሳብ፤ መረጃ፤ ዕውቀትና የአሠራር ዘዴ በመልዕክት መልክ በማጠናቀርና በማዘጋጀት ገበሬው የማስተላለፍ ተግባርና የማከናወን ሥራ ነው።

በዚህ ጥናት ኤክስቴንሽን መርኻ ግብር የተሳተፉ ገበሬዎች በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት አንዳንድ ገበሬዎች ከኤክስቴሽን ተሳታፊ ገበሬዎች በማየትና በመኮረጅ የኤክስቴሽንን ጠቅላላ መልእክቶች በተዘጋጀው መሠረት ሙሉ በሙሉ ከራሳቸው ፍላጎትና አቅም ጋር በተጣጣመ መልኩ በኤክስቴሽን ውስጥ በተጠቀሱት መልእክቶች መካከል የተወሰኑትን የአሠራር ስልቶች ብቻ ተቀብሎ ሥራ ላይ የሚያውሉ ናቸው።

39. ክትር

አፈር በጎርፍ እንዳይታጠብ ለማድረግ በእርከኖች ዳርና ዳር በድንጋይ ወይም በአፈር የሚሠራ ካብ /ግንብ ነው።

40. አግድመት እርሻ

በተዳፋት መሬት ላይ አፈሩ እንዳይታጠብ ወይም እንዳይሸረሸር ወደ ጎን የሚካሄድ የአስተራረስ ዘዴ ነው።

41. ባህላዊ ቀፎ

ማለት ከተለያዩ ነገሮች /ለምሣሌ፤ ከሸንበቆ፤ ከቀርከሃ፤ እንጨት፤ ከተቦረቦረ ዛፍ፤ ከእንሥራ... ወዘተ/ የተሰራና ማር የሚመረትበት ማለት ነው።

42. መለስተኛ ዘመናዊ /የሽግግር/ ቀፎ

ማለት በግብርና ሚኒስቴር ወይም አግባብ ባላቸው መሥሪያ ቤቶች የሙያ ድጋፍ ተሰርቶ ከባህላዊ ቀፎ የተሻለ ምርት የሚሰጥ ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ

- ገበሬው በቀላሉ ሊሠራው የሚችል
- በሣጥን መልክ የተሰራ አንድ ቀፎ ብቻ የሆነ
- በአንድ ዘንግ ጠርዝ ሰም በማጣበቅ ንቦች እንጀራው ተጋግሮ ለዕንቁላል መጣያና ማር መሥሪያ እንዲገለገሉበት ወደ ቀፎ በመጨመር የሚዘጋጅ የቀፎ ዓይነት ነው፡፡

43. <u>ዘመናዊ ቀፎ</u>

ማለት በግብርና ሚኒስቴር ወይም አግባብ ባላቸው መሥሪያ ቤቶች ባለሙያ ማለት በግብርና ሚኒስቴር ወይም አግባብ ባላቸው መሥሪያ ቤቶች ባለሙያ

ማለት በግብርና ሚኒስቴር ወይም አግባብ ባላቸው መሥሪያ ቤቶች ባለሙያ ተሰርቶ ከፍ ያለ ምርት የሚሰጥ ማለት ሲሆን በሳጥን መልክ የተሰራና ከ3 5 ቀፎዎች አደራርቦ ማስቀመጥ የሚቻልበት ነው፡፡ በተጨማሪም የራሱ የሆነ በሽቦ የተሰራ የእንጀራ መጋገሪያ ፍሬም ያለውና እንጀራው በባለሙያ ከተሰራ በኋላ ወደ ቀፎው በመጨመር በቀጥታ ንቦች ዕንቁላልና ማር እንዲሰሩበት ተደርጎ የተዘጋጀ የንብ ቀፎ ነው፡፡

## VI. <u>በጥናቱ የሚሸፈኑ ሰብሎች ዝርዝር</u>

<u>ጊዜያዊ ሰብሎች</u>

ሀ. <u>የብርዕና አገዳ ሰብሎች</u>
1. ጤፍ
2. ገብስ
3. ስንዴ
4. በቆሎ
5. ማሽላ/ዘንጋዳ/
6. ዳጉሣ
7. አጃ
8. ሩዝ
9. ሌሎች…ይገለጽ*

ለ. <u>ጥራጥሬ</u>
1. ባቄላ
2. አተር/አኩሪ አተር/
3. ሽንብራ
4. ምስር
5. ጓያ
6. ቦሎቄ
7. ግብጦ
8. አብሽ
9. ሌሎች…ይገለጽ*

ሐ. <u>የቅባት እህሎች</u>
1. ኑግ
2. ሠሊጥ
3. ሱፍ
4. ተልባ

መ. <u>ቅመማ ቅመም</u>
1. ጥቁር አዝሙድ*
2. ነጭ አዝሙድ*
3. ዝንጅብል*
4. ዕርድ*
5. ኮረሪማ*
6. ድንብላል*
7. ሌሎች…ይገለጽ*

ሠ. <u>አትክልት</u>
1. የአበሻ ጎመን
2. ጥቅል ጎመን
3. ሠላጣ
4. ቆስጣ
5. በርበሬ
6. ቃሪያ
7. ቲማቲም
8. አበባ ጎመን*
9. ፎሶሊያ/ፋጆሊ*
10. ዱባ*
11. ሌሎች…ይገለጽ*

ረ. <u>ሥራሥር</u>
1. ቀይ ሽንኩርት
2. ነጭ ሽንኩርት
3. ካሮት
4. ቀይ ሥር

5. ጎመን ዘር
6. ለውዝ
7. ሌሎች...ይገለጽ*

5. ድንች
6. ስኳር ድንች
7. ጎደሬ
8. ሌሎች...ይገለጽ*

ሰ. <u>ካሽ ክሮፕ</u>
1. ጥጥ*
2. ትምባሆ*
3. ሌሎች ይገለጽ*

<u>ቋሚ ሰብሎች</u>

ሀ. <u>ፍራፍሬ እና ካሽ ክሮፕ</u>
1. ቡና
2. ጫት
3. ጌሾ
4. ሸንኮራአገዳ
5. ብርቱካን
6. ሙዝ
7. ሎሚ
8. ፓፓያ
9. ማንጎ
10. ዘይቱን
11. አቮካዶ
12. አናናስ
13. ኮክ*
14. እንሰት*
15. መንደሪን*
16. ትርንጎ*
17. ወይን*
18. ከርቡሽ/ሀብሀብ*
19. እንጆሪ*
20. ሌሎች*

ለ. <u>ቅመማ ቅመም</u>
1. ቁንዶ በርበሬ*
2. ቀረፋ*
3. ቅርንፉድ*
4. ጥምዝ ቅመም*
5. ጤናዳም*
6. ሄል*
7. እንስላል*
8. ሌሎች...ይገለጽ*

*<u>ማስታወሻ:-</u>*
*ከላይ በተዘረዘሩት ሰብሎች የተያዙ ማሳዎች በሙሉና ሌሎች የመሬት አጠቃቀም የማሣ ልኪ ሲደረግላቸው የሰብል አጨዳ የሚካሄደው ግን በጊዜያዊ ሰብሉች ለተመደቡትና በገጽ 19 ሀ, ለ, ሐ ተብለው ለተዘረዘሩት ብቻ ነው:: ለቋሚ ሰብሎች አትክልት ሥራሥርና ቅመማ ቅመሞች የሰብል አጨዳ አይደረግላቸውም::*

## VII. <u>ለሰብል ብልሽት ወይም ምርታማነት መቀነስ ምክንያቶች</u>

የሰብል ብልሽት ምክንያቶች

1. የዝናብ ብዛት
2. የዝናብ እጥረት

11. ወፍ
12. ሌሎች*

3. ፀረ አዝርዕት ተባዮች

4. ፀረ አዝርዕት በሽታዎች

5. አረም

6. በረዶ

7. ውርጭ

8. ጎርፍ

9. የዱር አራዊት

10. አንበጣ

ለምርታማነት መቀነስ ምክንያቶች

1. የዘር ዕጥረት
2. የእርሻ መሬት ለምነት መቀነስ
3. በአካባቢው የፀጥታ ሁኔታ አለመረጋጋት
4. ሌሎች ምክንያቶች ናቸው።

[1]*የቅጾች አሞላል መመሪያ*

## የቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/0 የቤተሰቦች መመዝገቢያ ቅጽ አሞላል

ይህ ቅጽ በተመረጠው የቆጠራ ቦታ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦችና የግል ባለይዞታዎች በሙሉ ለመመዝገብ ያገለግላል:: ምዝገባው የሚካሄደው በቆጠራ ቦታው ክልል ውስጥ ከቤት ወደ ቤት በመሄድ ስለሆነ በምዝገባው ጊዜ ቤቶች እንዳይረሱና ወይም በድጋሚ እንዳይመዘገቡ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል:: በተመሳሳይ ሁኔታ ቤተሰቦችና የግል ባለይዞታዎች በተሟላ አኳኋን መመዝገብ ይኖርባቸዋል:: የአመዘጋገቡ ተግባር እንደ ቤቶቹ አቀማመጥ ሳይዘበራረቅ መሆን አለበት::

## የቤተሰቦች አመዘጋገብ ሁኔታ

በተመረጠው ቆጠራ ቦታ ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦችና ባለይዞታዎች በሚከተለው ሁኔታ መመዝገብ አለባቸው::

ሀ. በመጀመሪያ ለጥናቱ የተመረጠውን ቆጠራ ቦታ ክልል ከሚያውቅ ሰው ጋር በመሆን ድንበሩን/ክልሉን ዞሮ ማየትና ማጥናት፣

ለ. የቤቶቹን፣ የመንገዶችንና የመንደሮችን አቀማመጥ ማየት፣

ሐ. ምዝገባውን ከቆጠራ ቦታው ሰሜን ምዕራብ ከሚገኘው መንደር/አካባቢ/ በመነሳት ወደ ምሥራቅ ከዚያ ወደ ምዕራብ/ጥምዝምዞሽ/ ሥርዓት ባለው መንገድ በመጓዝ እያንዳንዱን ቤተሰብና በስራቸው የሚገኙትን ባለይዞታዎች በቅደም ተከተል መመዝገብና በቤቱ በር ወይም ሊጠፋ ከማይችል ቦታ ላይ በቾክ/ጠመኔ/ ምልክት ማድረግ ያስፈልጋል:: ስለሆነም በተመዘገበው ቤተሰብ ቤት በር ላይ «AG 96/001, AG 96/002 ... ወዘተ» እየተባለ ምልክት መፃፍ ይኖርበታል:: በተጨማሪም ከተመረጠው ቆጠራ ቦታ በመውጣት ምዝገባ እንዳይካሄድ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል::

<u>ክፍል 1</u> <u>የአካባቢ መለያ</u>

<u>ዓምድ 1</u> <u>ክልል</u>

ጥናቱ የሚካሄድበት የቆጠራ ቦታ የሚገኝበት ክልል ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል::

<u>ዓምድ 2</u> <u>ዞን</u>

ጥናቱ የሚካሄድበት የቆጠራ ቦታ የሚገኝበት ዞን ስም/ቁጥር/ በዚህ ዓምድ ይሞላል::

[1] c:\ease94>96gn.doc

ዓምድ 3 ወረዳ

ጥናቱ የሚካሄድበት የቆጠራ ቦታ የሚገኝበት ወረዳ ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 4 ገበሬ ማኀበር

ጥናቱ የሚካሄድበት የቆጠራ ቦታ የሚገኝበት ገበሬ ማኀበር ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 5 የቆጠራ ቦታ ኮድ

ጥናቱ የሚካሄድበት የቆጠራ ቦታ መለያ ቁጥር ከቆጠራ ቦታው ካርታ ላይ በመውሰድ በዚህ ዓምድ ይሞላል::

## ክፍል 2 የቤተሰቦችና የግብርና የግል ባለይዞታዎች ዝርዝርና የምርጫ ቅደም ተከተል

ዓምድ 1 የቤተሰብ መለያ ቁጥር

በተመረጠው የቆጠራ ቦታ ለሚገኙ ቤተሰቦች በዚህ ዓምድ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ ከ001 በመጀመር 002፣ 003፣ ...ወዘተ በማለት የቤተሰብ መለያ ቁጥር በመስጠት ይሞላል::

ዓምድ 2 የቤተሰብ ኃላፊ ስም ከነአያት

በዓምድ 1 በተሰጠው ተራ ቁጥር አንፃር ለእያንዳንዱ ቤተሰብ የቤተሰቡ ኃላፊ ስም ከነአያት በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 3 በቤተሰቡ ውስጥ የግብርና የግል ባለይዞታ /አለ = 1፣ የለም = 2

በዓምድ 2 በተመዘገቡ ቤተሰቦች ውስጥ የግብርና የግል ባለይዞታ መኖር አለመኖሩ ተጠይቆ ካለ «አለ» ተብሎ ኮድ «1» ከሌለ ደግሞ «የለም» ተብሎ ኮድ «2» በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 4 በቤተሰቡ ውስጥ የግብርና የግል ባለይዞታዎች ተራ ቁጥር

በዓምድ 3 ኮድ «1» ከተሞላ በቤተሰቡ ውስጥ የግል ይዞታ ያላቸው ባለይዞታዎች ተከታታይ ቁጥር ከአንድ በመጀመር በዚህ ዓምድ የሚሰጥ ሲሆን በሚቀጥለው ቤተሰብ ውስጥ ላሉት ባለይዞታዎች ደግሞ እንደገና ከአንድ በመጀመር የባለይዞታ ተራ ቁጥር ይሰጣል::

ዓምድ 5 የባለይዞታው ሙሉ ስም

በዚህ ዓምድ በዓምድ 4 በተሰጡት ተራ ቁጥሮች አንፃር የባለይዞታው ስም ይሞላል::

ዓምድ 6 በቤተሰቡ ውስጥ የግል ባለይዞታ ያላቸው ቤተሰቦች ተከታታይ ቁጥር

በዚህ ዓምድ በዓምድ 3 ኮድ «1» የተሞላላቸውን ቤተሰቦች በመለየት/በመምረጥ እንደቅደም ተከተላቸው ከ001 በመጀመር 002፣ 003 ... ወዘተ የቤተሰብ ተከታታይ ቁጥር በመስጠት ይሞላል።

ዓምድ 7 የአመራረጥ ቅደም ተከተል

በዓምድ 6 የቤተሰብ ተከታታይ ቁጥር ከተሰጣቸው ቤተሰቦች ውስጥ ለጥናቱ ለተመረጡት ቤተሰቦች በአመራረጥ ቅደም ተከተላቸው መሠረት ከ01 በመጀመር እስከ 25 ቁጥር ይሰጣቸዋል።

ማስታወሻ፡- በቆጠራ ቦታው ውስጥ የግል ባለይዞታ ያላቸው ቤተሰቦች ጠቅላላ ብዛት ከዓምድ 6 የመጨረሻውን ቁጥር በመውሰድ በተሰጠው ቦታ ይመዘገባል።

## የግብርና ባለይዞታ የቤተሰብ አባል ያላቸው ቤተሰቦች አመራረጥ ዘዴ

በቅጽ ግ.ና.ፕ. 96/0 የሚመዘገቡት ቤተሰቦች ምዝገባ በተሟላ ሁኔታ መጠናቀቁን ቤተሰቦች ሳይዘለሉ ወይም ሳይረሱና የግብርና ባለይዞታ ያላቸው ቤተሰቦች ምዝገባ ሳይምታታና በትክክል መከናወኑን ደጋግሞ በማረጋገጥ የግብርና ባለይዞታ የቤተሰብ አባል ያላቸው 25 ቤተሰቦች የሚከተለውን የአመራረጥ ዘዴ በመከተል ይመረጣሉ።

በቅጽ ግ.ና.ፕ. 96/0 ክፍል 2 ዓምድ 6 የግል ባለይዞታ የቤተሰብ አባል ላላቸው ቤተሰቦች የተሰጠውን የመጨረሻ ተራ ቁጥር በመውሰድ ለሚመረጡት ቤተሰቦች ብዛት ይካፈላል። በዚህ ስሌት የተገኘው ቁጥር/አንቲጀር/ ካልሆነ ክፍልፋዩን ትቶ ሙሉው ቁጥር ይወሰዳል። ይህ ቁጥር «መ» ነው እንበል። ከዚህ በኋላ «መ»ን በመያዝ የራንደም ሠንጠረዥ በመጠቀም ከ1-መ ካሉት ቁጥሮች መካከል በመጀመሪያ የተገኘው ቁጥር /«1» እና «መ»ን ጨምሮ/ይመረጣል። ይህም የተመረጠው ቁጥር በመጀመሪያ የተመረጠውን ባለይዞታ የቤተሰብ አባል ያለውን ቤተሰብ ያመለክታል። በዚህም መሠረት ቤተሰቡ መጀመሪያ መመረጡን ለማመልከት በቅጽ ግ.ና.ፕ. 96/0 ክፍል 2 ዓምድ 6 ላይ የቤተሰቡ ተከታታይ ተራ ቁጥር ይከበብና በዚሁ ቅጽ ክፍል 2 ዓምድ 7 በተመረጠው ቤተሰብ አንጻር «01» ተብሎ ይጻፋል።

በሁለተኛ ደረጃ የሚመረጠውን የግብርና ባለይዞታ የቤተሰብ አባል ያለውን ቤተሰብ ለማግኘት በመጀመሪያ ለተመረጠው ቤተሰብ በዓምድ 6 የተከበበው ተራ ቁጥር ላይ «መ» ይደመርና የሚገኘውን ቁጥር በዓምድ 6 ከተዘረዘሩት ተራ ቁጥሮች የያዘው ቤተሰብ ተራ ቁጥር ይከበብና በዓምድ 7 «02» ይጻፋል። ይህ አሰራር በቆጠራው የሚሸፈኑ 25 የግብርና ባለይዞታ የቤተሰብ አባል ያላቸው ቤተሰቦች እስኪመረጡ ድረስ ይቀጥላል።

ምሣሌ

በአንድ ለዚህ ግ.ና.ፐ. በተመረጠ የቆጠራ ቦታ የተመዘገቡና በቤተሰባቸው ውስጥ የግብርና ባለይዞታ የቤተሰብ አባል ያላቸው ቤተሰቦች ጠቅላላ ብዛት (በዓምድ 6 ተከታታይ ተራ ቁጥር የተሰጣቸው) 191 ቢሆኑ፣ ለጥናቱ የሚመረጡት ቤተሰቦች ብዛት ደግሞ 25 ስለሆነ፡-

$$መ = 191/25 = 7.64$$

ከነጥብ በኋላ ያለው ቁጥር ይተውና መ ተብሎ ይወሰዳል:: የራንደም ቁጥር ሠንጠረዥ በመጠቀም ከ1-7 ካሉት ቁጥሮች ውስጥ በቅድሚያ የተገኘው ቁጥር ይመረጣል:: ይህን በማድረግ የተገኘው ቁጥር 2 ቢሆን በመጀመሪያ የተመረጠው ይህን ቁጥር የያዘው በዓምድ 6 ላይ 002 የቤተሰብ ተራ ቁጥር የተሰጠው የግብርና ቤተሰብ ይሆናል ማለት ነው:: 002 የቤተሰብ ተራ ቁጥር በዓምድ 6 ይከበብና በአንጻሩ በዓምድ 7 «01» ይጻፋል::

በሁለተኛ ደረጃ የሚመረጠው ባለይዞታ የቤተሰብ አባል ያለው ቤተሰብ ደግሞ 2+7=9 በስሌቱ መሠረት በዓምድ 6 ላይ 009 ተከታታይ ተራ ቁጥር የያዘው (አቶ ታደስ ደስታ) የግብርና ቤተሰብ ይሆናል ማለት ነው:: ይህ ቁጥር በዓምድ 6 ይከበብና በአንጻሩ በዓምድ 7 «02» ይጻፋል:: ይህ አሠራር 25 የግብርና ባለይዞታ ያላቸው ቤተሰቦች እስኪመረጡ ድረስ ይቀጥላል:: ከዚህ ቀጥሎ የተሰጠውንም የቅጽ ግ.ና.ፐ. 96/0 አሠራር ምሣሌ በመመልከት ስለአሠራሩ የበለጠ ግንዛቤ ማግኘት ይቻላል::

ምርጫው እንደተጠናቀቀ ምዝገባውን ያካሄደው መረጃ ሰብሳቢ የመስክ ሥራ ተቆጣጣሪና የዞን አስተባባሪ ስለ ስራው ትክክለኛነት ስማቸውን ፊርማቸውንና ሥራው የተጠናቀቀበት ቀን በተሰጠው ቦታ ማስፈር አለባቸው::

ማሳሰቢያ፡- ለሰብል ትንበያ ጥናት የሚፈለጉት ቤተሰቦች ብዛት 10 ሲሆኑ የሚመረጡትም ከላይ በተገለፀው መንገድ ከተመረጡት 25 የግብርና የግል ባለይዞታ ካላቸው ቤተሰቦች መካከል ነው:: ይሁንና የእነኚህ 10 ቤተሰቦች ምርጫ በዋናው መሥሪያ ቤት የተከናወነ ሲሆን እነሱም በእያንዳንዱ የቆጠራ ቦታ ከተመረጡት 25ቱ ቤተሰቦች መካከል በአመራረጥ ቅደም ተከተላቸው በ02፣ 04፣ 07፣ 09፣ 12፣ 14፣ 17፣ 19፣ 22 እና 24ኛ ደረጃ የተመረጡት ቤተሰቦች መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል:: ከላይ በተገለፀው ምሣሌ መሠረት የአቶ ታደሰ ደስታ ወዳጆ፣ የአቶ ብርሀኑ ዘሩ በላይ እና የአቶ ደጉ በላይ ዘሩ ቤተሰብ በሰብል ትንበያ የሚካተቱ ሲሆኑ ሌሎቹም በተመሳሳይ መልኩ እንደሚመረጡ ማስታወስ ተገቢ ነው::

ቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/0

# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን
## በብሔራዊ የተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም
## የግብርና ናሙና ጥናት 1996 ዓ.ም.

ክፍል 1 - የአካባቢ መለያ

| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|
| ክልል | ዞን | ወረዳ | ገበሬ ማኅበር | ቆጠራ ቦታ |
| አማራ | ሰሜን ሸዋ | አሣግርት | ቀዩ አፈር | 01 |

ክፍል 2 - የቤተሰቦችና የግብርና የግል ባለይዞታዎች ዝርዝርና የምርጫ ቅደም ተከተል

| 1<br>የቤተሰብ መለያ ቁጥር | 2<br>የቤተሰብ ኃላፊ ስም ከነአያት | 3<br>በቤተሰቡ ውስጥ የግብርና የግል ባለይዞታ አለ 1 የለም → 2 | ኮድ | 4<br>በቤተሰቡ ውስጥ የግብርና የግል ይዞታ ያላቸው ባለይዞታዎች ተከታታይ ተራ ቁጥር | 5<br>የባለይዞታው ሙሉ ስም | 6<br>የግብርና የግል ባለይዞታ ያላቸው ቤተሰቦች ተከታታይ ቁጥር | 7<br>የአመራረጥ ቅደም ተከተል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 001 | አቶ ከበደ ታዬ ጉዬ | አለ | 1 | 1 | አቶ ከበደ ታዬ | 001 | |
| 002 | አቶ ዳምጠው ገብሬ ታፈ | አለ | 1 | 1 | አቶ ዳምጠው ገብሬ | (002) | 01 |
| 003 | ወ/ሮ አበባ ዛፋ በላይ | የለም | 2 | — | — | — | |
| 004 | አቶ ጋሻው ከበደ አበበ | አለ | 1 | 1 | አቶ ጋሻው ከበደ | 003 | |
| | | | | 2 | ታደሰ ጋሻው | | |
| 005 | አቶ ተሰማ ገቶ ወዳጄ | አለ | 1 | 1 | አቶ ተሰማ ገቶ | 004 | |
| 006 | አቶ አየለ ተፈራ ቻሌ | አለ | 1 | 1 | አቶ አየለ ተፈራ | 005 | |
| 007 | አቶ አንዳርጌ ብዙነህ ካሣ | አለ | 1 | 1 | አቶ አንዳርጌ ብዙነህ | 006 | |
| | | | | 2 | አቶ ካሳው ታዬ | | |
| 008 | ወ/ሮ አታለም አበበ ቀሬ | የለም | 2 | — | — | — | |
| 009 | አቶ ንጉሴ መርሻ ዘነበ | አለ | 1 | 1 | አቶ ንጉሴ መርሻ | 007 | |
| 010 | አቶ አዳም ከፋር ወልዴ | አለ | 1 | 1 | አቶ አዳም ከፋር | 008 | |
| | | | | 2 | አቶ ከመሌስ ደነቀ | | |
| | | | | 3 | ወ/ሮ ሳሙኤ አዳም | | |
| 011 | አቶ ታደሰ ደስታ ወደጆ | አለ | 1 | 1 | አቶ ታደሰ ደስታ | (009) | 02 |
| | ' | | | | ' | | |
| | " | | | | ' | | |
| | ' | | | | ' | | |
| | ' | | | | ' | | |
| | ' | | | | ' | | |
| 014 | ወ/ሮ ወርቅነሽ አበበ ለምለም | አለ | 1 | 1 | ወ/ሮ ወርቅነሽ አበበ | 012 | |
| | ' | | | | ' | | |
| | ' | | | | ' | | |
| | ' | | | | ' | | |
| | ' | | | | ' | | |
| | ' | | | | ' | | |
| | ' | | | | ' | | |

| | ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| መረጃ ሰብሳቢ | ተመስገን አህመድ | [signature] | 5/13/95 |
| መስክ ተቆጣጣሪ | ማለዳ ክፍሌ | [signature] | 4/11/96 |
| የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ | ንጉሴ ደበበ | [signature] | 20/11/96 |

1. ጠቅላላ የግብርና ቤተሰቦች ብዛት 191
2. ራንደም ኢንተርቫል 7
3. ራንደም ስታርት 2

ገጽ ____ ከ ____ ገጾች

## ክፍል 2 - የቤተሰቦችና የግብርና የግል ባለይዞታዎች ዝርዝርና የምርጫ ቅደም ተከተል

| 1 | 2 | 3 | | 4 | 5 | 6 | 7 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቤተሰብ መለያ ቁጥር | የቤተሰብ ኃላፊ ስም ከነአያት | በቤተሰቡ ውስጥ የግብርና የግል ባለይዞታ አለ → 1 የለም → 2 | ኮድ | በቤተሰቡ ውስጥ የግብርና የግል ይዞታ ያላቸው ባለይዞታዎች ተከታታይ ተራ ቁጥር | የባለይዞታው ሙሉ ስም | የግብርና የግል ባለይዞታ ያላቸው ቤተሰቦች ተከታታይ ቁጥር | የአመራረጥ ቅደም ተከተል |
| 018 | ከቶ ታችበሌ በቀለ [illegible] | አለ | 1 | 1 | ከቶ ታችበሌ በቀለ | 015 | |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| 058 | ወ/ሮ ታየች በለው [illegible] | የለም | 2 | – | – | – | |
| 059 | ከቶ ሀብታሙ [illegible] | አለ | 1 | 1 | ከቶ [illegible] | 060 | |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| 078 | ከቶ ሀብቴ ነጋ [illegible] | አለ | 1 | 1 | ከቶ ሀብቴ ነጋ | 065 | 10 |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| 128 | ከቶ በላይነህ ዘውዴ [illegible] | አለ | 1 | 1 | ከቶ በላይነህ ዘውዴ | 114 | 17 |
| | | | | 2 | ከቶ [illegible] | | |
| 129 | ወ/ሮ [illegible] | የለም | 2 | – | – | – | |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| 166 | ወ/ሮ [illegible] | አለ | 1 | 1 | ወ/ሮ [illegible] | 142 | 21 |
| | 〃 | 〃 | | | 〃 | | |
| | 〃 | 〃 | | | 〃 | | |
| | 〃 | 〃 | | | 〃 | | |
| | 〃 | 〃 | | | 〃 | | |
| | 〃 | 〃 | | | 〃 | | |
| 176 | ከቶ [illegible] | አለ | 1 | 1 | ከቶ [illegible] | 163 | 24 |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| 184 | ከቶ በላይ ታደሰ [illegible] | አለ | 1 | 1 | ከቶ በላይ ታደሰ | 170 | 25 |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| | 〃 | | | | 〃 | | |
| 196 | ከቶ በቀለ [illegible] | አለ | 1 | 1 | ከቶ በቀለ [illegible] | 190 | |
| 197 | ከቶ [illegible] | አለ | 1 | 1 | ከቶ [illegible] | 191 | |

ገጽ ____ ከ ____ ገጾች

## [1]የቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/1 የናሙና ቤተሰቦች ዝርዝር አሞላል

በዚህ ቅጽ ላይ ለግ.ና.ጥ. የተመረጡትን 25 ቤተሰቦች እንደአመራረጥ ቅደም ተከተላቸው ከቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/0 በማወራረስ ይመዘገባሉ:: በተጨማሪም በተመረጡ ቤተሰቦች ውስጥ የሚገኙ የግብርና ባለይዞታዎች የሚያከናውኑትን የግብርና ዓይነት መረጃ ሰብሳቢው ከቤት ወደ ቤት ተዘዋውሮ በመጠየቅ በዚሁ ቅጽ ላይ ይመዘግባል::

**ክፍል 1** **የአካባቢ መለያ**

**ዓምድ 1** **ክልል**

በዚህ ዓምድ ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል ስም ከቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/0 ክፍል 1 ዓምድ 1 በመውሰድ ይሞላል::

**ዓምድ 2** **ዞን**

በዚህ ዓምድ ጥናቱ የሚካሄድበት ዞን ስም ከቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/0 ክፍል 1 ዓምድ 2 በመውሰድ ይሞላል::

**ዓምድ 3** **ወረዳ**

በዚህ ዓምድ ጥናቱ የሚካሄድበት ወረዳ ስም ከቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/0 ክፍል 1 ዓምድ 3 በመውሰድ ይሞላል::

**ዓምድ 4** **ገበሬ ማኅበር**

በዚህ ዓምድ ጥናቱ የሚካሄድበት ገበሬ ማኅበር ስም ከቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/0 ክፍል 1 ዓምድ 4 በመውሰድ ይሞላል::

**ዓምድ 5** **የቆጠራ ቦታ**

በዚህ ዓምድ ጥናቱ የሚካሄድበት የቆጠራ ቦታ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/0 ክፍል 1 ዓምድ 5 በመውሰድ ይሞላል::

**ክፍል 2** **የተመረጡ ቤተሰቦችና የግብርና የግል ባለይዞታዎች ዝርዝር**

**ዓምድ 1** **የቤተሰብ መለያ ቁጥር**

የቤተሰብ መለያ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/0 ክፍል 2 ዓምድ 1 በመውሰድ በዚህ ዓምድ ይሞላል::

---
[1] c:\ease94>96GN1.doc

ዓምድ 2 የቤተሰብ ኃላፊ ስም

በዚህ ዓምድ ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰብ ኃላፊ ስም ከቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/0 ክፍል 2 ዓምድ 2 በመውሰድ ይመዘገባል።

ዓምድ 3 የባለይዞታው መለያ ቁጥር

ይህ ዓምድ ለጥናቱ በተመረጠው ቤተሰብ ውስጥ ለሚገኙ ባለይዞታዎች የተሰጠውን ተራ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/0 ክፍል 2 ዓምድ 4 በማወራረስ ይሞላል።

ዓምድ 4 የባለይዞታው ሙሉ ስም

ይህ ዓምድ ለጥናቱ በተመረጠ ቤተሰብ ውስጥ ለሚገኙ ባለይዞታዎች የእያንዳንዱን የግል ባለይዞታ ስም ከቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/0 ክፍል 2 ዓምድ 5 በመውሰድ ይሞላል።

ዓምድ 5 የግብርናው ዓይነት/ሰብል = 1፣ ከብት = 2፣ ሁለቱም = 3/

በዓምድ 4 ስሙ የተመዘገበው እያንዳንዱ ባለይዞታ የተሰማራበት የግብርና ዓይነት ተጠይቆ የተሰማራበት የግብርና ዓይነት በሰብል ማምረት ብቻ ከሆነ ሰብል ተብሎ ኮድ «1» በከብት ማርባት/ማደለብ/ ብቻ ከሆነ ከብት ተብሎ ኮድ «2» በሁለቱም ከሆነ ደግሞ ሁለቱም ተብሎ ኮድ «3» በዚህ ዓምድ በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ይሞላል።

ዓምድ 6 የአመራረጥ ቅደም ተከተል

የግል ባለይዞታ ያላቸው ቤተሰቦች የአመራረጥ ቅደም ተከተል ከቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/0 ክፍል 2 ዓምድ 7 በመውሰድ በቅደም ተከተል በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 7 አስተያየት

በዚህ ዓምድ ለስ.ት.ጥ. የተመረጡ ቤተሰቦች በየአንፃራቸው ሰ.ት.ጥ. ተብሎ የሚፃፍ ሲሆን ቅጹን ለመሙላት ያጋጠሙ ችግሮችና ሌሎች አስፈላጊና መገለጽ ያለባቸው አስተያየቶችም ይሰፍራሉ።

ማስታወሻ፡-

ከቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/0 ወደ ቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/1 የተመረጡ ቤተሰቦችና ባለይዞታዎች እንዴት እንደሚተላለፉ የሚቀጥለውን ምሣሌ ይመልከቱ።

በመጨረሻም የመረጃ ሰብሳቢው፣ የመስክ ሥራ ተቆጣጣሪውና የዞን አስተባባሪው ስለስራው ትክክለኛነት ስማቸውን፣ ፊርማቸውንና ስራው የተጠናቀቀበት ቀን በተገቢው ቦታ ማስፈር አለባቸው።

ቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/1

## የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን[1]
## በብሔራዊ የተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም
## የግብርና ናሙና ጥናት 1996 ዓ.ም.

ክፍል 1 - የአካባቢ መለያ

| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|
| ክልል | ዞን | ወረዳ | ገበሬ ማኅበር | ቆጠራ ቦታ |
| አማራ | ሰሜን ሸዋ | ኬዣጠርች | ቀዩ ኩዴር | 01 |

ክፍል 2 - የተመረጡት ቤተሰቦችና የግብርና የግል ባለይዞታዎች ዝርዝር

| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | | 6 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቤተሰብ መለያ ቁጥር (ከቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/0 ዓምድ 1) | የቤተሰቡ ኃላፊ ስም ከነአያት (ከቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/1 ዓምድ 2) | የባለይዞታው መለያ ቁጥር (ከቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/0 ዓምድ 4) | የግል ባለይዞታው ሙሉ ስም | የግብርናው ዓይነት ሰብል → 1 ከብት → 2 ሁለቱም → 3 | ኮድ | የአመራረጥ ቅደም ተከተል (ከቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/0 ዓምድ 7) | አስተያየት |
| 002 | አቶ ደምሴ ጉጂ ታዬ | 1 | አቶ ደምሴ ጉጂ | ሁለቱም | 3 | 01 | |
| 011 | አቶ ታደሰ ደስታ ወልዴ | 1 | አቶ ታደሰ ደስታ | ሁለቱም | 3 | 02 | ስ.ች.ኘ. |
| | ' | | ' | | | ' | |
| | ' | | ' | | | ' | |
| | ' | | ' | | | ' | |
| | ' | | ' | | | ' | |
| 078 | አቶ ሀብቴ ነጋ ገበየ | 1 | አቶ ሀብቴ ነጋ | ሰብል | 1 | 10 | |
| | ' | | ' | | | ' | |
| | ' | | ' | | | ' | |
| | ' | | ' | | | ' | |
| | ' | | ' | | | ' | |
| 128 | አቶ ብርሀኑ ዘዉዴ በለጠ | 1 | አቶ ብርሀኑ ዘዉዴ | ሁለቱም | 3 | 17 | ስ.ች.ኘ. |
| | ' | 2 | አቶ ሙሉሀን ልዑል | ከብት | 2 | | |
| | ' | | ' | | | | |
| | ' | | ' | | | | |
| 166 | ወ/ሮ ሀዋ መኮንን | 1 | ወ/ሮ ሀዋ መኮንን | ሰብል | 1 | 21 | |
| | ' | | ' | | | | |
| | ' | | ' | | | | |
| | ' | | ' | | | | |
| | ' | | ' | | | | |
| | ' | | ' | | | | |
| | ' | | ' | | | | |
| | ' | | ' | | | | |
| | ' | | ' | | | | |
| | ' | | ' | | | | |
| | ' | | ' | | | | |
| | ' | | ' | | | | |

| | ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| መረጃ ሰብሳቢ | ተስፋዬ አንዳርጌ | [signature] | 5/13/96 |
| መስክ ተቆጣጣሪ | ግርማ ፈይሳ | [signature] | 4/1/96 |
| የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ | ንጉሴ ደበበ | [signature] | 20/1/96 |

ገጽ ____ ከ ____ ገጾች

[1] c:\ease94>cro961.doc

ክፍል 2 - የተመረጡት ቤተሰቦችና የግብርና የግል ባለይዞታዎች ዝርዝር

| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | | 6 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቤተሰብ መለያ ቁጥር (ከቅጽ ግ.ና.ፕ. 96/0 ዓምድ 1) | የቤተሰቡ ኃላፊ ስም ከነአያት (ከቅጽ ግ.ና.ፕ. 96/1 ዓምድ 2) | የባለይዞታው መለያ ቁጥር (ከቅጽ ግ.ና.ፕ. 96/0 ዓምድ 4) | የግል ባለይዞታው ሙሉ ስም | የግብርናው ዓይነት<br>ሰብል → 1<br>ከብት → 2<br>ሁለቱም → 3 | ኮድ | የአመራረጥ ቅደም ተከተል (ከቅጽ ግ.ና.ፕ. 96/0 ዓምድ 7) | አስተያየት |
| 176 | ከዩ ጴጥ በለጫ ዘሩ | 1 | ከዩ ጴጥ በለጫ | ሁለቱም | 3 | 24 | ሱ.ፕ.ሻ. |
| 184 | ከዩ በለጫ ታሪኩ ላቀው | 1 | ከዩ በለጫ ታሪኩ | ሁለቱም | 3 | 25 | |

ገጽ ____ ከ ____ ገጾች

## የቅጽ ግ.ና.ፕ 96/3ሀ - በጊዜያዊ ሰብሎች (አትክልትና ሥራሥርን ጨምሮ) የተያዙ ማሣዎች ዝርዝርና የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ በመኸር ወቅት አሞላል

ይህ ቅጽ በቆጠራ ቦታው በተመረጡ ቤተሰቦች ውስጥ ለሚገኙ ባለይዞታዎች በሙሉ የሚሞላ ነው:: በዚህ ቅጽ በዋናው መኸር ወቅት በጊዜያዊ ሰብሎች የተያዙ ማሳዎች (አትክልትና ሥራሥርን ጨምሮ) የሚዘረዘሩበትና አጠቃላይ የእርሻ ሥራ ሁኔታው ክትትል የሚደረግበት ነው::

### ክፍል 1. የአካባቢ መለያ

ዓምድ 1 - ክልል

ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 2 - ዞን

ጥናቱ የሚካሄድበት ዞን ስም ወይንም ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 3 - ወረዳ

ጥናቱ የሚካሄድበት ወረዳ ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 4 - ገበሬ ማህበር

ጥናቱ የሚካሄድበት የገበሬ ማህበር ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 5 - ቆጠራ ቦታ

ጥናቱ የሚካሄድበት ቆጠራ ቦታ ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 6 - የቤተሰብ መለያ ቁጥር

የተመረጠው ቤተሰብ መለያ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ፕ 96/1 ክፍል 2 ዓምድ 1 በመውሰድ ይሞላል::

ዓምድ 7 - የባለይዞታው መለያ ቁጥር

ይህ ዓምድ በቆጠራው ቦታ በተመረጠው ቤተሰብ ውስጥ ለሚገኙ የግል ባለይዞታዎች የተሰጠውን መለያ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ፕ 96/1 ክፍል 2 ዓምድ 3 በመውሰድ ይሞላል::

ዓምድ 8 - የባለይዞታው ስም

የባለይዞታው ስም ከቅጽ ግ.ና.ፕ 96/1 ክፍል 2 ዓምድ 4 በመውሰድ ይሞላል::

ዓምድ 9 - ዕድሜ

የባለይዞታው ትክክለኛ ዕድሜ ተጠይቆ በሙሉ ዓመት (የጨረሰው ዓመት) በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ምሣሌ:- የአንድ ሰው ዕድሜ 8 ዓመት ከ11 ወር ከ29 ቀን ቢሆን መመዝገብ ያለበት ዕድሜ 08 ዓመት ብቻ ይሆናል:: የአንድ ህፃን ዕድሜ ከ1 ዓመት በታች ከሆነ "00" ይመዘገባል:: እንዲሁም የአንድ ሰው ዕድሜ 97 እና ከዚያ በላይ ከሆነ "97" ብቻ ይመዘገባል:: ዕድሜያቸውን በትክክል የማያውቁ ወይንም ለመናገር ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎች እንደሚያጋጥሙ ይታወቃል:: ስለዚህ የእያንዳንዱን ቤተሰብ አባል ትክክለኛ ዕድሜ በተቻለ መጠን ለማግኘት ባለመሰልቸት ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል::

ዓምድ 10 - ፆታ (ወንድ = 1 ሴት = 2)

ባለይዞታው ወንድ ከሆነ ኮድ «1» ሴት ከሆነች ኮድ «2» በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 11 - የትምህርት ሁኔታ (የፈጸሙት ከፍተኛ ክፍል)

በዚህ ዓምድ የባለይዞታው የትምህርት ሁኔታ (የፈፀሙት ከፍተኛ ክፍል) ተጠይቆ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ኮዶች ትክክለኛው ተመርጦ ይሞላል:: በመጀመሪያ ባለይዞታው ማንበብና መፃፍ የሚችል መሆኑ ከተጠየቀ በኋላ የሚችል ከሆነ ተምሮ የጨረሰው ከፍተኛ ክፍል ይጠየቃል:: አንድ ባለይዞታ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ አለው የሚባለው በማንኛውም ባለይዞታው በሚያውቀው ቋንቋ አንብቦ መረዳትና መፃፍ ሲችል ብቻ ነው:: የራሳቸውን ስም ወይንም ቁጥሮችን ብቻ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ባለይዞታዎች እንደተማሩ አይቆጠሩም:: በተጨማሪም የፈፀመው ክፍል ሲባል በጥናቱ ወቅት የሚገኝበት ክፍል ሳይሆን ተምሮ የጨረሰው ከፍተኛ ክፍል ማለት ነው::

ለትምህርት ደረጃ የተሰጡ ኮዶች:-

| | | |
|---|---|---|
| መፃፍና ማንበብ የማይችሉ | ኮድ | 01 |
| መደበኛ ያልሆነ ትምህርት | "" | 02 |
| 1ኛ ክፍል ያጠናቀቁ | "" | 03 |
| 2ኛ "" "" | "" | 04 |
| 3ኛ "" "" | "" | 05 |
| 4ኛ "" "" | "" | 06 |
| 5ኛ "" "" | "" | 07 |
| 6ኛ "" "" | "" | 08 |
| 7ኛ "" "" | "" | 09 |
| 8ኛ "" "" | "" | 10 |
| 9ኛ "" "" | "" | 11 |
| 10ኛ "" "" | "" | 12 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 11ኛ | "" | "" | "" | 13 |
| 12ኛ | "" | "" | "" | 14 |
| ከ12ኛ ክፍል በላይ | | | "" | 15 |

*ማሳሰቢያ:-*

1. *መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ማለት በመደበኛ የትምህርት ደረጃ አመዳደብ ሊመደብ በማይችል የትምህርት መስጫ ድርጅት ትምህርት በመከታተል ላይ ላሉ /የተከታተሉ ለምሣሌ በቄስና በቁርአን ት/ቤት ፣ በመሠረተ ትምህርት ... ወዘተ ማለት ነው::*

2. *ኮድ 14 የሚሞላላቸው የሚከተሉት ናቸው*

*ሀ) የ12ኛ ክፍልን መልቀቂያ ፈተና የወሰዱ ነገር ግን ከዚያ ያለፈ መደበኛ ትምህርት የሌላቸው::*

*ለ) 12ኛ ከጨረሱ በኋላ አንዳንድ የሙያ ትምህርት የተከታተሉ ለምሳሌ/የታይፕ ጸሀፊት/*

*ሐ) በሙያ ትምህርት ቤቶች ተምረው ከ12ኛ መልቀቂያ ሰርተፊኬት ሌላ ተጨማሪ ዲፕሎማ ያገኙ ባለይዞታዎችም ዲፕሎማው የከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን ከ12ኛ ክፍል በላይ የሆነ ትምህርት ብሎ እስካልቆጠረው ድረስ ኮድ 14 ይመዘገብላቸዋል::*

ዓምድ 12 - የባለይዞታው የቤተሰብ አባላት ብዛት

የባለይዞታው የቤተሰብ አባላት ብዛት ተጠይቆ በዚህ ዓምድ ውስጥ ይሞላል:: በተጨማሪም በተመረጠው ቤተሰብ ወስጥ ከአንድ በላይ ባለይዞታ ካለ የቤተሰብ አባላት ብዛት በሚጠየቅበት ጊዜ ብዛት ለእያንዳንዱ ባለይዞታ ተደጋግሞ ይሞላል::

ዓምድ 13 - የግብርናው ዓይነት /ሰብል = 1 ከብት = 2 ሁለቱም= 3/

በዓምድ 7 መለያ ቁጥሩ የተመዘገበው እያንዳንዱ ባለይዞታ የተሰማራበት የግብርና ዓይነት ተጠይቆ ሰብል ማምረት ብቻ ከሆነ ኮድ «1» ከብት ማርባት /ማደለብ/ ብቻ ከሆነ ኮድ «2» ሁለቱም ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» በዚህ ዓምድ ይሞላል::

## ክፍል 2. በጊዜያዊ ሰብሎች (አትክልትና ሥራሥርን ጨምሮ) የተያዙ ማሣዎች ዝርዝርና የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ

ይህ ክፍል የሚያገለግለው ባለይዞታው በ1996 ዓ.ም በመኸር ወቅት ያሉትን በጊዜያዊ ሰብል የተያዙ ማሳዎች ለመመዝገብና የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታን ለመከታተል ነው። በዚህ ቅጽ ስምንት ማሣዎችን ለመመዝገብና ሌሎች የእርሻ ሥራን አጠቃላይ ሁኔታ የሚመለከቱ መረጃዎች ለመሰብሰብ የሚያስችል ቦታ (ከዓምድ 3 - ዓምድ 6 ከፊት ለፊትና ከዓምድ 7 - 10 በጀርባ) ተሰጥቷል። ከስምንት በላይ የሆኑ በጊዜያዊ ሰብል የተያዙ ማሣዎች ሲያጋጥሙ ተጨማሪ ቅጽ መጠቀም ያስፈልጋል።

ዓምድ 1 - ተራ ቁጥር

ተራ ቁጥር ከ01 በመጀመር በቅደም ተከተል ተሞልቷል።

ዓምድ 3-6 - የፓርስል ቁጥር ፣ የማሣ ቁጥርና የሰብል ስም

መረጃ የሚሰበሰብላቸው ጊዜያዊ ሰብሎች የሚገኙባቸው ፓርስሎች በሙሉ የፓርስል ቁጥር ይሰጣቸዋል። እንዲሁም በእያንዳንዱ ፓርስል ለሚገኙ ማሣዎች ተከታታይ የማሣ ቁጥር ይሰጣቸውና የሰብሉ ስም ደግሞ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል። ለኮድ የተሰጠው ቦታ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም።

*ማስታወሻ:-*

*በአንድ ባለይዞታ የተያዙ የተለያዩ ፓርስሎችና ማሣዎችን በተመለከተ የሚሰጡ የፓርስልና ማሣ ቁጥሮች ተከታታይነት ባለው መንገድ በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሀ፣ 3ለ፣ 3ሐ ና 3መ የተሰጡትን በማገናዘብ ይሆናል።*

ዓምድ 2 - ለባለይዞታዎች የሚቀርቡ ጥያቄዎች

ጥያቄ 1:- የይዞታው ዓይነት:- ባለይዞታው ያስመዘገበው እያንዳንዱ ማሳ የባለይዞታው የራሱ ከሆነ ኮድ «1»፣ በኪራይ ወይም በኮንትራት የተገኘ ከሆነ ኮድ «2»፣ ከእነዚህ ውጭ በሆነ መንገድ የተገኘ ከሆነ ኮድ «3» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል።

ጥያቄ 2:- የማሣው ስፋት በአካባቢ መለኪያ

ባለይዞታው ያስመዘገበው እያንዳንዱ ማሣ ስፋቱ በአካባቢ መለኪያ ተጠይቆ የአካባቢው መለኪያ ስምና የእያንዳንዱ ማሣ ስፋት መጠን በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል። ለኮድ የተሰጠው ቦታ ምንም አይሞላበትም።

ጥያቄ 3:- ማሣው በኤክስቴንሽን መርሀ-ግብር ታቅፏል? (አዎን =1 የለም =2)

ባለይዞታው ያስመዘገበውን እያንዳንዱን ማሣ አስመልክቶ በኤክስቴንሽን መርሀ-ግብር መታቀፉን ተጠይቆ ከታቀፈ ኮድ «1» ካልታቀፈ ደግሞ ኮድ «2» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል::

*ማስታወሻ:-*

*በኤክስቴንሽን መርሀ-ግብር የታቀፈ ገበሬ ማለት በዘመናዊ አስተራረስ የሚጠቀምና ለዚህም በአካባቢው ከሚገኘው የልማት ሠራተኛ የቅርብ እገዛ፣ ትምህርትና ምክር የሚያገኝ ነው:: ዘመናዊ አስተራረስ ሲባልም በጥናት የተደረሰበት አሠራርን መሠረት በማድረግ ለእያንዳንዱ የሰብል ዓይነት:-*

- *የማሣ አዘገጃጀት*
- *በጥቅም ላይ መዋል የሚገባው የማዳበሪያ ዓይነት አጠቃቀምና መጠን... ወዘተ*

*አሠራሩን ተግባራዊ ማድረግ ማለት ነው::*

ጥያቄ 4:- የመስኖ ዘዴ ተጠቀመዋል? (አዎን = 1 የለም = 2)

ባለይዞታው እያንዳንዱን ያስመዘገበውን ማሣ በማስመልከት በማሳው ላይ ያለውን ሰብል ለማምረትም ሆነ ምርትን ለማሻሻል የመስኖ ዘዴ መጠቀሙ ተጠይቆ ተጠቅሞ ከሆነ ኮድ «1» ፣ ካልተጠቀመ ደግሞ ኮድ «2» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ጥያቄ 5:- የዘር ዓይነት (ምርጥ ዘር = 1 ምርጥ ዘር ያልሆነ= 2)

ባለይዞታው በእያንዳንዱ ባስመዘገበው ማሣ ላይ የተጠቀመው የዘር ዓይነት ተጠይቆ ምርጥ ዘር ከሆነ ኮድ «1» ፣ ምርጥ ዘር ካልሆነ ደግሞ ኮድ «2» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ጥያቄ 6:- የተጠቀሙት ምርጥ ዘር ካልሆነ (በጥያቄ 5 ኮድ 2 ለተሞላላቸው) መጠን በኪሎ ግራም

ይህ ጥያቄ የሚጠየቀው ለብርዕ፣ አገዳ፣ ጥራጥሬና ቅባት ሰብሎች ብቻ ሲሆን ባለይዞታው ባስመዘገበው እያንዳንዱ ማሣ ላይ የሚገኘውን ሰብል አስመልክቶ ለዘር የተጠቀመው የአካባቢ ዘር ከሆነ መጠኑ በኪሎ ግራም ተጠይቆ በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ጥያቄ 7:- <u>የተጠቀሙት ምርጥ ዘር ከሆነ መጠን በኪ. ግራም (በጥያቄ 5 ኮድ «1» ለተሞላላቸው)</u>

ይህ ጥያቄ የሚጠየቀው ለብርዕ፣ አገዳ፣ ጥራጥሬና ቅባት ሰብሎች ብቻ ሲሆን ባለይዞታው ባስመዘገበው እያንዳንዱ ማሳ ላይ የሚገኘውን ሰብል አስመልክቶ ለዘር የተጠቀመው ምርጥ ዘር ከሆነ መጠኑ በኪሎ ግራም ተጠይቆ በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ጥያቄ 8:- <u>የተጠቀሙት ምርጥ ዘር ከሆነ ዋጋ (በጥያቄ 5 ኮድ «1» ለተሞላላቸው)</u>

በጥያቄ 5 ኮድ «1» ተሞልቶ በጥያቄ 7 መጠኑ የተጠቀሰው ምርጥ ዘር ዋጋው ምን ያህል እንደሆነ ተጠይቆ የተገኘው መልስ በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ጥያቄ 9:- <u>የሰብል ብልሽት ደርሷል? (አዎን = 1 የለም = 2)</u>

በእያንዳንዱ ማሣ ላይ ያለውን ሰብል አስመልክቶ የሰብል መበላሸት መድረሱን ባለይዞታው ተጠይቆ ደርሶ ከሆነ ኮድ «1» ካልደረሰ ደግሞ ኮድ «2» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ጥያቄ 10:- <u>የሰብል ብልሽት ደርሶ ከሆነ ለብልሽቱ አንድ ዋና ምክንያት</u>

ይህ ዓምድ የሚሞላው በጥያቄ 9 የሰብል መበላሸት ደርሷል ተብሎ ኮድ «1» የተሞላ እንደሆነ ብቻ ነው:: ስለዚህ የሰብል መበላሸት ደርሶ ከሆነ በዚህ የመረጃ ሰብሳቢዎች መመሪያ ገጽ 19 ከተዘረዘሩት የሰብል ብልሽት ምክንያቶች ውስጥ ዋነኛ የሆነው ምክንያት ተወስዶ በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል:: ለኮድ የተሰጠው ቦታ ምንም አይሞላበትም::

ጥያቄ 11:- <u>የብልሽት መጠን በመቶኛ</u>

በጥያቄ 10 በተገለጸው ምክንያት በሰብል ላይ ጉዳት የደረሰ ከሆነ ሰብሉ የተበላሸው ወይም ጉዳት የደረሰበት ሰብል ከማሣው ጠቅላላ ስፋት ምን ያህሉን እንደሚሸፍን በመቶኛ ባለይዞታው ተጠይቆ የተገኘው መልስ በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል:: <u>ለምሣሌ</u>:- ባለይዞታው ማሣው ላይ ከሚገኘው ሰብል ከጠቅላላ ማሣው ስፋት ሩብ ያህሉን የሸፈነው ተበላሽቷል ቢል በተሰጠው ቦታ «25» መሞላት አለበት::

ጥያቄ 12:- ብልሽቱን ለመከላከል /ለጥንቃቄ/ የተወሰደ እርምጃ (አለ = 1 የለም = 2)

ብልሽት የደረሰበትን እያንዳንዱን ማሣ አስመልክቶ ባለይዞታው የደረሰውን የሰብል ብልሽት ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ ወይም አስቀድሞ ለመከላከል የወሰደው እርምጃ ካለ ኮድ «1»፣ ከሌለ ደግሞ ኮድ «2» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

ጥያቄ 13:- የተወሰደው እርምጃ ዓይነት (ኬሚካል = 1 ኬሚካል ያልሆነ = 2 ሁለቱም = 3)

ባለይዞታው የሰብሉን ብልሽት ለማስወገድ ወይም አስቀድሞ ለመከላከል የተጠቀመው መድኃኒት ኬሚካል ከሆነ ኮድ «1»፣ ኬሚካል ካልሆነ ኮድ «2»፣ ሁለቱም ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

ጥያቄ 14:- ለጥያቄ 13 ኮድ «1» ወይም ኮድ «3» ከተሞላ (ኬሚካል ከተጠቀሙ ዓይነቱ (ፀረ-ተባይ =1፣ ፀረ-አረም =2 ፀረ-በሽታ =3፣ 1ና2 =4 1ና3 =5፣ 2ና3 =6 ሁሉም =7)

ባለይዞታው በጥያቄ 13 የወሰደው የእርምጃ ዓይነት ኬሚካል ከሆነ (ኮድ «1» ወይም ኮድ «3» ከተሞላ) ለእያንዳንዱ ማሣ ምን ዓይነት ኬሚካል እንደተጠቀመ ተጠይቆ ፀረ-ተባይ ከሆነ ኮድ «1»፣ ፀረ-አረም ከሆነ ኮድ «2»፣ ፀረ-በሽታ ከሆነ ኮድ «3»፣ ፀረ-ተባይ እና ፀረ-አረም ከሆነ ኮድ «4»፣ ፀረ-ተባይ እና ፀረ-በሽታ ከሆነ ኮድ «5»፣ ፀረ-አረም እና ፀረ-በሽታ ከሆነ ኮድ «6»፣ ሁሉንም ዓይነት ከሆነ ደግሞ ኮድ «7» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

ጥያቄ 15:- የተፈጥሮ /የኬሚካል ማዳበሪያ ተጠቅመዋል? (አዎን = 1 የለም = 2)

ባለይዞታው ባስመዘገበው በሰብል በተያዘ በእያንዳንዱ ማሣ ላይ ሊገኝ የሚችለውን ምርት ለማሻሻል ማዳበሪያ መጠቀም አለመጠቀሙ ተጠይቆ ተጠቅሞ ከሆነ ኮድ «1»፣ ያልተጠቀመ ከሆነ ደግሞ ኮድ «2» በእያንዳንዱ ማሣ አንፃር ይሞላል።

ጥያቄ 16:- ከተጠቀሙ የማዳበሪያው ዓይነት (የተፈጥሮ = 1 ኬሚካል = 2 ሁለቱም = 3)

ባለይዞታው ማዳበሪያ ተጠቅሞ በጥያቄ 15 ኮድ «1» ተሞልቶ ከሆነ የማዳበሪያው ዓይነት ይጠየቃል። በዚሁ መሠረት ጥቅም ላይ የዋለው የማዳበሪያ ዓይነት የተፈጥሮ ከሆነ ኮድ «1» ኬሚካል ከሆነ ኮድ «2»፣ ሁለቱም ዓይነት ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

ጥያቄ 17:- ኬሚካል ማዳበሪያ ካልተጠቀሙ አንድ ዋና ምክንያት (በጥያቄ 16 ኮድ «1» ከተሞላ

ባለይዞታው ማዳበሪያ መጠቀም አለመጠቀሙ በጥያቄ 15 ላይ ተጠይቆ ኮድ «2» ከተሞላ ወይም ማዳበሪያ ተጠቅሞ በጥያቄ 16 ኮድ «1» ከተሞላ ኬሚካል ማዳበሪያ ያልተጠቀመበትን ምክንያት ተጠይቆ ምክንያቱ በጥያቄ 17 ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ምክንያቶች በመምረጥ ምክንያቱና ትክክለኛው ኮድ ይሞላል።

ዋና ዋና ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው

- ጥቅሙን ካለማወቅ = 1
- ውድ ስለሆነ = 2
- የገንዘብ ዕጥረት = 3
- የአቅርቦት ዕጥረት = 4
- የብድር አገልግሎት አለመኖር = 5
- ውጤታማነቱ አጠራጣሪ ስለሆነ = 6
- ሌላ ካለ ይገለጽ = 7

ማስታወሻ

ይህ ጥያቄ (ጥያቄ 7) የሚጠየቀው ለእያንዳንዱ ማሳ ስለሆነ ባለይዞታው የሚሰጠው አንድ ዋና ምክንያት ሆኖ ይኸው ምክንያት ለሁሉም ማሳዎች ይመዘገባል እንጂ ለተለያዩ ማሳዎች የተለያየ ምክንያት መመዝገብ የለበትም።

በጥያቄ 18:- ኬሚካል ማዳበሪያ ከተጠቀሙ (በጥያቄ 16 ኮድ «2» ወይም «3» ከተሞላ)

ጥያቄ 18.1:- ዓይነት

ባለይዞታው የተጠቀመው የኬሚካል ማዳበሪያ ዓይነቱ ተጠይቆ ዩሪያ ከሆነ ኮድ «1»፣ ዳፕ ከሆነ ኮድ «2»፣ ሁለቱም ዓይነት ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» እያንዳንዱን ማሣ አስመልክቶ በተሰጠው ቦታ ይሞላል::

ጥያቄ 18.2:- መጠን በኪሎ ግራም

በጥያቄ 18.1 ዓይነቱ የተገለጸውን ማዳበሪያ መጠን ባለይዞታው ተጠይቆ መልሱ በኪሎ ግራም በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል:: ሆኖም ባለይዞታው የማዳበሪያውን መጠን በኪሎ ግራም መግለጽ ካልቻለ ማዳበሪያውን ሲገዛ ወይም ጥቅም ላይ ሲያውል መጠኑን ለመለካት የተጠቀመበትን የመለኪያ ዕቃ (ጣሳ፣ ቁና፣ ሳህን፣ ... ወዘተ ) በመጠቀም ባለይዞታው ማዳበሪያ ካለው የራሱን በመውሰድ ከሌለው ደግሞ በአካባቢው ማዳበሪያ ያለውን ቤተሰብ በማፈላለግ ይህም ካልሆነ ማዳበሪያ ሊገኝ ከሚችልበት ማለትም ከገበያ ከልማት ወኪሎች ከግብርና መ/ቤቶች ... ወዘተ ለጊዜው በመውሰድ መጀመሪያ ባዶውን እቃ ቀጥሎ ደግሞ ማዳበሪያውን አስይዞ ከመዘነ በኋላ የዕቃውን ክብደት በመቀነስ የሚገኘው ክብደት በጥቅም ላይ የዋለውን ማዳበሪያ መጠን ስለሚገልፅ ውጤቱን በተሰጠው ክፍት ቦታ ውስጥ መሙላት አስፈላጊ ነው::

ለበለጠ ማብራሪያ የሚከተለውን ምሣሌ ይመልከቱ :-

ምሣሌ:- ባለይዞታው አንድ ሣህን ማዳበሪያ በጤፍ ማሳው ላይ እንደተጠቀመና በኪሎ ግራም ምን ያህል እንደሆነ የማያውቅ መሆኑን ቢገልጽ መረጃ ሰብሳቢው በጥቅም ላይ የዋለውን ማዳበሪያ መጠን በኪሎ ግራም በጥያቄ 18.2 ማስፈር ስለሚገባው መጠኑን በኪሎ ግራም ለማግኘት የሚከተለውን አሠራር መከተል ይኖርበታል::

1. ባለይዞታው በጥቅም ላይ ያዋለውን ማዳበሪያ መጠን የለካበትን ዕቃ ባዶውን ይመዝናል:: በዚህ መሠረት የዕቃው ክብደት 500 ግራም ቢሆን፣

2. በመቀጠልም ከባለይዞታው ወይም ከሌሎች ቤተሰቦች ወይም ደግሞ ከገበያ፣ ወይም ከልማት ወኪሎች ... ወዘተ ያገኘውን ማዳበሪያ በዕቃው ወስጥ በማድረግ መዝኖ የተገኘው ክብደት 9.500 ኪሎ ግራም ቢሆን፣

3. በመጨረሻም ማዳበሪያውን ከነዕቃው መዝኖ ከተገኘው ክብደት ዕቃው ባዶውን ተመዝኖ ያገኘውን ክብደት ይቀንሳል። በዚህም መሠረት 9.500 ኪሎ ግራም ላይ 500 ግራም ሲቀነስ 9 ኪሎ ግራም ይሆናል። (9.500 - 0.500 = 9.000) ይህ መጠን በጥቅም ላይ የዋለውን የማዳበሪያ መጠን ስለሚገለጽ በጥያቄ 18.2 በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

*ማስታወሻ፡*

*ነጭ የማዳበሪያ ዓይነት «ዩሪያ» ሲሆን ቡላ (ግሬይ) ደግሞ «ዳፕ» ነው።*

ጥያቄ 19:- <u>የተፈጥሮ ማዳበሪያ ከተጠቀሙ (በጥያቄ 16 ኮድ 1 ወይም 3 ከተሞላ) ዓይነት</u>

ባለይዞታው በጥያቄ 16 የተፈጥሮ ማዳበሪያ መጠቀሙን ገልጾ ኮድ «1» ወይም «3» ከተሞላ የተጠቀመው የማዳበሪያ ዓይነት ተጠይቆ የከብቶች ፍግ ከሆነ ኮድ «1»፣ የተለያየ ብስባሽ ከሆነ ኮድ «2»፣ ሁለቱንም ዓይነት የተጠቀመ ከሆነ ኮድ «3» ከነዚህ ውጪ ሌላ ከሆነ በዚህ ጥያቄ ትይዩ በተሰጠው ቦታ ስሙን በመጻፍ ኮድ «4» ይሞላል።

## የቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ለ - በቋሚ ሰብሎች የተያዙ ማሣዎች ዝርዝርና የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ አሞላል

ይህ ቅጽ ለጥናቱ በተመረጡ ቤተሰቦች ውስጥ ለሚገኝ ለእያንዳንዱ ባለይዞታ የሚሞላ ሲሆን ቅጹ በቋሚ ሰብሎች የተያዙ ማሣዎች የሚዘረዘሩበትና የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ መረጃ የሚሰበሰብበት ነው።

ክፍል 1:- የአካባቢ መለያ

ዓምድ 1 - ክልል

ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 2 - ዞን

ጥናቱ የሚካሄድበት ዞን ስም ወይንም ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 3 - ወረዳ

ጥናቱ የሚካሄድበት ወረዳ ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 4 - ገበሬ ማህበር

ጥናቱ የሚካሄድበት ገበሬ ማህበር ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 5 - ቆጠራ ቦታ

ጥናቱ የሚካሄድበት ቆጠራ ቦታ ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 6 - የቤተሰብ መለያ ቁጥር

የተመረጠው ቤተሰብ መለያ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/1 ክፍል 2 ዓምድ 1 በመውሰድ ይሞላል።

ዓምድ 7 - የባለይዞታው መለያ ቁጥር

በቆጠራ ቦታው በተመረጠው ቤተሰብ ውስጥ ለሚገኙ የግል ባለይዞታዎች የተሰጠውን መለያ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/1 ክፍል 2 ዓምድ 3 በማወራረስ ይሞላል።

ዓምድ 8 - የባለይዞታው ስም

የባለይዞታው ስም ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/1 ክፍል 2 ዓምድ 4 በማወራረስ ይሞላል።

ዓምድ 9- ዕድሜ

የባለይዞታው ዕድሜ ተጠይቆ በሙሉ ዓመት በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 10 - ፆታ (ወንድ = 1 ሴት = 2)

ባለይዞታው ፆታው ወንድ ከሆነ ኮድ «1»፣ ሴት ከሆነች ኮድ «2» በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 11- የትምህርት ሁነታ (የፈፀሙት ከፍተኛ ክፍል)

በዚህ ዓምድ የባለይዞታው የትምህርት ሁኔታ /የፈፀሙት ከፍተኛ ክፍል/ ተጠይቆ ይሞላል:: ማብራሪያውን በገጽ 31 እና 32 ይመልከቱ::

ዓምድ 12 - የባለይዞታው የቤተሰብ አባላት ብዛት

የባለይዘታው የቤተሰብ አባላት ብዛት ተጠይቆ በዚህ ዓምድ ውስጥ ይሞላል:: በተጨማሪም በተመረጠው ቤተሰብ ወስጥ ከአንድ በላይ ባለይዞታ ካለ የቤተሰብ አባላት ብዛት በሚጠየቅበት ጊዜ ብዛት ለእያንዳንድ ባለይዞታ ተደጋግሞ ይሞላል::

ዓምድ 13 - የግብርናው ዓይነት /ሰብል = 1 ከብት = 2 ሁለቱም= 3/

በዓምድ 7 መለያ ቁጥሩ የተመዘገበው እያንዳንዱ ባለይዞታ የተሰማራበት የግብርና ዓይነት ተጠይቆ ሰብል ማምረት ብቻ ከሆነ ኮድ «1» ከብት ማርባት /ማደለብ/ ብቻ ከሆነ ኮድ «2» ሁለቱም ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ክፍል 2:- በቋሚ ሰብል የተያዙ ማሣዎች ዝርዝርና የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ

ዓምድ 1- ተራ ቁጥር

ተራ ቁጥር ከ«01» በመጀመር በቅደም ተከተል ተሞልቷል::

ዓምድ 3-6 -ፓርስል ቁጥር ፣ማሣ ቁጥርና የሰብል ስም

ፓርስል

መረጃ የሚሰበሰብላቸው በቋሚ ሰብሎች የተያዙ ማሣዎች የሚገኙባቸው ፓርስሎች በሙሉ ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሀ ወይም 96/3ሐ ወይም 96/3መ ከተሰጠው ቁጥር ጋር በማገናዘብና የፓርስልን ትርጉም በመጠቀም ቁጥር ይሰጣቸዋል::

*ማሣ*

መረጃ የሚሰበሰብላቸው በቋሚ ሰብሎች የተያዙ ማሣዎች በሙሉ ተከታታይ የማሣ ቁጥር ማለትም ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሀ ወይም 96/3ሐ ወይም 96/3መ ከተሰጠው ቁጥር ጋር በማገናዘብና የተሰጠውን የማሣ ትርጉም በመጠቀም ቁጥር ይሰጣቸዋል::

<u>የሰብል ስም</u>

የባለይዞታው በሆኑ ማሣዎች ላይ የሚገኙ ቋሚ ሰብሎች በሙሉ (ድብልቆችን ሳይጨምር) ለየብቻቸው በዓይነት በተሰጠው ባዶ ቦታ ይመዘገባሉ:: የተሰጠው የኮድ ቦታ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም:: በዚህ ቅጽ በፊት ለፊቱ የአራት ማሣዎችን መረጃ ሊያስሞላ የሚችል ቦታ (ከዓምድ 3 - ዓምድ 6) ተሰጥቷል:: ከአራት በላይ በቋሚ ሰብል የተያዙ ማሣዎች ሲያጋጥሙ ጀርባውን መጠቀም ያስፈልጋል:: ከስምንት በላይ ማሣዎች ካጋጠሙ ግን ተጨማሪ ቅጽ መጠቀም ይቻላል::

<u>ዓምድ 2 - ለባለይዞታው የሚቀርቡ ጥያቄዎች</u>

ጥያቄ 1:- <u>የይዞታው ዓይነት:-</u>

ባለይዞታው ያስመዘገበው እያንዳንዱን ማሳ አስመልክቶ ይዞታው የግል ከሆነ ኮድ «1»፣ በኪራይ ወይም በኮንትራት የተገኘ ከሆነ ኮድ «2»፣ ከእነዚህ ውጭ በሌላ መንገድ የተገኘ ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል::

ጥያቄ 2:- <u>የማሣ ስፋት በአካባቢ መለኪያ</u>

ባለይዞታው ያስመዘገበው እያንዳንዱ የሰብል ዓይነት የያዘው የመሬት ስፋት በአካባቢ መለኪያ ተጠይቆ የመለኪያው ስምና የማሣው ስፋት መጠን በአንጻሩ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል::

ጥያቄ 3:- <u>ማሣው በኤክስቴንሽን መርሀ-ግብር ታቅፏል?</u>

<u>(አዎን =1 አልታቀፈም = 2)</u>

ባለይዞታው ያስመዘገበው እያንዳንዱ ማሣ በኤክስቴንሽን መርሀ-ግብር መታቀፍ አለመታቀፉ ተጠይቆ ከታቀፈ ኮድ «1» ካልታቀፈ ኮድ «2» በተሰጠው ቦታ ይሞላል::

ጥያቄ 4:- <u>የቋሚ ሰብል እግር ብዛት</u>

ባለይዞታው ያስመዘገበው እያንዳንዱ የቋሚ ሰብል ማሣ ያለው ጠቅላላ የቋሚ ሰብል እግር ብዛት ተቆጥሮ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል:: ይህ ጥያቄ ቡናን፣ ጫትን፣ አናናስንና ሸንኮራ አገዳን አይመለከትም::

ጥያቄ 5:- <u>ፍሬ /ምርት ለመስጠት የደረሰ ቋሚ ሰብል እግር ብዛት</u>

ባለይዞታው እያንዳንዱን ቋሚ ሰብል አስመልክቶ በጥያቄ 4 ካስመዘገበው ጠቅላላ የእግር ብዛት መካከል በምርት ዘመኑ ምርት ሰጥተዋል፣ ወይም ሊሰጡ ይችላሉ የሚላቸውን እግሮች በመቁጠር ብዛታቸው ይሞላል።

ጥያቄ 6:- <u>የመስኖ ዘዴ ተጠቅመዋል? (አዎን = 1 የለም = 2)</u>

ባለይዞታው ባስመዘገበው በእያንዳንዱ ማሣ ላይ ያለውን ቋሚ ሰብል ለማምረትም ሆነ ምርትን ለማሻሻል የመስኖ ዘዴ መጠቀም አለመጠቀሙ ተጠይቆ ተጠቅሞ ከሆነ ኮድ «1» ያልተጠቀመ ከሆነ ደግሞ ኮድ «2» ይሞላል።

ጥያቄ 7:- <u>የዘር /የችግኝ/ ዓይነት (ምርጥ ዘር = 1 ምርጥ ዘር ያልሆነ = 2)</u>

ባለይዞታው ላስመዘገበው ለእያንዳንዱ ቋሚ ሰብል የተጠቀመው የዘር /ችግኝ/ ዓይነት ተጠይቆ ምርጥ ዘር ከሆነ ኮድ «1» ፣ ምርጥ ዘር ካልሆነ ደግሞ ኮድ «2» ይሞላል።

ጥያቄ 8:- <u>የሰብል ብልሽት ደርሷል ወይ? (አዎን = 1 የለም = 2)</u>

ባለይዞታው ያስመዘገበውን እያንዳንዱን የቋሚ ሰብል ማሣ አስመልክቶ የሰብል መበላሸት ደርሶ ከሆነ ኮድ «1» ያልደረሰ ከሆነ ደግሞ ኮድ «2» ይሞላል።

ጥያቄ 9:- <u>የሰብል ብልሽት ደርሶ ከሆነ ለብልሽቱ አንድ ዋና ምክንያት</u>

ይህ ጥያቄ የሚጠየቀው በጥያቄ 8 በቋሚ ሰብሉ ላይ ብልሽት አለ ተብሎ ኮድ «1» የተሞላ እንደሆነ ብቻ ነው። ስለዚህ የሰብል መበላሸት ካለ በዚህ ዓምድ ለሰብሉ መበላሸት አንድ ዋና ምክንያት ብቻ ባለይዞታው ተጠይቆ መገለጽ አለበት። ለሰብል መበላሸት ዝርዝር ምክንያቶችን በገጽ 19 ይመልከቱ።

ጥያቄ 10:- <u>የብልሽት መጠን በመቶኛ</u>

በጥያቄ 9 በተገለፀው ምክንያት በቋሚ ሰብሉ ላይ ጉዳት የደረሰ ከሆነ በማሣው ላይ ጉዳት የደረሰበትን ሰብል መጠን በመቶኛ በመጠየቅ ይሞላል።

ጥያቄ 11:- ብልሽቱን ለመከላከል /ለጥንቃቄ/ የተወሰደ እርምጃ (አለ = 1 የለም = 2)

ባለይዞታው የደረሰበትን የቋሚ ሰብል ብልሽት ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ ወይም ለጥንቃቄ አስቀድሞ የወሰደው እርምጃ ካለ ኮድ «1»፣ ከሌለ ደግሞ ኮድ «2» ይሞላል::

ጥያቄ 12:- የተወሰደው እርምጃ ዓይነት (ኬሚካል= 1 ኬሚካል ያልሆነ = 2 ሁለቱም = 3)

ባለይዞታው በቋሚ ሰብሉ ላይ የደረሰውን ብልሽት ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ ወይም አስቀድሞ ለመከላከል የተጠቀመው መድኃኒት ኬሚካል ከሆነ ኮድ «1» ፣ ኬሚካል ካልሆነ ኮድ «2»:: ሁለቱም ከሆነ ኮድ «3» ይሞላል::

ጥያቄ 13:- ጥያቄ 12 ኮድ «1» ወይም ኮድ «3» ከተሞላ (ኬሚካል ከተጠቀሙ ዓይነቱ)

ባለይዞታው በጥያቄ 12 የተጠቀመው መድኃኒት ኬሚካል ከሆነ ማለትም ኮድ «1» ወይም «3» ከተሞላ ለእያንዳንዱ ማሣ ምን ዓይነት ኬሚካል እንደተጠቀመ በመጠየቅ ፀረ-ተባይ ከሆነ ኮድ «1»፣ ፀረ-አረም ከሆነ ኮድ «2»፣ ፀረ-በሽታ ከሆነ ኮድ «3» ፀረ-ተባይ እና ፀረ-አረም ከሆነ ኮድ «4» ፣ ፀረ-ተባይና ፀረ-በሽታ ከሆነ ኮድ «5» ፣ ፀረ-አረምና ፀረ-በሽታ ከሆነ ኮድ «6» ፣ ሁሉንም ዓይነት ከሆነ ኮድ «7» ይሞላል::

ጥያቄ 14:- የተፈጥሮ /የኬሚካል ማዳበሪያ ተጠቅመዋል? (አዎ = 1 የለም = 2)

ባለይዞታው በማሣው ላይ ያለውን ቋሚ ሰብል ምርት ለማሻሻል የተፈጥሮ ወይም ኬሚካል ማዳበሪያ ተጠቅሞ ከሆነ ኮድ «1» ፣ ያልተጠቀመ ከሆነ ደግሞ ኮድ «2» ይሞላል::

ጥያቄ 15:- ከተጠቀሙ የማዳበሪያው ዓይነት(የተፈጥሮ = 1 ኬሚካል = 2 ሁለቱም = 3)

ባለይዞታው በጥያቄ 14 ማዳበሪያ ተጠቅሞ ኮድ «1» ተሞልቶ ከሆነ በዚህ ዓምድ የማዳበሪያው ዓይነት ይጠየቃል:: ጥቅም ላይ የዋለው የማዳበሪያ ዓይነት የተፈጥሮ ከሆነ ኮድ «1»፣ ኬሚካል ከሆነ ኮድ «2» ፣ ሁለቱም ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» ይሞላል::

ጥያቄ 16:- ኬሚካል ማዳበሪያ ካልተጠቀሙ አንድ ዋና ምክንያት (በጥያቄ 14 ኮድ «2» ወይም በጥያቄ 15 ኮድ «1» ከተሞላ)

ባለይዞታው ማዳበሪያ መጠቀም አለመጠቀሙ በጥያቄ 14 ላይ ተጠይቆ ኮድ «2» ከተሞላ ወይም ተጠቅሞ በጥያቄ 15 ኮድ «1» ከተሞላ ኬሚካል ማዳበሪያ ያልተጠቀመበት አንድ ምክንያት በተሰጠው ክፍት ቦታ በፊደል ይሰፍራል ኮዱም ይሞላል። የምክንያቶቹ ዝርዝር በገጽ 37 የቀረበ ሲሆን እነዚህን በመጠቀም ትክክለኛው ምክንያትና ኮድ በተሰጠው ቦታ ይሰፍራል።

ማስታወሻ

ይህ ጥያቄ (ጥያቄ 16) የሚጠየቀው ለእያንዳንዱ ማሳ ስለሆነ ባለይዞታው የሚሰጠው አንድ ዋና ምክንያት ሆኖ ይኸው ምክንያት ለሁሉም ማሳዎች ይመዘገባል እንጂ ለተለያዩ ማሳዎች የተለያየ ምክንያት መመዝገብ የለበትም።

ጥያቄ 17:- ኬሚካል ማዳበሪያ ከተጠቀሙ (በጥያቄ 15 ኮድ «2» ወይም «3» ከተሞላ)

ጥያቄ 17.1- ዓይነት

ባለይዞታው የተጠቀመው የኬሚካል ማዳበሪያ ዓይነት ተጠይቆ ዩሪያ ከሆነ ኮድ «1» ፣ ዳፕ ከሆነ ኮድ «2» ፣ ሁለቱም ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» ይሞላል።

ጥያቄ 17.2- መጠን በኪ.ግራም

በጥያቄ 17.1 ዓይነቱ የተገለጸው ማዳበሪያ መጠኑ ምን ያህል እንደሆነ ባለይዞታው ተጠይቆ በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ በኪሎ ግራም ይሞላል። ባለይዞታው መጠኑን የማያውቅ ከሆነ በዚህ መመሪያ በገጽ 38 እና 39 የተሰጠውን የአሠራር ዘዴ መጠቀም ያስፈልጋል።

ጥያቄ 18- የተፈጥሮ ማዳበሪያ ከተጠቀሙ (በጥያቄ 15 ኮድ «1» ወይም «3» ከተሞላ) ዓይነት:-

ባለይዞታው በጥያቄ 15 የተፈጥሮ ማዳበሪያ መጠቀሙ ተገልጾ ኮድ «1» ወይም «3» ከተሞላ በዚህ ጥያቄ ደግሞ የተጠቀመው የተፈጥሮ ማዳበሪያ ዓይነት ተጠይቆ የከብቶች ፍግ ከሆነ ኮድ «1»፣ የተለያየ ብስባሽ ከሆነ ኮድ «2»፣ የሁለቱም ዓይነት ከሆነ ኮድ «3» ከእነዚህ ውጪ (ሌላ) ከሆነ ደግሞ ዓይነቱ በተሰጠው ቦታ ተገልጾ ኮድ «4» ይሞላል።

## የቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሐ - በድብልቅ ሰብሎች የተያዙ ማሣዎች ዝርዝርና

## የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ በመኸር ወቅት አሞላል

በዚህ ቅጽ የባለይዞታው የሆኑ በጊዜያዊና ጊዜያዊ፣ በጊዜያዊና ቋሚ፣ እንዲሁም በቋሚና ቋሚ ድብልቅ ሰብሎች ብቻ የተያዙ ማሣዎች በሙሉ ይመዘገባሉ።

ክፍል 1. የአካባቢ መለያ

ዓምድ 1 - ክልል

ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 2 - ዞን

ጥናቱ የሚካሄድበት ዞን ስም ወይንም ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 3 - ወረዳ

ጥናቱ የሚካሄድበት ወረዳ ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 4 - ገበሬ ማህበር

ጥናቱ የሚካሄድበት የገበሬ ማህበር ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 5 - ቆጠራ ቦታ

ጥናቱ የሚካሄድበት ቆጠራ ቦታ ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 6 - የቤተሰብ መለያ ቁጥር

የተመረጠው ቤተሰብ መለያ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/1 ክፍል 2 ዓምድ 1 በመውሰድ ይሞላል።

ዓምድ 7 - የባለይዞታው መለያ ቁጥር

በቆጠራ ቦታው በተመረጠው ቤተሰብ ውስጥ ለሚገኙ የግል ባለይዞታዎች የተሰጠውን መለያ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/1 ክፍል 2 ዓምድ 3 በማወራረስ ይሞላል።

ዓምድ 8 - የባለይዞታው ስም

የባለይዞታው ስም ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/1 ክፍል 2 ዓምድ 4 በማወራረስ ይሞላል።

ዓምድ 9 - ዕድሜ

የባለይዞታው ዕድሜ ተጠይቆ በሙሉ ዓመት በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 10 - ፆታ (ወንድ = 1 ሴት = 2)

የባለይዞታው ፆታ ወንድ ከሆነ ኮድ «1» ሴት ከሆነች ኮድ «2» በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 11 - የትምህርት ሁኔታ (የፈጸሙት ከፍተኛ ክፍል)

በዚህ ዓምድ የባለይዞታው የትምህርት ሁኔታ /የፈፀሙት ከፍተኛ ክፍል/ ተጠይቆ ትክክለኛው ኮድ ተመርጦ ይሞላል።

ዓምድ 12 - የባለይዞታው የቤተሰብ አባላት ብዛት

የባለይዞታው የቤተሰብ አባላት ብዛት ተጠይቆ በዚህ ዓምድ ውስጥ ይሞላል። በተጨማሪም በተመረጠው ቤተሰብ ወስጥ ከአንድ በላይ ባለይዞታ ካለ የቤተሰብ አባላት ብዛት በሚጠየቅበት ጊዜ ብዛት ለእያንዳንዱ ባለይዞታ ተደጋግሞ ይሞላል።

ዓምድ 13 - የግብርናው ዓይነት /ሰብል = 1 ከብት = 2 ሁለቱም= 3/

በዓምድ 7 መለያ ቁጥሩ የተመዘገበው እያንዳንዱ ባለይዞታ የተሰማራበት የግብርና ዓይነት ተጠይቆ ሰብል ማምረት ብቻ ከሆነ ኮድ «1» ከብት ማርባት /ማደለብ/ ብቻ ከሆነ ኮድ «2» ሁለቱም ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ክፍል 2. በድብልቅ ሰብሎች (አትክልትና ሥራሥርን ጨምሮ) የተያዙ ማሣዎች ዝርዝርና የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ

ይህ ክፍል የሚያገለግለው ባለይዞታው በ1996 ዓ.ም በመኸር ወቅት ያሉትን በድብልቅ ሰብሎች የተያዙ ማሣዎች ዝርዝርና የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ለመመዝገብ ነው። በዚህ ክፍል 2 በድብልቅ ሰብል የተያዙ ማሣዎችን መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ቦታ (ዓምድ 3 ና 4) ተሰጥቷል። ከሁለት በላይ በድብልቅ ሰብል የተያዙ ማሣዎች ሲያጋጥም የቅጹን ጀርባ መጠቀም ይቻላል ከአራት በላይ በድብልቅ የተያዙ ማሣዎች ካጋጠሙ ግን ተጨማሪ ቅጽ መጠቀም ያስፈልጋል።

ዓምድ 1 - ተራ ቁጥር

ተራ ቁጥር ከ«01» በመጀመር በቅደም ተከተል ተሞልቷል።

ዓምድ 3-4 - የፓርስል ቁጥር ፣ የማሣ ቁጥርና የሰብል ስም

የፓርስል ቁጥር

መረጃ የሚሰበሰብላቸው በድብልቅ ሰብል የተያዙ ፓርስሎች በሙሉ የፓርስል ቁጥራቸው ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሀ፣ 96/3ለ፣ እንዲሁም 96/3መ የተሰጠውን በማገናዘብና ተከታታይነቱን በመጠበቅ ይሰጣል።

የማሣ ቁጥር

መረጃ የሚሰበሰብላቸው በድብልቅ ሰብል የተያዙ ማሣዎች በሙሉ የማሣ ቁጥራቸው ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሀ - 96/3መ የተሰጠውን መሠረት በማድረግና የማሣ ፍቺን በጠበቀ መልኩ ተከታታይ ቁጥር በመስጠት ይሞላል።

የሰብል ስም

የባለይዞታው በሆኑ በድብልቅ ሰብል በተያዙ ማሣዎች ላይ የሚገኙ ድብልቅ ሰብሎች ስማቸው ለየብቻ ተዘርዝሮ በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ይመዘገባል:: በድብልቅ ሰብሎች ለተያዘ አንድ ማሣ በማሣው ላይ ለ«3» የድብልቅ ሰብሎች ስም ብቻ መመዝገቢያ የሚሆን ቦታ ተዘጋጅቷል:: ሆኖም ማሣው የያዘው ከ«3» በላይ የድብልቅ ሰብሎችን ከሆነ እያንዳንዱ ድብልቅ ሰብል ከጠቅላላው የማሣ ስፋት ያለውን ድርሻ በማወዳደር ከፍተኛውን የማሣ ድርሻ የያዙትን «3» ድብልቅ ሰብሎች ብቻ በመውሰድ በዚህ ዓምድ በተሰጡት ባዶ ቦታዎች የ«3»ቱ ድብልቅ ሰብሎች ስም በዝርዝር ይመዘገባል:: በእያንዳንዱ ሰብል አቅጣጫ ለኮድ የተተወው ቦታ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም:: በዚህ ቅጽ ሁለት የድብልቅ ማሣዎች መረጃን ሊያስሞላ የሚችል ቦታ (ዓምድ 3 እና ዓምድ 4) ተሰጥቷል:: ከሁለት በላይ በድብልቅ ሰብል የተያዙ ማሣዎች ሲያጋጥም ጀርባውን መጠቀም ያስፈልጋል:: ከአራት በላይ የድብልቅ ማሣዎች ሲያጋጥም ግን ተጨማሪ ቅጽ መጠቀም ይቻላል::

ዓምድ 2 - ለባለይዞታው የሚቀርቡ ጥያቄዎች

ጥያቄ 1:- የይዞታው ዓይነት:- ባለይዞታው ያስመዘገበው እያንዳንዱ ማሣ ተጠይቆ ይዞታው የራሱ ከሆነ ኮድ «1» ፤ በኪራይ ወይም በኮንትራት የተያዘ ከሆነ ኮድ «2»፤ ከነዚህ ከሁለቱ ውጭ የተገኘ ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል::

ጥያቄ 2:- ድብልቅ ሰብሉ የያዘው ማሣ ስፋት በአካባቢ መለኪያ

በዚህ ቅጽ ላይ የተመዘገበው እያንዳንዱ በድብልቅ ሰብሎች የተያዘ ማሣ ስፋት የሚታወቅበት የአካባቢ መለኪያ ስም ተጠይቆ የመለኪያው ስምና በዚሁ መለኪያ የስፋቱ መጠን በእያንዳንዱ ማሣ አንጻር በተሰጠው ክፍት ቦታ ውስጥ ይመዘገባል::

ጥያቄ 3:- ማሣው በኤክስቴንሽን መርሀ-ግብር ታቅፏል?

(አዎ = 1 አልታቀፉም = 2)

ባለይዞታው ያስመዘገበው እያንዳንዱ በድብልቅ ሰብል የተያዘ ማሣ በኤክስቴንሽን መርሀ-ግብር መታቀፍ አለመታቀፉ ተጠይቆ ከታቀፈ ኮድ «1» ካልታቀፈ ደግሞ ኮድ «2» በተሰጠው ቦታ ይሞላል::

ጥያቄ 4:- በማሣው ላይ ያሉ ሰብሎች የያዙት ስፋት (በመቶኛ):-

እያንዳንዱን በድብልቅ ሰብሎች የተያዘ ማሣ አስመልክቶ እያንዳንዱ የሰብል ዓይነት ከጠቅላላ የማሣው ስፋት የያዘው የመሬት ስፋት ድርሻ በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ባለይዞታው ተጠይቆ ይሞላል:: ከ«3» በላይ ድብልቅ ካጋጠመ የማሣው ከፍተኛ ድርሻ ላላቸው «3» ሰብሎች ብቻ ድርሻቸው በመቶኛ ተጠይቆ ይመዘገብላቸዋል:: የቀሪዎቹም ድርሻ ለሦስቱ ዋና ዋና ሰብሎች ይከፋፈላል::

ጥያቄ 5:- የቋሚ ሰብል እግር ብዛት

በድብልቅ ሰብሉ ማሣ ላይ ያለው ቋሚ ሰብል ጠቅላላ እግሮች ብዛት ተቆጥሮ ይሞላል:: ይህ ጥያቄ ቡናን፣ ጫትን፣ አናናስንና ሸንኮራ አገዳን አይመለከትም::

ጥያቄ 6:- ፍሬ/ምርት ለመስጠት የደረሰ ቋሚ ሰብል እግር ብዛት

ባለይዞታው በጥያቄ 5 ላይ ካስመዘገበው የቋሚ ሰብሎች እግሮች ብዛት መካከል በምርት ዘመኑ ፍሬ ወይም ምርት ሰጥተዋል ወይም ሊሰጡ ይችላሉ የሚላቸው እግሮች ብዛት ተቆጥሮ ይሞላል::

ጥያቄ 7:- የመስኖ ዘዴ ተጠቅመዋል? (አዎን = 1 የለም = 2)

ባለይዞታው በእያንዳንዱ ማሳ ላይ ያሉትን ድብልቅ ሰብሎች ለማምረትም ሆነ ምርትን ለማሻሻል የመስኖ ዘዴ የተጠቀመ ከሆነ ኮድ «1»፥ ያልተጠቀመ ከሆነ ደግሞ ኮድ «2» ይሞላል::

ጥያቄ 8:- የዘር /የችግኝ/ ዓይነት (ምርጥ ዘር = 1 ምርጥ ዘር ያልሆነ = 2)

ባለይዞታው በድብልቅ ለዘራቸው /ለተከላቸው ሰብሎች ለእያንዳንዳቸው የተጠቀመው የዘር /የችግኝ/ ዓይነት ተጠይቆ ምርጥ ዘር ከሆነ ኮድ «1»፣ ምርጥ ዘር ካልተጠቀመ ደግሞ ኮድ «2» ይሞላል:: (ለቋሚ ሰብሎች ምርጥ ዘር ችግኞችን እንደሚያጠቃልል ማስታወስ ይገባል)::

ጥያቄ 9:- ምርጥ ዘር ካልሆነ መጠን በኪ.ግራም

ባለይዞታው በጥያቄ 8 ላይ ምርጥ ያልሆነ ዘር ተጠቅሚአለሁ ብሎ ኮድ «2» ከተሞላ በዚህ ጥያቄ ደግሞ የተጠቀመው የአካባቢ ዘር መጠኑ በኪሎ ግራም ተጠይቆ ይሞላል:: ጥያቄው የሚመለከተው የብርዕ፣ አገዳ፣ ጥራጥሬና ቅባት ሰብሎችን ብቻ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል::

ጥያቄ 10:- ምርጥ ዘር ከሆነ መጠን በኪሎ ግራም

በጥያቄ 8 ባለይዞታው ምርጥ ዘር መጠቀሙን ገልጾ ኮድ «1» ከተሞላ በዚህ ጥያቄ ደግሞ የተጠቀመው የምርጥ ዘር መጠን ተጠይቆ መጠኑ በኪሎ ግራም ይሞላል:: ጥያቄው የብርዕ፡ አገዳ፡ ጥራጥሬና ቅባት ሰብሎችን ብቻ ይመለከታል::

ጥያቄ 11:- ምርጥ ዘር ከሆነ ዋጋ

ባለይዞታው በጥያቄ 8 ምርጥ ዘር ተጠቅሟል ተብሎ የዘሩ መጠን በጥያቄ 10 ከተሞላ በዚህ ዓምድ የተጠቀመው ምርጥ ዘር ዋጋ ተጠይቆ በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል:: ጥያቄው ችግኝን አይመለከትም::

ጥያቄ 12:- የሰብል ብልሽት ደርሷል ወይ? (አዎን = 1 የለም = 2)

በድብልቅ የሚገኙትን እያንዳንዱን ሰብል አስመልክቶ የሰብል መበላሸት ደርሶ ከሆነ ኮድ «1» ካልደረሰ ደግሞ ኮድ «2» ባለይዞታው ተጠይቆ ይሞላል::

ጥያቄ 13:- የሰብል ብልሽት ደርሶ ከሆነ የብልሽቱ አንድ ዋና ምክንያት

በጥያቄ 12 የሰብል መበላሸት ደርሷል ተብሎ ኮድ «1» ከተሞላ ብቻ ለሰብሉ መበላሸት አንድ ዋና ምክንያት ተጠይቆ ጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ መገለጽ አለበት:: የሰብል መበላሸት ምክንያቶች ዝርዝርን በገጽ 19 ይመልከቱ:: በዚሁ ጥያቄ አቅጣጫ ለኮድ የተተወው ቦታ ለቢሮ ሥራ ብቻ የሚያገለግል ስለሆነ ምንም አይሞላበትም::

ጥያቄ 14:- የብልሽት መጠን በመቶኛ

በጥያቄ 13 በተገለፀው ምክንያት በሰብል ላይ ጉዳት የደረሰ ከሆነ በማሣው ላይ የሚገኙትን እያንዳንዱን ሰብል አስመልክቶ የደረሰው የጉዳት መጠን በመቶኛ በተሰጠው ቦታ ይገለጻል::

ጥያቄ 15:- ብልሽቱን ለመከላከል /ለጥንቃቄ/ የተወሰደ እርምጃ?

(አለ = 1 የለም = 2)

በዚህ ዓምድ ባለይዞታው የደረሰበትን የሰብል ብልሽት ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ ወይም ለጥንቃቄ አስቀድሞ የወሰደው እርምጃ ካለ ኮድ «1» ከሌለ ደግሞ ኮድ «2» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ጥያቄ 16:- የተወሰደ እርምጃ ዓይነት (ኬሚካል = 1 ኬሚካል ያልሆነ = 2 ሁለቱም = 3)

ባለይዞታው የሰብሉን ብልሽት ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ ወይም ለጥንቃቄ እርምጃ ወስዶ በጥያቄ 15 ኮድ «1» ከተሞላ የወሰደው እርምጃ ዓይነት ኬሚካል መጠቀም ከሆነ ኮድ «1» ፣ ኬሚካል ካልሆነ ኮድ «2» ሁለቱም ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» ይሞላል።

ጥያቄ 17:- ኬሚካል ከተጠቀሙ ዓይነቱ

ባለይዞታው በጥያቄ 16 የወሰደው እርምጃ ዓይነት ኬሚካል ከሆነ (በጥያቄ 16 ኮድ «1» ወይም «3» ከተሞላ) ዓይነቱ ተጠይቆ ፀረ-ተባይ ከሆነ ኮድ «1» ፣ ፀረ-አረም ከሆነ ኮድ «2» ፣ ፀረ-በሽታ ከሆነ ኮድ «3»፣ ፀረ-ተባይና ፀረ-አረም ከሆነ ኮድ «4» ፀረ-ተባይና ፀረ-በሽታ ከሆነ ኮድ «5» ፣ ፀረ-አረምና ፀረ-በሽታ ከሆነ ኮድ «6»፣ እንዲሁም ሁሉንም ዓይነት ከሆነ ደግሞ ኮድ «7» ይሞላል።

ጥያቄ 18:- የተፈጥሮ /የኬሚካል ማዳበሪያ ተጠቅመዋል?

(አዎን = 1 የለም = 2)

ባለይዞታው በድብልቅ ሰብል ከተያዘ እያንዳንዱ ማሣ ላይ የሚገኘውን ምርት ለማሻሻል የተፈጥሮም ይሁን የኬሚካል ማዳበሪያ ተጠቅሞ ከሆነ ኮድ «1» ያልተጠቀመ ከሆነ ኮድ «2» ይሞላል።

ጥያቄ 19:- ማዳበሪያ ከተጠቀሙ ዓይነቱ (የተፈጥሮ = 1 ኬሚካል = 2 ሁለቱም = 3)

በጥያቄ 18 ባለይዞታው ማዳበሪያ ተጠቅሞ ኮድ «1» ከተሞላ የማዳበሪያው ዓይነት ተጠይቆ ጥቅም ላይ የዋለው የማዳበሪያ ዓይነት የተፈጥሮ ከሆነ ኮድ «1» ኬሚካል ከሆነ ኮድ «2» ሁለቱም ዓይነት ከሆነ ኮድ «3» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

ጥያቄ 20 - ኬሚካል ማዳበሪያ ካልተጠቀሙ አንድ ዋና ምክንያት (ጥያቄ 18 ኮድ «2» ወይም ጥያቄ 19 ኮድ «1» ከተሞላ)

ባለይዞታው ማዳበሪያ መጠቀም አለመጠቀሙ በጥያቄ 18 ላይ ተጠይቆ ኮድ «2» ከተሞላ ወይም ተጠቅሞ በጥያቄ 19 ኮድ «1» ከተሞላ ኬሚካል ማዳበሪያ ያልተጠቀመበት አንድ ዋና ምክንያት ተጠይቆ በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይመዘገባል። የምክንያቶቹ ዝርዝር በገጽ 35 የቀረበ ሲሆን እነዚህን በመጠቀም ትክክለኛው ኮድ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

ማስታወሻ

ይህ ጥያቄ (ጥያቄ 20) የሚጠየቀው ለእያንዳንዱ ማሳ ስለሆነ ባለይዞታው የሚሰጠው አንድ ዋና ምክንያት ሆኖ ይኸው ምክንያት ለሁሉም ማሳዎች ይመዘገባል እንጂ ለተለያዩ ማሳዎች የተለያየ ምክንያት መመዝገብ የለበትም።

ጥያቄ 21:- ኬሚካል ማዳበሪያ ከተጠቀሙ (ጥያቄ 19 ኮድ «2» ወይም «3» ከተሞላ)

ጥያቄ 21.1:- ዓይነት

ባለይዞታው የተጠቀመው ማዳበሪያ ኬሚካል ከሆነ የተጠቀመው ማዳበሪያ ዓይነት ተጠይቆ ዩሪያ ከሆነ ኮድ «1» ዳፕ ከሆነ ኮድ «2» ሁለቱም ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

ጥያቄ 21.2:- መጠን በኪሎ ግራም

በጥያቄ 21.1 የተገለፀውን የማዳበሪያ ዓይነት መጠኑ ከባለይዞታው ተጠይቆ በኪሎ ግራም ይሞላል። ባለይዞታው መጠኑን የማያውቀው ከሆነ በገጽ 38 እና 39 የተሰጠውን የአሠራር ዘዴ መከተል ያስፈልጋል።

ጥያቄ 22:- የተፈጥሮ ማዳበሪያ ከተጠቀሙ (በጥያቄ 19 ኮድ «1» ወይም «3» ከተሞላ) ዓይነት

ባለይዞታው በጥያቄ 19 የተፈጥሮ ማዳበሪያ መጠቀሙን ገልጾ ኮድ «1» ወይም «3» ከተሞላ የተጠቀመው የማዳበሪያ ዓይነት ተጠይቆ የከብቶች ፍግ ከሆነ ኮድ «1» የተለያየ ብስባሽ ከሆነ ኮድ «2» ሁለቱንም ዓይነት ከሆነ ኮድ «3» ከእነዚህ ውጭ (ሌላ) ከሆነ ደግሞ ዓይነቱ ተገልጾ ኮድ «4» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

## የቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3መ - ሌላ የመሬት አጠቃቀም ዝርዝር (በማንኛውም ሰብል ያልተያዘ) በመኸር ወቅት አሞላል

ይህ ቅጽ በተመረጠው ባለይዞታ ቁጥጥር የሚገኙ ሌሎች የመሬት አጠቃቀሞች (እዳሪ መሬት፣ የግጦሽ መሬት፣ በደን የተያዙ በቤት የተያዙ ቦታዎች ... ወዘተ) የሚዘረዘሩበት ነው።

ክፍል 1. የአካባቢ መለያ

ዓምድ 1 - ክልል

ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 2 - ዞን

ጥናቱ የሚካሄድበት ዞን ስም ወይንም ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 3 - ወረዳ

ጥናቱ የሚካሄድበት ወረዳ ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 4 - ገበሬ ማህበር

ጥናቱ የሚካሄድበት የገበሬ ማህበር ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 5 - ቆጠራ ቦታ

ጥናቱ የሚካሄድበት ቆጠራ ቦታ ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 6 - የቤተሰብ መለያ ቁጥር

የተመረጠው ቤተሰብ መለያ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/1 ክፍል 2 ዓምድ 1 በመውሰድ ይሞላል።

ዓምድ 7 - የባለይዞታው መለያ ቁጥር

በቆጠራ ቦታው ከተመረጠው ቤተሰብ ውስጥ ለሚገኙ የግል ባለይዞታዎች የተሰጠውን መለያ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/1 ክፍል 2 ዓምድ 3 በማወራረስ ይሞላል።

ዓምድ 8 - የባለይዞታው ስም

የባለይዞታው ስም ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/1 ክፍል 2 ዓምድ 4 በማወራረስ ይሞላል።

ዓምድ 9 - ዕድሜ

የባለይዞታው ዕድሜ ተጠይቆ በሙሉ ዓመት በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 10 - ፆታ (ወንድ = 1 ሴት = 2)

የባለይዞታው ፆታ ወንድ ከሆነ ኮድ «1» ሴት ከሆነች ኮድ «2» በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 11 - የትምህርት ሁኔታ (የፈጸሙት ከፍተኛ ክፍል)

በዚህ ዓምድ የባለይዞታው የትምህርት ሁኔታ /የፈፀሙት ከፍተኛ ክፍል/ ተጠይቆ ትክክለኛው ኮድ ተመርጦ ይሞላል:: ለበለጠ ማብራሪያ ገጽ 31 እና 32 ይመልከቱ::

ዓምድ 12 - የባለይዞታው የቤተሰብ አባላት ብዛት

የባለይዞታው የቤተሰብ አባላት ብዛት ተጠይቆ በዚህ ዓምድ ውስጥ ይሞላል:: በተጨማሪም በተመረጠው ቤተሰብ ወስጥ ከአንድ በላይ ባለይዞታ ካለ የቤተሰብ አባላት ብዛት በሚጠየቅበት ጊዜ ብዛት ለእያንዳንድ ባለይዞታ ተደጋግሞ ይሞላል::

ዓምድ 13 - የግብርናው ዓይነት /ሰብል = 1 ከብት = 2 ሁለቱም= 3/

በዓምድ 7 መለያ ቁጥሩ የተመዘገበው እያንዳንዱ ባለይዞታ የተሰማራበት የግብርና ዓይነት ተጠይቆ ሰብል ማምረት ብቻ ከሆነ ኮድ «1» ከብት ማርባት /ማደለብ/ ብቻ ከሆነ ኮድ «2» ሁለቱም ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ክፍል 2. ሌላ የመሬት አጠቃቀም ዓይነትና ስፋት

ዓምድ 1 - ተራ ቁጥር

ተራ ቁጥር ከ01 በመጀመር ተሰጥቷል::

ዓምድ 2-6- የፓርስል ቁጥር፣ ማሣ ቁጥርና የመሬት አጠቃቀሙ ዓይነት/ስም

በሌላ የመሬት አጠቃቀም የተያዘ ቦታ የፓርስልና የማሣ ቁጥሮች በቅጽ ግ.ና.ፕ 96/3ሀ፣ 96/3ለና 96/3ሐ ከተመዘገቡት ማሳዎች ጋር በማገናዘብና ተከታታይነታቸውን በመጠበቅ በዓምድ 2ና በዓምድ 3 ይመዘገባሉ:: በባለይዞታው ሥር የሚገኝ እያንዳንዱ የመሬት አጠቃቀም ዓይነት/ስም በዓምድ 4 ሲመዘገብ ዓምድ 5 ለኮድ የተተወው ቦታ ምንም አይሞላበትም::

ዓምድ 6-7 - የይዞታ ዓይነት

ባለይዞታው በዓምድ 4 ያስመዘገበው የመሬት አጠቃቀም የይዞታው ሁኔታ ተጠይቆ በዓምድ 6 ይመዘገብና የግል ከሆነ ኮድ «1» በኪራይ ወይም በኮንትራት የተያዘ ከሆነ ኮድ «2» ከነዚህ ከሁለቱ ውጭ ከሆነ ደግሞ ሌላ የሚለው ከተገለጸ በኋላ ኮድ «3» በዓምድ 7 ይሞላል::

ዓምድ 8-10 - ስፋት በአካባቢ መለኪያ

በዓምድ 4 የተመዘገበውና በሌላ የመሬት አጠቃቀም የተያዘ መሬት ስፋት በአካባቢ መለኪያ ተጠይቆ የአካባቢው መለኪያ ስም በዓምድ 8 ይመዘገብና የመሬቱ ስፋት ደግሞ በዓምድ 10 ይሞላል:: ዓምድ 9 ለኮድ የተተወው ቦታ ምንም አይሞላበትም::

ክፍል 3. ለባለይዞታው የሚቀርቡ ሌሎች የእርሻ ሥራ ተዛማጅ ጥያቄዎች

በዚህ ክፍል ለባለይዞታው የሚቀርቡ የተለያዩ ጥያቄዎች ከተራ ቁጥር 1-8 ተዘርዝረዋል:: መረጃ ሰብሳቢው ጥያቄዎቹን በትክክል ተገንዝቦ ለባለይዞታው በማቅረብ ባለይዞታው የሚሰጠውን መልስ በየጥያቄዎቹ አቅጣጫ በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ አስፈላጊውን መረጃ በጥንቃቄ መመዝገብ አለበት::

ጥያቄ 1:- ባለዎት የመሬት ይዞታ ላይ አዝርዕትን አፈራርቀው ይዘራሉን?

ባለይዞታው በመሬቱ ላይ በሰብል ዘመኑም ሆነ ባለፉት የሰብል ዘመናት አዝርዕትን በማፈራረቅ ዘርቶ ከሆነ በመጠየቅ የሚገኘው መልስ አዎ ከሆነ ኮድ «1» የለም ከሆነ ኮድ «2» ይሞላል:: አዝርዕት ማፈራረቅ ሲባል ባለይዞታው አምና ገብስ የዘራበትን መሬት ዘንድሮ ስንዴ ወይም ጤፍ ...ወዘተ ቢዘራበት አዝርዕትን በማፈራረቅ ይዘራል ማለት ነው:: እንዲሁም በአንድ የሰብል ዘመን ሁለት ጊዜ ምርት የመሰብሰብ ልምድ ባላቸው አካባቢዎች በአንድ ማሣ መጀመሪያ ጤፍ ዘርቶ ከሰበሰበ በኋላ በሁለተኛው ጊዜ ሽምብራ ቢዘራበት አዝርዕትን በማፈራረቅ እንደዘራ ይቆጠራል::

ጥያቄ 2:- በመስኖ ዘዴ የሚጠቀሙ ከሆነ ለመስኖ የሚሆነውን ውሃ ከየት ያገኛሉ?

ባለይዞታው በቆጠራው ዓመት በመስኖ ዘዴ የሚጠቀም ከሆነ ተጠይቆ አዎን የሚል መልስ ከሰጠ ለመስኖ የሚሆነውን ውሃ የሚያገኘው ከወንዝ ከሆነ ኮድ «1» ከሐይቅ ከሆነ ኮድ «2» ከኩሬ ከሆነ ኮድ «3» ከላይ ከተዘረዘሩት ውጭ ከሆነ ኮድ «4» በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል:: መስኖ ካልተጠቀመ ግን ኮድ «5» ይሞላል::

ጥያቄ 3:- የአፈር መታጠብን ለመከላከል በአብዛኛው በምን ዓይነት ዘዴ ይጠቀማሉ?

ባለይዞታው በጎርፍም ሆነ በሌላ ምክንያት በማሣው ላይ የሚደርሰውን የአፈር መሸርሸርን ለመከላከል በአብዛኛው ምን ዓይነት የመከላከል ዘዴ እንደሚጠቀም ተጠይቆ የሚሰጠው መልስ:- እርከን በመሥራት ከሆነ ኮድ «1» ክትር በመሥራት ከሆነ ኮድ «2» ዛፍ በመትከል /ደን በማልበስ/ ከሆነ ኮድ «3» አግድም በማረስ ከሆነ ኮድ «4» ከላይ ከተዘረዘሩት ውጭ ከሆነ ኮድ «5» ከተሞላ በኋላ የመከላከያ ዘዴው ፊት ለፊት ከሚገኘው ባዶ ቦታ ይመዘገባል::

ባለይዞታው ምንም ዓይነት የአፈር መሸርሸር መከላከያ ዘዴ ካልተጠቀመ ኮድ «6» ለኮድ መዓፊያ በተዘጋጀው ቦታ ይሞላል፡፡

ጥያቄ 4፡- በኤክስቴንሽን ታቅፈው ያውቃሉ?

በአሁኑ ወቅት ከእርሻ ሥራ ጥሩ ምርት የሚያገኙበትን ሁኔታ ለመፍጠር መንግስታዊ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑና ዕርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ገበሬዎች በኤክስቴንሽን እንዲታቀፉ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በወረዳ ደረጃ በተቋቋሙ የግብርና ጽ/ቤቶች የተመደቡ የልማት ሠራተኞች በአካባቢው የኤክስቴሽን ሥራ እየሠሩ ነው፡፡ እንዲሁም ስሳካዋ ግሎባል 2000 እና ሌሎች የዕርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ገበሬዎች በኤክስቴንሽን እንዲታቀፉ እያደረጉ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ባለይዞታው በቆጠራው ወቅትም ሆነ ቀደም ሲል በኤክስቴንሽን ታቅፎ ያውቅ እንደሆን ተጠይቆ የሚሰጠው መልስ አዎን ከሆነ ኮድ «1» የለም ከሆነ ኮድ «2» ለኮድ መዓፊያ በተዘጋጀው ቦታ ይሞላል፡፡

ጥያቄ 5፡- በኤክስቴንሽን ካልታቀፉ ምክንያት

በጥያቄ 4 የለም ተብሎ ኮድ «2» ተሞልቶ ከሆነ ባለይዞታው በኤክስቴሽን ያልታቀፉበት ምክንያት ተጠይቆ የሚገኘው መልስ (ምክንያት) ከፊት ለፊት በተዘጋጀው ቦታ ይመዘገባል፡፡

ዋና ዋና ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ጥቅሙን ካለማወቅ
2. የገንዘብ ዕጥረት
3. ውጤታማነቱ አጠራጣሪ ስለሆነ
4. ፕሮግራሙ በአካባቢው ስለሌለ
5. በቂ የእርሻ መሬት ስለሌለ
6. ሌላ /ይገለጽ/

ጥያቄ 6፡- የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ነዎት?

ባለይዞታው በጥናቱ ዓመት የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን አለመሆኑ ተጠይቆ ተጠቃሚ ከሆነ ኮድ «1» ካልሆነ ደግሞ ኮድ «2» በተሰጠው ቦታ ይመዘገባል

ጥያቄ 7:- የምክር አገልግሎት ተጠቃሚ ነዎት?

ባለይዞታው በጥናቱ ዓመት የምክር አገልግሎት ተጠቃሚ ከሆነ ኮድ «1» ካልሆነ ደግሞ ኮድ «2» በተሰጠው ቦታ ይመዘገባል::

ጥያቄ 8:- የኬሚካል ማዳበሪያ በአብዛኛው ከየት ይገዛሉ?

ባለይዞታው ኬሚካል(የኢንዱስትሪ ውጤት) የሆነ ማዳበሪያ በአብዛኛው ከየት እንደሚገዛ ተጠይቆ ከመንግሥት ድርጅቶች ከሆነ ኮድ «1» ከግል ድርጅት ከሆነ ኮድ «2» ከግል ነጋዴዎች ከሆነ ኮድ «3» ከእነዚህ ውጭ ሌላ ከሆነ የተገዛበትን በመግለጽ ኮድ «4» በተሰጠው ቦታ ይሞላል:: ባለይዞታው አልገዛሁም ካለ ደግሞ ኮድ «5» ይሞላል::

በጊዜያዊ፡ ቋሚና ድብልቅ ሰብሎች የተያዙ ማሣዎች የፓርስልና፡ ማሣ ቁጥር አሰጣጥና አመዘጋገብ ምሣሌ

አንድ ለዚህ ቆጠራ የተመረጠ ባለይዞታ ዙሪያውን ከሌሎች ባለይዞታዎች ይዞታ ጋር ከሚዋሰን ቦታ ላይ በበቆሎ፣ ሽንኩርት፣ ጤፍ፣ በቡናና ማሽላ ድብልቅ የተያዙ አራት ማሣዎችና የራሱ ቤት ሲኖሩት አንድ ትልቅ አውራ ጎዳናን ተሻግሮ ደግሞ በኩል አራሽ የያዛቸው አንድ ቲማቲም፣ አንድ የብርቱካን፣ አንድ ጌሾና ጫት ድብልቅ የያዙ ኩታ ገጠም ማሣዎች፣ አንድ እዳሪ መሬት እና አንድ የበቆሎ ማሣ አሉት እንዲሁም በአንድ ዙሪያውን በመንግሥት ደን ከሚዋሰን ይዞታው ላይ ደግሞ በገብስና ስንዴ ድብልቅ የተያዘ ማሣ በጤፍ የተያዘ አንድ ማሣ፣ በጫት የተያዘ አንድ ማሣ፣ በጎመን የተያዘ አንድ ማሣ በቃሪያ የተያዘ አንድ ማሣ እንዲሁም ከቤቱ አካባቢ እራቅ ብሎ አንድ የበቆሎና የማሽላ ድብልቅ የያዘ ማሣ ቢኖረውና እነዚህንም ለመረጃ ሰብሳቢው በመስክ ተዘዋውሮ ቢያሳየው፣

መረጃ ሰብሳቢውም ይዞታውን ተዘዋውሮ ከተመለከተ በኋላ ለጠቅላላ ይዞታው እንደሚከተለው የፓርስልና ማሣ ቁጥር በመስጠት በቅጽ 96/3ሀ፣ 96/3ለ፣ 96/3ሐ እና 96/3መ ላይ ምዝገባውን ያከናውናል።

በመጀመሪያ ለተመለከተው ይዞታ 01 የፓርስል ቁጥር በሁለተኛ ደረጃ ለተመለከተው አውራ ጎዳናውን ተሻግሮ ለሚገኘው 02 የፓርስል ቁጥር፣ በመንግሥት ደን ለተከበበው ይዞታ 03 የፓርስል ቁጥር እንዲሁም ከቤቱ እራቅ ብሎ ለሚገኘው ይዞታ 04 የፓርስል ቁጥር በመስጠት በአራቱ ፓርስሎች ውስጥ ለሚገኙ ማሣዎች እንደሚከተለው ቁጥሮች ይሰጣል።

በ01 ፓርስል ላይ ለሚገኘው የበቆሎ ማሣ 01 የማሣ ቁጥር በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሀ ላይ ዓምድ 3

በ01 ፓርስል ላይ ለሚገኘው የሽንኩርት ማሣ 02 የማሣ ቁጥር በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሀ ላይ ዓምድ 4

በ01 ፓርስል ላይ ለሚገኘው የጤፍ ማሣ 03 የማሣ ቁጥር በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሀ ላይ ዓምድ 5

በ01 ፓርስል ላይ ለሚገኘው የቡናና ማሽላ ድብልቅ ማሣ 04 የማሣ ቁጥር በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሐ ላይ ዓምድ 3

በ01 በፓርስል ላይ ለሚገኘው የባለይዞታው ቤት ለሚገኝበት ቦታ 05 የማሣ ቁጥር በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3መ ላይ ክፍል 2 ከዓምድ 2-10

በ02 ፓርስል ላይ ለሚገኘው የቲማቲም ማሣ 01 የማሣ ቁጥር በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሀ ላይ ዓምድ 6

በ02 ፓርስል ላይ ለሚገኘው የብርቱካን ማሣ 02 የማሣ ቁጥር በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ለ ላይ ዓምድ 3

በ02 ፓርስል ላይ ለሚገኘው የጌሾና ጫት ድብልቅ ማሳ 03 የማሳ ቁጥር በቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/3ሐ ዓምድ 4

በ02 ፓርስል ላይ ለሚገኘው የእዳሪ መሬት 03 የማሣ ቁጥር በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3መ ላይ ክፍል 2 ከዓምድ 2-10

በ02 ፓርስል ላይ ለሚገኘው የበቆሎ ማሣ 04 የማሣ ቁጥር በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሀ ላይ ዓምድ 7

በ03 ፓርስል ላይ ለሚገኘው የገብስና ስንዴ ድብልቅ ማሣ 01 የማሣ ቁጥር በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሐ ላይ ዓምድ 5

በ03 ፓርስል ላይ ለሚገኘው የጤፍ ማሣ 02 የማሣ ቁጥር በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሀ ላይ ዓምድ 8

በ03 ፓርስል ላይ ለሚገኘው የጫት ማሣ 03 የማሣ ቁጥር በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ለ ላይ ዓምድ 4

በ03 ፓርስል ላይ ለሚገኘው የጎመን ማሣ 04ና ለቃሪያ ማሣ 05 በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሀ ላይ ዓምድ 9ና 10

በ04 ፓርስል ላይ ለሚገኘው የበቆሎና ማሽላ ድብልቅ ማሣ 01 የማሣ ቁጥር በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሐ ላይ ዓምድ 6 በፓርስልና ማሳ ቁጥሮች መጻፊያ በተሰጡት ቦታዎች ላይ መስፈር ይኖርበታል።

ከላይ የተዘረዘሩት ፓርስሎችና ማሣዎች በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሀ፣ 96/3ለ፣ 96/3ሐና 96/3መ እንዴት እንደሚመዘገቡ በሚቀጥሉት ገጾች ላይ የቀረቡ ስለሆነ በሚገባ ማጤን ያስፈልጋል።

<u>*ማሳሰቢያ፡-*</u> *መረጃ ሰብሳቢው የነዚህን የተለያዩ ሰብሎች የአጨዳ ውጤት በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/6 ላይ በሚመዘገብበት ጊዜ የፓርስልና የማሣ ቁጥሮችን እንዳይምታቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት።*

## የቅጽ ግ.ና.ፐ 96/4 - የማሣዎችና ሌላ የመሬት አጠቃቀም የስፋት ልኪ ውጤት በመኸር ወቅት አሞላል

ይህ ቅጽ የማሣዎችና ሌላ የመሬት አጠቃቀም የስፋት ልኪ ውጤት የሚሰፍርበት ሲሆን በቆጠራ ቦታው በተመረጡ ቤተሰቦች ውስጥ ለሚገኙ ባለይዞታዎች በሰብል (ጊዜያዊ፡ ቋሚና ድብልቅ) እንዲሁም በሌላ የመሬት አጠቃቀም (ግጦሽ፡ እዳሪ፡ ቤት፡ ጎተራ፡ አውድማ ... ወዘተ) በተያዙና በቅጽ ግ.ና.ፐ 96/3ሀ፡ 96/3ለ፡ 96/3ሐ ና 96/3መ ለተዘረዘሩት በሙሉ ይሞላል።

ክፍል 1. የአካባቢ መለያ

ዓምድ 1 - ክልል

ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 2 - ዞን

ጥናቱ የሚካሄድበት ዞን ስም ወይም ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 3 - ወረዳ

ጥናቱ የሚካሄድበት ወረዳ ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 4 - ገበሬ ማህበር

ጥናቱ የሚካሄድበት ገበሬ ማህበር ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 5 - ቆጠራ ቦታ

ጥናቱ የሚካሄድበት ቆጠራ ቦታ ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 6 - የቤተሰብ መለያ ቁጥር

የተመረጠው ቤተሰብ መለያ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ፐ 96/3ሀ፡ 96/3ለ፡ 96/3ሐና 96/3መ ክፍል 1 ዓምድ 6 በመውሰድ ይሞላል።

ዓምድ 7 - የባለይዞታው መለያ ቁጥር

የባለይዞታው መለያ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ፐ 96/3ሀ፡ 96/3ለ፡ 96/3ሐና 96/3መ ክፍል 1 ዓምድ 7 በመውሰድ ይሞላል።

ዓምድ 8 - የባለይዞታው ስም

የባለይዞታው ስም ከቅጽ ግ.ና.ፐ 96/3ሀ ወይም 96/3ለ፡ ወይም 96/3ሐ፡ ወይም 96/3መ ክፍል 1 ከዓምድ 8 በመውሰድ በዚህ ዓምድ ይመዘገባል።

ዓምድ 9 - የፓርስል ቁጥር

የፓርስል ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ፐ 96/3ሀ፡ 96/3ለ፡ 96/3ሐ ና 96/3መ ክፍል 2፡ ካሉት ዓምዶች በመውሰድ ይሞላል።

ዓምድ 10 - የማሣ/ሌላ የመሬት አጠቃቀም ቁጥር

የማሣው/ሌላ የመሬት አጠቃቀም ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ፕ 96/3ሀ፣ 96/3ለ፣ 96/3ሐ ና 96/3መ ክፍል 2፣ ከሚገኙት ዓምዶች በመውሰድ ይሞላል።

ዓምድ 11 - ማሣው/ሌላ የመሬት አጠቃቀም የያዘው

በዚህ ዓምድ ማሣው የተያዘው በጊዜያዊ ሰብል (አትክልትና ሥራሥር ጨምሮ) ከሆነ ኮድ «1» በቋሚ ሰብል ከሆነ ኮድ «2» በድብልቅ ሰብል ከሆነ ኮድ «3» እንዲሁም ሌላ የመሬት አጠቃቀም ከሆነ ኮድ «4» ይሞላል።

ዓምድ 12 - ተራ ቁጥር

በዓምድ 11 ኮድ «3» ለተሰጣቸው ድብልቅ ሰብሎች ከ1-3 ተራ ቁጥር ተሰጥቷል።

ዓምድ 13 - የሰብል ስም/የሌላ የመሬት አጠቃቀም ዓይነት

በዓምድ 11 ኮድ «3» ለተሞላላቸው ድብልቅ ሰብሎች ስማቸው በተናጠል /ለየብቻ/ በዚህ ዓምድ ይሞላል። በማሣው ላይ ያሉት ድብልቅ ሰብሎች ከሦስት በላይ ከሆኑ ከማሣው ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ሦስት የሰብል ዓይነቶች ብቻ ይመዘገባሉ። አንድ ዓይነት ሰብል ብቻ ወይም ሌላ የመሬት አጠቃቀም ከሆነ ደግሞ በመጀመሪያው መስመር የዚሁ ሰብል ስም ወይም የመሬት አጠቃቀም ዓይነት ይመዘገባል።

ዓምድ 14 ና 15 - በዓምድ 11 ኮድ «1»፣ «2» ና «3» ከተሞላ የምርት መጠን በአካባቢ መለኪያ

እነዚህ ዓምዶች የሚሞሉት በዓምድ 11 ኮድ «1» ወይም «2» ወይም «3» ከተሞላ ነው። በዓምድ 10 በተጠቀሰው ማሣ ላይ የሚገኘውና በዓምድ 13 የተመዘገበው ሰብል ምርቱ ምን ያህል እንደሚሆን በአካባቢ መለኪያ ተጠይቆ የመለኪያው ስም በዓምድ 14 መጠኑ ደግሞ በዓምድ 15 ይሞላል። በድብልቅ ለሚገኙት ሰብሎች የምርት መጠን በተናጠል ተጠይቆ መመዝገብ እንዳለበት ማስታወስ ያስፈልጋል።

ዓምድ 16 - በድብልቅ ለተያዘ ማሣ ብቻ /ከማሣው ሰብሉ የያዘው ስፋት ድርሻ በመቶኛ/

በዓምድ 13 በተናጠል የተዘረዘሩትን ድብልቅ ሰብሎች አስመልክቶ በድብልቅ ከሚገኙበት ማሣ እያንዳንዱ ሰብል የያዘው የመሬት ስፋት ድርሻ ከመቶ ምን ያህል እንደሆነ ባለይዞታው ተጠይቆ በዚህ ዓምድ ይሞላል። ከሦስት በላይ ድብልቅ ካጋጠመ ከማሣው ከፍተኛ ድርሻ ያላቸውን ሦስት ሰብሎች ብቻ ድርሻቸው ከመቶ ተጠይቆ ይመዘገብላቸዋል።

ክፍል 2. የማሣ/ሌላ የመሬት አጠቃቀም ስፋት ልኪ ውጤት

ዓምድ 1 - የማሣው/ሌላ የመሬት አጠቃቀም የተለካበት ቀንና ወር

በዚህ ዓምድ ማሣው/ሌላ የመሬት አጠቃቀም የተለካበት ቀንና ወር ይጻፋል:: ለምሳሌ ማሣው/ሌላ የመሬት አጠቃቀም የተለካው ህዳር 6 ቀን ቢሆን በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ «0603» ይሞላል ማለት ነው::

ዓምድ 2 - ስፋት በስኴየር ሜትር

ከሂሣብ ማሽኑ (Calculator) የተገኘው የማሣ/የሌላ መሬት አጠቃቀም ስፋት በስኴየር ሜትር በተሰጠው ክፍት ቦታ ውስጥ ይሞላል::

ዓምድ 3-4 - የማሣው/ሌላ የመሬት አጠቃቀም ስፋት በአካባቢ መለኪያ

ዓምድ 3 - የአካባቢ መለኪያ ስም

በዚህ ቅጽ ክፍል 1 ዓምድ 13 ላይ የተመዘገበው የሰብል ዓይነት /ሌላ የመሬት አጠቃቀም/የያዘውን መሬት ስፋት በአካባቢ መለኪያ ለማወቅ በቅጽ ግ.ና.ፕ 96/3ሆ፡ 96/3ለ ና 96/3ሐ ክፍል 2 ጥያቄ 2 እንዲሁም በቅጽ ግ.ና.ፕ 96/3መ ክፍል 2 ዓምድ 8 የተገለጸው የአካባቢ መለኪያ ስም በዚሁ ዓምድ ውስጥ ይጻፋል:: ለኮድ የተተወው ቦታ ምንም አይሞላበትም::

ዓምድ 4 - ስፋት

በክፍል 1 ዓምድ 13 ላይ የተመዘገበው ማሣ/የመሬት አጠቃቀም /ስፋት በዚህ ክፍል ዓምድ 3 በተጠቀሰው የአካባቢ መለኪያ ተጠይቆ የተገኘው መልስ ይሞላል::

ዓምድ 5 - በማሣው/ሌላ የመሬት አጠቃቀም ላይ የስፋት ልኪ ካልተካሄደ ምክንያት

በክፍል 1 ዓምድ 13 ላይ በተመዘገበው ማሣ/ሌላ የመሬት አጠቃቀም የስፋት ልኪ ካልተካሄደለት በዚህ ዓምድ ምክንያቱ ይገለጻል:: ለኮድ የተተወው ቦታ ምንም አይሞላበትም::

ክፍል 3. የማሣ /ሌላ የመሬት አጠቃቀም ስፋት መለኪያ

በቅጽ ግ.ና.ፕ 96/4 ክፍል 1 ዓምድ 13 የተመዘገበው ማሣ /ሌላ የመሬት አጠቃቀም በሜትርና በኮምፓስ ተለክቶ የማሣው/የሌላ መሬት አጠቃቀጠም የጎን ርዝመትና ቤሪንግ የሚመዘገብበት ክፍል ነው::

ቤሪንግ /0/:- ኮምፓስ በመጠቀም ለእያንዳንዱ ማሣ/ሌላ የመሬት አጠቃቀም ጎን የተነበበው ቤሪንግ የሚመዘገብበት ነው::

ርዝመት /ሜ/:- ሜትር በመጠቀም የተለካው እያንዳንዱ የማሣው/ሌላ የመሬት አጠቃቀም ጎን ርዝመት የሚመዘገብበት ነው::

*ማስታወሻ፡*

*በጥናቱ መሸፈን ያለበት አንድ ይዞታ ከተመረጠው ቆጠራ ቦታ ክልል ውጪ ቢገኝ ይዞታው የተመረጠው ቆጠራ ቦታው ከሚገኝበት ገበሬ ማህበር ክልል ውጭ እስካልሆነ ድረስ ለይዞታው የስፋት ልክቶሽና ከተመረጠም የሰብል አጨዳ ይካሄድለታል፡፡ ሆኖም ይዞታው የቆጠራ ቦታው ከሚገኝበት ገበሬ ማህበር አላለቀም፡፡*

## *የማሣ /ሌላ መሬት አጠቃቀም አለካክ መመሪያ*

አስፈላጊው የአካባቢ መለያ በዚህ ቅጽ መጀመሪያ ክፍል ላይ ከተሞላ በኋላ ወደ ባለይዞታው በመሄድ ይዞታውን መለካት አስፈላጊ መሆኑን ካስረዱ በኋላ ለመለካት ፈቃድ ማግኘት ተገቢ ነው፡፡ ከዚያም ከዚህ በታች በተሰጠው መመሪያ መሠረት ማሳው/ የመሬት አጠቃቀሙ ይለካል፡፡ ማሣው /ሌላ የመሬት አጠቃቀሙ/ ከመለካቱ በፊት ቅርጹንና ማዕዘኑን ዞሮ ማየትና መለየት ያስፈልጋል፡፡ ከዚያም ወደ ማሣው እምብርት /መሐል/ በመግባት በኮምፓሱ አማካይነት የማሣው /ሌላ የመሬት አጠቃቀም ሰሜናዊ ምዕራብ /North-western/ ማዕዘኑን ወይም ወደዚህ የሚቀርበውን በመፈለግ እዚህ ማዕዘን ላይ ችካል ይተከላል፡፡ ይህም ማዕዘን A ይባላል፡፡ ልኪውን ለማከናወን የተመደበው ረዳት ወደ ቀኝ /Clock wise/ ወዳለው ቀጣይ ማዕዘን (ጎን) በመሄድ ማዕዘኑ ላይ ችካል ይተክላል፡፡ ይህም ማዕዘን B ይባላል፡፡ ይህ ከሆነ በኋላ መረጃ ሰብሳቢው ከቆመበት A ወደ B ያለውን አንግል /Angle/ ኮምፓስ በመጠቀም ማንበብና የጎን ርዝመቱንም ማለትም ከA-B ያለውን ርቀት በሜትር በመለካት ውጤቱን በቅጹ ላይ በተሰጡት ቦታዎች ማስፈር ያስፈልጋል፡፡

### የአንግል አነባበብ

A ላይ በመቆም ፊትን ወደ B በመመለስ የBን ቤሪንግ ከA ማንበብና የተገኘውን ቁጥር ቤሪንግ /0/ በሚለው ጽሑፍ አንፃር የጎን መለያ A- B ከሚለው ሥር በሚገኘው ባዶ ቦታ መመዝገብ ያስፈልጋል፡፡ አንግል/ቤሪንግ ሲነበብ የኮምፓሱ መርፌ መንቀጥቀጥ /መወዛወዝ/ ማቆሙን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ማንኛውም ማግኔት ሊስብ የሚችል ብረት ነክ ነገር ሁሉ ንባቡን ሊያበላሽ ስለሚችል ኮምፓሱ በሚነበብበት ጊዜ ከኮምፓሱ ማራቅ ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም በጣም ትንሽ የሆነ የአንግል ስህተት የማሣውን ስፋት ሊያዛባ ስለሚችል ነው፡፡

### የርዝመት አለካክ

ከA በመጀመር ከA እስከ B ያለው የጎን ርዝመት በሜትር ይለካል፡፡ የሚለካበት ሜትር B ላይ ሳይደርስ የቀረ እንደሆነ ከደረሰበት በመቀጠል እስከ B ያለውን በመለካት ጠቅላላ ርዝመቱን ማለት ከ A እስከ B ያለውን ቁርጥራጮችን በመደመር የተገኘውን ርዝመት /ሜ/ ከሚለው ጽሑፍ አንፃር ባለው ባዶ ቦታ ይመዘገባል፡፡

ከላይ በተገለጸው መመሪያ መሠረት አሁን ደግሞ ማዕዘን B ላይ በመቆም ማዕዘን C ላይ የቆመውን ረዳት ወይም ችካል በመመልከትና የአንግሉን ቤሪንግ ንባብ በኮምፓስ በማንበብ ቤሪንግ /0/ በሚለው አንፃር ባለው ባዶ ቦታ በትክክል ማስፈርና ከዚያም ከ B እስከ C ያለውን ርዝመት በመለካት በተገቢው ቦታ ማስፈር ያስፈልጋል:: በዚህ ቅደም ተከተል መሠረት አንግል በማንበብና ርዝመት በመለካት መነሻ ከሆነው ማለትም A እስከሚደርስ (እስከሚገጥም) ሁልጊዜ ወደቀኝ /Clock wise/ በመሄድ ሥራው መከናወን አለበት::

## የማሣው ስፋት አሰላል

የማሣው ቤሪንግና ርዝመት በትክክል ከተለካ በኋላ ለመረጃ ሰብሳቢው በተሰጠው የሂሣብ ማሽን /Calculator/ እያንዳንዱን ቤሪንግና ርዝመት በሒሣብ ማሽኑ በማስገባት ማሽኑ የሚሰጠው አሀዝ (የማሣው ስፋት) በክፍል 2 ዓምድ 2 ይመዘገባል::

*ማሳሰቢያ:-*

1. *የሂሣብ ማሽኑ የሚሰጠው ማለትም ማሣው ሲለካ የሚፈጠረው የስህተት መጠን (error) 5% ና በላይ ከሆነ ልኪው ትክክል ስላልሆነ በድጋሚ የማሣው ቤሪንግና ርዝመት መለካት አለበት:: ነገር ግን የስህተት መጠኑ ከ5% በታች ከሆነ ማሣው በትክክል የተለካ ስለሆነ ከሂሣብ ማሽኑ ስሌት የተገኘው ውጤት (አሀዝ) በዚህ ቅጽ ክፍል 2 ዓምድ 2 ይመዘገባል::*

2. *የሂሣብ ማሽኑን አያያዝና አጠቃቀም እንዲሁም የቤሪንግና ርዝመት መጠን ወደ ማሽኑ ማስገባት፣ የማሳ ስፋትና የስህተት (Error) መጠን እንዴት በማሽኑ እንደሚሰላ በሥልጠና ወቅት በሚገባ መረዳት አስፈላጊ ነው::*

## የቋሚ ሰብል ዛፎች ማሣ አለካክ ተጨማሪ መመሪያ (ቡና፣ ጫት፣ ሸንኮራ አገዳንና አናናስን አይጨምርም)

የቋሚ ሰብሎች በዓይነት ወይም በድብልቅ የተወሰነ ቅርጽ ያለው ማሣ ከያዙ የማሣ አለካክ መመሪያን በመከተል የማሣ ልኪ ይደረግላቸዋል:: ሆኖም ተራርቀውና ተበታትነው የተተከሉ ቋሚ ሰብሎች ለምሳሌ ከባለይዞታው ቤት ፊትና ጀርባ ሁለት የቋሚ ሰብል ዛፎች ወይም በባለይዛታው የግጦሽ መሬት ላይ ተራርቀው (ተበታትነው) ቢገኙ የተወሰነ ቅርጽ ያለው ማሣ ይዘዋል ለማለት ስለሚያስቸግር የማሳ ልኪውን አፈጻጸም አስቸጋሪ ያደርገዋል::

የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ለአንድ ዓይነት ቋሚ ሰብል ከዛፎቹ መካከል በመጠን መሀከለኛ የሆነውን ዛፍ በመምረጥ ዛፉ የሚገኝበትን ቦታ ሁሉንም የዛፉን ቅርንጫፎች የሚያካትት አራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው መሬት አዘጋጅቶ በማሣ አለካክ መመሪያ መሠረት ኮምፓስና ሜትር በመጠቀም መለካትና የልኪውን ውጤት በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/4 መመዝገብ ያስፈልጋል:: ለቀሪዎቹ ዛፎች ግን እንደገና መለካት ሳያስፈልግ ይህንኑን ውጤት እየደጋገሙ በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/4 ላይ መመዝገብ ያስፈልጋል:: የቋሚ ሰብል ዛፎቹ ዓይነት የተለያየ ከሆነ ግን ከየዓይነቱ ከላይ በተሰጠው መመሪያ መሠረት አንድ ዛፍ ብቻ ለክቶ ይኸው ውጤት ለቀሪዎቹ ተመሳሳይ ቋሚ ሰብል ዛፎች በሙሉ ተደጋግሞ በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/4 ላይ ይመዘገባል::

ይህ ሁኔታ በማሣ ቁጥር አሰጣጥ ላይም ከተለመደው አሰራር ለየት ያለ መሆኑን ከወዲሁ መገንዘብ ያስፈልጋል:: ከላይ በተጠቀሰው ሁኔታ የሚገኙ የቋሚ ሰብል ዛፎች በሚገኙበት ፓርስል እያንዳንዳቸው የየራሳቸው ማሳ ቁጥር ተሰጥቷቸው በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ለ ከተመዘገቡ በኋላ አስፈላጊው መረጃ የሚሞላላቸው መሆኑ መዘንጋት የለበትም::

የቋሚ ሰብል ዛፎች አበቃቀል የተለያየ በመሆኑ አንዳንዶቹን የቋሚ ሰብል ዛፎች ለመቁጠር አስቸጋሪ ይሆናል:: ለምሳሌ:- ማንጎ፣ ብርቱካን፣ አቮካዶ የመሳሰሉት ዛፎች አንዳንድ ብቻ ሆነው ስለሚበቅሉ ለመቁጠር አያስቸግሩም እንደ እንሰትና ሙዝ የመሳሰሉት ተክሎች ግን እጅግ ተጠጋግተው ስለሚበቅሉ ለመቁጠር ያስቸግራሉ:: ስለዚህ ለመለየት የሚያስቸግሩትንና ተጠጋግተው የሚበቅሉትን እንደ አንድ ዛፍ መቁጠር ይገባል:: የቋሚ ሰብል ችግኞች የተወሰነ ቅርጽ ያለው ማሳ ከያዙ ብቻ በመመሪያው መሠረት የማሳ ልኪ ይካሄድላቸዋል:: ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችም ይሰበሰቡላቸዋል ሆኖም ችግኞች አይቆጠሩም:: ሌሎቹ ቋሚ ሰብሎች ለምሳሌ:- ኮክ፣ እንሰት፣ መንደሪን የመሳሰሉትና በዚህ መመሪያ በገጽ የተዘረዘሩት ቋሚ ሰብሎች በሙሉ ሌሎች መረጃዎች እንደሚሰበሰብላቸውና የማሳ ልኪ እንደሚካሄድላቸው መዘንጋት የለበትም::

## ክፍል 4 <u>አጨዳ ለሚካሄድላቸው ጊዜያዊ ሰብሎች የረጅሙ/አጭሩ ጎን ርዝመት እና ከራንደም የተገኘ</u>

በዚህ ክፍል አጨዳ ለሚካሔድላቸው የጊዜያዊ ሰብሎች ማሣ የመጀመሪያው ዓምድ አጭሩን እና ረጅሙን ጎን ርዝመት መመዝገቢያ ሲሆን የሁለተኛው አምድ የራንደም ቁጥር ሰንጠረዥ ተጠቅሞ የአጭሩን እና የረጅሙን ጎን ከራንደም የተገኘ ርዝመት መመዝገቢያ ነው::

ክፍል 5 አትክልት፣ ሥራ ሥርና ቋሚ ሰብሎችን ብቻ በተመለከተ በዚህ ክፍል የሚሰበሰበው መረጃ ቀጥሎ የተዘረዘሩትንና በባለይዞታው ማሳ ላይ የሚገኙትን

| ሀ. አትክልት | ለ. ሥራ ሥር | ሐ. ቋሚ ሰብል |
|---|---|---|
| 1. ሠላጣ | 1. ቀይ ሥር | 1. ቡና |
| 2. ጥቅል ጎመን | 2. ካሮት | 2. ጫት |
| 3. የሃበሻ ጎመን | 3. ቀይ ሽንኩርት | 3. ጌሾ |
| 4. ቲማቲም | 4. ድንች | 4. ሸንኮራ አገዳ |
| 5. ቃሪያ | 5. ነጭ ሽንኩርት | 5. ብርቱካን |
| 6. በርበሬ | 6. ጎደሬ | 6. ሙዝ |
| 7. ቆስጣ | 7. ስኳር ድንች | 7. ሎሚ |
| | | 8. ፓፓያ |
| | | 9. ማንጎ |
| | | 10. ዘይቱን |
| | | 11. አቮካዶ |
| | | 12. አናናስ |

ብቻ ይመለከታል::

ባለይዞታው ከላይ ከተዘረዘሩትና ይዞታው ለሆኑት በቅጽ 96/4 ልኪ ለተደረገላቸው ማሳዎች በሙሉ በክፍል 5 የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች በማቅረብ አስፈላጊው መረጃ ይሰበሰባል::

ዓምድ 1 ይጨምራል = 1፣ እኩል ይሆናል = 2፣ ይቀንሳል = 3

በቅጽ 96/4 የተመዘገበውንና ልኪ የተደረገለትን ማሳ በማስመልከት የዘንድሮው የሰብል ምርታማነት ከአምናው ጋር ሲነጻጸር የሚጨምር ከሆነ ኮድ 1፣ እኩል ከሆነ ኮድ 2፣ የሚቀንስ ከሆነ ደግሞ ኮድ 3 በዚሁ ዓምድ ለኮድ መጻፊያ በተሰጠው ቦታ ባለይዞታው ተጠይቆ የሚሰጠው መልስ ይመዘገባል::

ዓምድ 2 የሚጨምር ከሆነ መጠን በመቶኛ ባለይዞታው

ባለይዞታው በዓምድ 1 ተጠይቆ የሰጠው መልስ ይጨምራል ከሆነ በዚህ ዓምድ የሚጨምረው መጠን በመቶኛ ምን የህል እንደሆነ ተጠይቆ በተሰጠው ቦታ ይሞላል:: ምሳሌ ዘንድሮ የብርቱካን ምርታማነት ከአምናው ጋር ሲነጻጸር 10% ይጨምራል ከተባለ በተሰጠው ቦታ 10 ይሞላል::

ዓምድ 3 የሚቀንስ ከሆነ መጠን በመቶኛ

ባለይዞታው በዓምድ 1 ተጠይቆ የሰጠው መልስ ይቀንሳል ከሆነ በዚህ ዓምድ የሚቀንሰው መጠን በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ተጠይቆ በተሰጠው ቦታ ይሞላል:: ምሳሌ ዘንድሮ የድንች ምርታማነት ከአምናው ጋር ሲነጻጸር 25% ይቀንሳል ከተባለ በዚህ ዓምድ 25 ይመዘገባል::

ዓምድ 4 የተገኘው ለውጥ በመቶኛ

ይህ ዓምድ በዓምድ 1፣ 2 እና 3 የተመዘገበውን በማገናዘብ የሚሞላ ይሆናል:: በዓምድ 1 ይጨምራል ተብሎ ኮድ 1 ከተሞላ እና በዓምድ 2 የሚጨምረው መጠን በመቶኛ ከተመዘገበ በኋላ በዚህ ዓምድ /ዓምድ 4/ የሚጨምረው መጠን በመቶ ላይ ተደምሮ ውጤቱ በተሰጠው ቦታ ይሞላል::

ምሳሌ 1

ዘንድሮ የብርቱካን ምርታማነት ከአምናው ጋር ሲነጻጸር ይጨምራል ተብሎ በዓምድ 1 ኮድ 1 ከተሞላና በዓምድ 2 ደግሞ የሚጨምረው መጠን በመቶኛ 10 ተብሎ ከተመዘገበ በዓምድ 4 110 ይሞላል::

2. ዘንድሮ የድንች ምርታማነት ከአምናው ጋር ሲነጻጸር ይቀንሳል ተብሎ በዓምድ 1 ኮድ 3 ከተሞላና በዓምድ 2 ደግሞ የሚቀንሰው መጠን በመቶኛ 25 ተብሎ ከተመዘገበ በኋላ በዓምድ 4 ከመቶ ላይ 25 ተቀንሶ የሚገኘው ውጤት /ማለት 75/ ይመዘገባል።

3. ዘንድሮ የሃበሻ ጎመን ምርታማነት ከአምናው ጋር ሲነጻጸር እኩል ይሆናል ተብሎ በዓምድ 1 ኮድ 2 ከተሞላ ዓምድ 2 እና 3 በሠረዝ ታልፈው ዓምድ 4 ላይ 100 ተብሎ የመዘገባል።

ማስታወሻ የአሁኑን ዘመን ምርታማነት ከአምናው ጋር ባለይዞታው ሲያነጻጸርልን በሁለቱም የምርት ዓመታት በስፋት እኩል የሆኑ ማሳዎችን በማሰብ መሆን አለበት።

## በ1996 ዓ.ም በመላ አገሪቱ ለሚካሔደው የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት መረጃ ከመስክ ለመሰብሰብ የሚያስችል መመሪያና የቅጽ ግ.ና.ጥ 96/2 አሞላል።

### I. መግቢያ

የማእከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ባለፉት ሁለት አስርት አመታት በየአመቱ የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት በማካሔድ ወቅታዊ የትንበያ መረጃዎችን ለመንግሥትና ለሌሎች ተጠቃሚዎች ሲያቀርብ መቆየቱ ይታወሣል። ሆኖም መስሪያ ቤቱ በየአመቱ ሲያቀርባቸው የነበሩ የትንበያ መረጃዎች የመረጃው ተጠቃሚዎች እንዲቀርብላቸው የሚፈልጉበትን ወቅት ከሞላ ጉደል ያሟላ አልነበረም። በመሆኑም የባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ የመረጃው ተጠቃሚዎች ጥያቄዎችን ለማሟላት ባካሄደው ጥናት ከዚህ ቀደም ይካሄድ በነበረው ከመስክ መረጃዎችን የማሰባሰብ ሥራ ላይ መጠነኛ ለውጥ በማድረግ የትንበያ መረጃዎችን ተጠቃሚዎች በሚፈልጉበት ወቅት ለማቅረብ የሚያስችለውን አሰራር በመንደፍ በዚህ አመት ተግባራዊ ለማድረግ አቅዷል። በመሆኑም ከዚህ በታች የቀረቡትን የአሰራር መመሪያዎች በ1996 ዓ.ም የሰብል·ምርት ትንበያ ጥናት ከቅ/ጽ/ቤት ሀላፊዎች ጀምሮ እስከ መረጃ ሰብሣቢዎች ድረስ ያሉ በስራው የሚሳተፉ የባለሥልጣኑ መ/ቤት ሠራተኞች ተግባራዊ እንዲያደርጓቸው በማሳሰብ የአሰራር መመሪያዎቹ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### II. የ1996 ዓ.ም የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት የሚሸፈኑ ሰብሎችና የመስክ ስራ ክንውንና አሰራር መመሪያ

ከዚህ በታች በዝርዝርና በቅደም ተከተል የቀረቡ የመስክ ስራ የአሰራር መመሪያዎች በመስከረም ወር በ1996 ዓ.ም መጀመሪያ ጀምሮ ለአንድ ወር በመላ ሀገሪቱ በተመረጡ ቆጠራ ቦታዎች በሚካሔደው የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት የመስክ ስራ ተግባራዊ ይሆናሉ።

1ኛ. በ1996 ዓ.ም በሚካሄደው <u>የሰብል ትንበያ ጥናት</u> /የዋናውን መኸር ጥናት አይጨምርም/ በሠንጠረዥ 1 የተዘረዘሩት የሰብል አይነቶች ብቻ እንዲሸፈኑ የተወሰነ ሲሆን ጥናቱ እንዲካሔድበት በሚመረጠው ቆጠራ ቦታና ለጥናቱ በሚመረጡ 10 ቤተሰቦች ውስጥ የሚገኙ ባለይዞታዎች በሰብል ከተያዙ ማሣዎቻቸው በሠንጠረዥ 1 በተገለፁት ሰብሎች የተያዙትን ብቻ በማስመልከት ለትንበያ የሚያገለግሉ መረጃዎችን በቅጽ 96/2 ፤ 96/3ሀ ፤ 96/3ሐ እና በቅጽ 96/4 ከእያንዳንዱ ባለይዞታ በቃለ መጠይቅና በተግባራዊ መረጃ አሰባሰብ ዘዴ መሰብሰብና የተሰበሰቡትን መረጃዎች በሚመለከተው ቅጽ መሙላት የመረጃ ሰብሣቢው ዋነኛ ተግባር ሲሆን በተጓዳኝ የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቅበታል።

ሀ . በጥናቱ በሚሸፈን ቆ/ቦታ የተመደበ አንድ መረጃ ሰብሳቢ ከላይ በተጠቀሱት ቅጾች በጥናቱ ከሚሸፈኑ እያንዳንዱ ባለይዞታ መረጃዎችን ከመሰብሰቡ በፊት መረጃ

ሰብሳቢው በእያንዳንዱ ቆጽ ክፍል 1 የሚሞሉ የአካባቢ መለያ ስሞችንና ኮዳቸውን እንዲሁም ተዛማጅ መረጃዎችን በቅድሚያ በመሙላት ማዘጋጀት ይኖርበታል። ለዚህም እንዲረዳው የተመደበበት ቆ/ቦታ የሚገኝበት ክልል ፤ ዞን ፤ ወረዳ ፤ ገ/ማህበር ስሞችና ኮዶች እንዲሁም የቆጠራ ቦታውን መለያ ቁጥር ወደ ምድብ ሥራ ቦታው ከመንቀሣቀሱ በፊት ከቅ/ጽ/ቤት ኃላፊው /የመስክ ሥራ ተቆጣጣሪ/ ጠይቆ መያዝ ይኖርበታል።

<u>ሠንጠረዥ 1 በ1996 ዓ.ም በሚካሄደው የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት የማሣ ልክቶሽ ፤ የሰብል ሁኔታ ግምገማና የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ መረጃዎች ከመስክ የሚሰበሰብላቸው ሰብሎች ዝርዝርና ኮድ</u>

| ተ.ቁ | የሰብል ስም | ኮድ | ተ.ቁ | የሰብል ስም | ኮድ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ገብስ | 01 | 12 | ሽምብራ | 11 |
| 2 | ጤፍ | 07 | 13 | ምስር | 14 |
| 3 | ስንዴ | 08 | 14 | ኑግ | 16 |
| 4 | በቆሎ | 02 | 15 | አብሽ | 36 |
| 5 | ማሽላ | 06 | 16 | ግብጦ | 17 |
| 6 | ዳጉሣ | 03 | 17 | ኑግ | 25 |
| 7 | አጃ | 04 | 18 | ተልባ | 23 |
| 8 | ሩዝ | 05 | 19 | ለውዝ | 24 |
| 9 | ባቄላ | 13 | 20 | ሱፍ | 28 |
| 10 | አተር | 15 | 21 | ሰሊጥ | 27 |
| 11 | አደንጓሬ | 12 | 22 | ጉመን ዘር | 26 |

ለ. ከላይ በተጠቀሱት በእያንዳንዱ ቆጽ መረጃ ለተሰበሰበለት እያንዳንዱ የሰብል አይነት የሰብሉ ስም ከተመዘገበበት መስመር ትይዩ በተዘጋጀው ኮድ የመመዝገቢያ ቦታ በሠንጠረዥ 1 ለየሰብሉ ከተሰጠው ኮድ ትክክለኛውን በመምረጥ በተገቢው ቦታ ማስፈር/መሙላት/ የመረጃ ሰብሳቢው ተጨማሪ ሥራ ይሆናል።

ሐ. በሠንጠረዥ 1 የተዘረዘሩና በቅጽ 96/3ሀ እና 96/3ሐ በጥናቱ የተካተተ እያንዳንዱ ባለይዞታ ማሣ ላይ እንደሚገኙ ከተመዘገቡ ሰብሎች ብልሽት ለደረሰባቸው ሰብሎች የሚመዘገበው የብልሽቱ አንድ ዋና ምክንያትና ኮድ በሰንጠረዥ 2 የተመዘገቡትን ምክንያቶችና የተሰጣቸውን ትክክለኛ ኮድ በመምረጥ በየቅጾቹ በተዘጋጀው የኮድ መመዝገቢያ ቦታ መመዝገብ የመረጃ

ሰብሳቢው ተግባር ይሆናል። እዚህ ላይ አንዳንድ ጊዜ በሠንጠረዥ 2 ከተገለፁት ምክንያቶች የተለዩ ምክንያቶች በመልስ ሰጭው ሊቀርቡ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ የተሠጠውን ምክንያት እንዳለ መመዝገብና ኮድ በሚለው ዓምድ ሥር ለሌሎች የተሰጠው ኮድ ማለት ኮድ "10" መሙላትን ማስታወስ ተገቢ ይሆናል።

*ሠንጠረዥ 2 የሰብል ብልሽት /የምርት መጠን እንዲቀንስ / የሚያደርጉ ምክንያቶች ኮድ*

| ተ.ቁ | ምክንያት | ኮድ |
|---|---|---|
| 1 | ፀረ አዝዕርት የሆኑ በሽታዎች | 01 |
| 2 | ውርጭና ጎርፍ | 02 |
| 3 | አንበጣ | 03 |
| 4 | ፀረ አዝዕርት የሆኑ ተባዮች | 04 |
| 5 | የዝናብ እጥረት | 05 |
| 6 | የዝናብ ብዛት | 06 |
| 7 | አዱር አራዊት | 07 |
| 8 | ወር | 08 |
| 9 | በረዶ | 09 |
| 10 | ሌሎች | 10 |

<u>ማስታወሻ</u> በቅጽ 96/4 የስፋት መረጃ ለተሰበሰበላቸው በሠንጠረዥ 1 በተዘረዘሩት ሰብሎች ለተያዙ ማሣዎች በመረጃ ሰጪ የተገለፁና በቅፁ የሰፈሩ የአካባቢ የስፋት መለኪያዎችና ማሣውን ለመለካት ስላለመቻሉ ለሰፈሩ መረጃዎች መረጃ ሰብሣቢው ኮድ እንዲሞላ አይጠበቅም። ስለሆነም ለኮድ መስጫ የተተወው ቦታ ባዶ መተው ይኖርበታል ማለት ነው።

2ኛ . በ1996 ዓ.ም በሚካሄደው የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት በተመረጡት ቆጠራ ቦታዎች የሰብል ትንበያ ጥናት በሚሸፍናቸው 10 ቤተሰቦች ውስጥ የሚገኙ ባለይዞታዎች በሠንጠረዥ 1 ከተዘረዘሩት ሰብሎች በተጨማሪ ሌሎች ሰብሎች ሌላ የመሬት አጠቃቀም በማሣዎቻቸው ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል። ሆኖም እነዚህን በተመለከተ ከመስከረም ወር በኋላ በሚካሔደው የግብርና ናሙና ጥናት እንዲሸፈኑ የተወሰነ በመሆኑ መረጃ ሰብሳቢ የፖርሰልꝉ የማሣ ቁጥሮችና የሰብሎቹን ስም በሚመለከተው ቅጽ ማለትም /በቅጽ 96/3ሀꝉ3ለꝉ3ሐꝉ 3መ/በመመዝገብ ከአወራረስ በኋላ የትንበያ ጥናቱ እንዳለቀ የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታንና ማሣ ልክቶሽን የተመለከቱ መረጃዎችን መሰብሰብ እንዳለበት መዘንጋት የለበትም።

ኢትዮጵያ በዚህ አመት የደረሰባት ድርቅ ከመቼውም ጊዜ የከፋ መሆኑ ለማንኛውም የሀገሪቱ ዜጋ ግልጽና በገሀድ የታየ ሀገሪቱ ያጋጠማት ብርቱ ችግር ሆኗል። በ1996 ዓ.ም የሚሆነውን ከወዲሁ ለማወቅ ደግሞ ከሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ወቅታዊና አስተማማኝ መረጃዎች የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን እንዲያቀርብ ይጠበቃል። በመሆኑም የባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ የ1996 ዓ.ም መኸር ወቅትን የሚመለከት የሰብል ምርት ትንበያ መረጃዎችን በማቅረብ መንግሥትንና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሁኔታውን ከወዲሁ በማሳወቅ ችግር ከመድረሱ በፊት ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱ በማገዝ ያለው ድርሻ ይህ ነው አይባልም። ስለሆነም በዚህ ስራ የተሰማሩ የባለስልጣኑ መስሪያ ቤት ሠራተኞች ወቅታዊና አስተማማኝ የትንበያ መረጃዎችን ለማቅረብ ከላይ የተዘረዘሩትን የአሰራር መመሪያዎች ተግባራዊ በማድረግ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ የባለስልጣኑ መስሪያ ቤት ያሣስባል።

## የቅጽ ግ.ና.ጥ 96/2 - የሰብል ሁኔታ ግምገማ አሞላል

ይህ ቅጽ ለሰብል ትንበያ ጥናት የሚያገለግል ሲሆን በናሙና ለተመረጡት 25 ቤተሰቦች በሙሉ በገጽ 69 በሠንጠረዥ 1 ለተጠቀሱት የሰብል ሁኔታ ግምገማ መረጃ የሚሰበሰብበት ነው።

ይህ ቅጽ ሁለት ክፍሎች ሲኖሩት ክፍል 1 ጥናቱ የሚካሄድበት የአካባቢ መለያ የሚሞላበት ሲሆን ክፍል 2 ደግሞ ትንበያ ለሚደረግላቸው ሰብሎች የሰብል ሁኔታ ግምገማ መረጃ የሚሰበሰብበት ነው።

ክፍል 1. የአካባቢ መለያ

ዓምድ 1 - ክልል

ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 2 - ዞን

ጥናቱ የሚካሄድበት ዞን ስም ወይንም ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 3 - ወረዳ

ጥናቱ የሚካሄድበት ወረዳ በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 4 - ገበሬ ማህበር

ጥናቱ የሚካሄድበት የገበሬ ማህበር ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 5 - ቆጠራ ቦታ

ጥናቱ የሚካሄድበት ቆጠራ ቦታ ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 6 - የሰብሉ ስም

በዚህ ዓምድ ውስጥ የሰብል ሁኔታ ግምገማ የሚደረግለት የአንድ ሰብል ስም ብቻ ይሞላል።

ማስታወሻ

1

ድብልቅ ሰብሎችን በሚመለከት በዚህ ቅጽ የትንበያ መረጃ የሚሰበሰበው እንደሚከተለው ይሆናል። ትንበያ ለሚአረግላቸው የሰብል አይነቶች በአንድ ማሣ ላይ በድብልቅ የተዘሩ ማለትም ሁለትና ከሁለት በላይ ድብልቅ ሰብሎች የጊዜያዊ ሰብል ድብልቅ ከሆኑ ለምሣሌ እንደ በቆሎና ማሽላ፣ አደንጓሬ፣ ማሽላና በቆሎ፣ ... ወዘተ ለእያንዳንዱ የሰብል ዓይነት አንድ ቅጽ በመሙላት ተፈላጊው የትንበያ መረጃ ይሰበሰብላቸዋል። ሆኖም ድብልቁ የቋሚና የጊዜያዊ ሰብሎች ለምሣሌ እንደ ቡናና ማሽላ፣ ጫት ፣

በቆሎና አደንጓሬ ...ወዘተ ከሆነ ለአንዱ ሰብል አንድ ቅጽ በመሙላት ተፈላጊ የ

ተገቢ ነው። ሆኖም የሰብል ዓይነቱ ቀደም ብሎ መረጃ ከተሰበሰበለት በየዓይነቱ ከተሰበሰበው መረጃ ጋር ማካተት አስፈላጊ ነው።

2. በድብልቅ የሚገኙ ሰብሎችን በተመለከተ በዓምድ 6 የሰብል ስም እንዴት እንደሚመዘገብ የሚከተለውን ምሳሌ ማጤን አስፈላጊ ነው።

ምሳሌ:- ለዚህ ጥናት የተመረጠ አንድ ባለይዞታ በሁለት የተለያዩ ማሣዎቹ ላይ የበቆሎና ማሽላ የድብልቅ ሰብል ቡቃያዎች የሚገኙ ቢሆን በተናጠል ለእያንዳንዳቸው አንዳንድ ቅጽ በመጠቀም በአንዱ ቅጽ ዓምድ 6 ላይ በቆሎ ተብሎ ሲሞላ በሌላ ቅጽ ዓምድ 6 ደግሞ ማሽላ ተብሎ ተሞልቶ አስፈላጊው መረጃ በተናጠል ይሰበሰብላቸዋል።

ክፍል 2. የሰብል ሁኔታ ግምገማ

ዓምድ 1 - ተራ ቁጥር

ተራ ቁጥር ከ01 በመጀመር በቅደም ተከተል ተሞልቷል።

ዓምድ 2 - የባለይዞታው ስም

በክፍል 1 ዓምድ 6 ላይ የተመዘገበው ሰብል በማሣ ላይ ያላቸው ባለይዞታዎች በሙሉ በዚህ ዓምድ ይመዘገባሉ።

ዓምድ 3 - የቤተሰብ መለያ ቁጥር

የተመረጠው ቤተሰብ መለያ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሀ ወይም 96/3ሐ ክፍል 1 ዓምድ 6 በመውሰድ ይሞላል።

ዓምድ 4 - የባለይዞታው መለያ ቁጥር

የባለይዞታው መለያ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሀ ወይም 96/3ሐ ክፍል 1 ዓምድ 7 በመውሰድ ይሞላል።

ዓምድ 5 - የማሣዎች ብዛት

በዚህ ክፍል በዓምድ 2 የተመዘገበው እያንዳንዱ ባለይዞታ በክፍል 1 ዓምድ 6 በተሞላው የሰብል ዓይነት የተያዙ ማሣዎች ብዛት ብቻ በተሰጠው ክፍት ቦታ ውስጥ ይሞላል። በዚህ ዓምድ የሚሞላው በባለይዞታው ሥር ያሉት በተለያዩ የሰብል ዓይነቶች የተያዙ ማሣዎች ብዛት አለመሆኑ መታወቅ አለበት።



c:\condit.doc

ማስታወሻ:-

ድብልቅ ሰብሎችን በሚመለከት በዚህ ዓምድ የማሣዎች ብዛት አመዘጋገብ እንደሚከተለው ይሆናል:: ለምሣሌ አንድ ለዚህ ቆጠራ የተመረጠ ባለይዞታ አንድ በበቆሎ ብቻ የተያዘ አንድ በበቆሎና ማሽላ ድብልቅ ሰብሎች የተያዘ አንድ ደግሞ በበቆሎና አደንጓሬ የተያዘ በድምሩ ሦስት ማሣዎች ቢኖረው በተጠቀሰው ቅጽ የሰብል ግምገማ መረጃ የሚሰበሰበው የበቆሎን ሰብል በሚመለከት ቢሆን በሦስቱም ማሣዎች የሚገኘውን በቆሎ በጥቅል በመውሰድ ይሆናል:: በቅጹ ክፍል ሁለት ዓምድ 5 የማሣዎች ብዛት በሚለው ሥር የበቆሎ ሰብል በሦስት ማሣዎች ላይ ስለሚገኝ ሦስት ይመዘገባል:: ማሽላን በተመለከተ የሚሰበሰብ የትንበያ መረጃ ደግሞ ከበቆሎ ጋር በድብልቅ የሚገኘውን ማሽላ ብቻ በሚመለከት ይሆናል:: በዚህም መሠረት በቅጹ ክፍል 2 ዓምድ 5 የማሣ ብዛትን በተመለከተ ደግሞ አንድ ተብሎ ይመዘገባል:: ከዚህ ምሣሌ ለመረዳት የሚቻለው በድብልቅ ሰብሎች የተያዘ ማሣን ሁለት ጊዜና ከሁለት ጊዜ በላይ ደግሞ መቁጠርና መመዝገብ አስፈላጊ እንደሆነ ነው::

<u>ዓምድ 6-10</u> - የሰብሉ ምርታማነት ካለፈው ዓመት መኸር ወቅት ጋር ሲነፃፀር

<u>ዓምድ 6</u> - የሰብል ምርታማነት (ይጨምራል = 1
እኩል ይሆናል /ለውጥ የለውም/ = 2 ይቀንሳል = 3)

በክፍል 1 ዓምድ 6 የተመዘገበውን የሰብል ዓይነት አስመልክቶ የዘንድሮው የሰብል ምርታማነት /Productivity/ ካለፈው ዓመት የሰብል ምርታማነት ጋር ሲነፃፀር የዚህ ዓመት ምርታማነት ይጨምራል የሚል መልስ ከባለይዞታው ከተገኘ በዓምድ 6 ኮድ «1» እኩል ይሆናል /ለውጥ የለውም/ የሚል መልስ ከተገኘ በዓምዱ ኮድ «2» ይቀንሳል የሚል መልስ ከተገኘ በዓምዱ ኮድ «3» ይሞላል ማለት ነው::

<u>ዓምድ 7</u> - የሚጨምር ከሆነ የሚጨምረው መጠን በመቶኛ

ይህ ዓምድ የሚሞላው በዓምድ 6 ኮድ «1» የተሞላ ከሆነ ብቻ ነው:: ካለፈው ዓመት ምርታማነት ጋር በማነፃፀር ባለይዞታው የዘንድሮው የሰብል ምርታማነት ይጨምራል የሚል ከሆነ ባለይዞታው የሚናገረው በመቶኛ በዚህ ዓምድ ውስጥ ይሞላል:: ለምሣሌ ባለይዞታው ለአንድ የሰብል ዓይነት የዚህ ዓመት የሰብል ምርታማነት ካለፈው ዓመት የሰብል

ምርታማነት ጋር ሲነፃፀር እጥፍ ይሆናል ካለ በዚህ ዓምድ ውስጥ «100» ይሞላል ማለት ነው፡፡

*ማሳሰቢያ፡-*

ምርትና ምርታማነትን ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ ባለፈው ዓመት አንድ ባለይዞታ ሁለት ጥማድ በቆሎ ዘርቶ 10 ቁና ቢያገኝና ዘንድሮ ደግሞ 1 ጥማድ ዘርቶ 8 ቁና አገኘለሁ ቢል በዚህ ምሳሌ ምርት ከ10 ወደ 8 ቁና ቢወርድ ምርታማነት ግን ከ5=(10/2) ወደ 8=(8/1) ቁና በጥማድ አደገ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በማንኛውም ምርታማነትን ሊያስጨምር በሚችል ምክንያት የተነሳ ምርታማነት 60 በመቶ =(8-5)/5X100 አደገ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ለዚህ ባለይዞታ በዓምድ 6 ኮድ «1» በዓምድ 7 ደግሞ 060 መጻፍ አለበት፡፡

## የምርታማነትን ለውጥ በመቶኛ የሚገልጹ መረጃዎችን ከባለይዞታው ከራሱ ለመሰብሰብ መረጃ ሰብሳቢው ከዚህ በታች በተሰጠው ምሳሌ የቀረበውን አሠራር ማጤን ይገባዋል

*ምሳሌ፡-* በ1996 ዓ.ም በሚካሄደው የሰብል ትንበያ ናሙና ጥናት በተመረጠ ቆጠራ ቦታ ለጥናት ከተመረጡ 25 ቤተሰቦች በመጀመሪያው የሚገኝ አንድ ባለይዞታ ከሌሎች ሰብሎች በተጨማሪ የበቆሎ ሰብልን በ5 ማሣዎች ላይ ዘርቶ ቡቃያው በሁሉም ማሣዎች ይታያል እንበል፡፡ በቆጠራ ቦታው የተመደበ መረጃ ሰብሳቢ ከላይ ወደ ተጠቀሰው ባለይዞታ በመሄድ የትንቢያ መረጃዎችን የመሰብሰብ ሥራ በበቆሎ ሰብል ከተያዙ ማሣዎች ይጀምራል፡፡ ለትንቢያ ስታቲስቲክስ ከሚያገለግሉ መረጃዎች ዋነኛው ሰብሉን በማስመልከት በአምናና በዘንድሮ ዓመት ሊኖር የሚችለውን የምርታማነት ለውጥ በመቶኛ የሚገለጽ መረጃዎችን መሰብሰብ ነው፡፡ ይህን መረጃ ለማግኘት መረጃ ሰብሳቢው የሚከተሉትን የአሠራር ዘዴዎች በሚገባ ተረድቶ ትክክለኛ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባል፡፡

1. አምና ማለትም (በ1995 ዓ.ም የሰብል ዘመን) የበቆሎ ሰብል ያመርት እንደነበር ይጠየቃል፡፡ ለዚህ ጥያቄ የባለይዞታው መልስ አዎን ከሆነ ወደ ቀጣይ ጥያቄዎች ይሸጋገራል፡፡ መልሱ አላመረትኩም ከሆነ ቀጣይ ጥያቄዎችን ከአካባቢው ሁኔታ ጋር በማገናዘብ እንዲመልስ ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡

2. መልሱ አዎ ከሆነ በሰብል ተይዞ የነበረውን ጠቅላላ የመሬት ስፋት በአካባቢ /በስታንዳርድ መለኪያ ምን ያህል እንደሆነ ይጠይቃል። ለዚህ ጥያቄ ባለይዞታው 10 ጥማድ ብሎ መልሶ ቢሆን።

3. በመቀጠልም ከአንድ ጥማድ ምን ያህል ምርት አግኝቶ እንደነበር ይጠይቃል (እዚህ ላይ ከ10 ጥማድ የተገኘውን ጠቅላላ የምርት መጠን አለመሆኑን ለባለይዞታው ማስረዳት ከመረጃ ሰብሳቢው ይጠበቃል) ለዚህ ጥያቄ መረጃ ሰጭው 6 ቁና ብሎ መልስ ቢሰጥ።

4. ዘንድሮ በዚሁ ሰብል ማለትም በበቆሎ የተያዘው መሬት ጠቅላላ ስፋት የአምናውን በገለጸበት ተመሳሳይ መለኪያ ስንት እንደሆነ ይጠየቃል። ለዚህ ጥያቄ የባለይዞታው መልስ 8 ጥማድ ቢሆን።

5. ዘንድሮ በበቆሎ ሰብል ከተሸፈነው አንድ ጥማድ መሬት ሊገኝ ይችላል ብሎ የሚገምተውን ምርት መጠን (የአምናውን የመሬት ስፋት ለመግለጽ በተጠቀመበት ተመሳሳይ መለኪያ) እንዲገልጽ ይጠየቃል። (እዚህ ላይ ባለይዞታው በዘንድሮ ዓመት ሊገኝ የሚችለውን የምርት መጠን የአምናውን ለመግለጽ በተጠቀመበት ተመሳሳይ መለኪያ ተጠቅሞ መግለጽ እንደሚገባው ማስታወስ ከመረጃ ሰብሳቢው ይጠበቃል) ለዚህ ጥያቄ ባለይዞታው የሰጠው መልስ 10 ቁና ነው።

6.. በመጨረሻም ተመሳሳይ የመሬት ስፋት ካላቸው የዘንድሮ (1996 ዓ.ም)ና የአምና (1995 ዓ.ም) የበቆሎ ሰብል ሊገኝ የሚችለውንና የተገኘውን በተመሳሳይ መለኪያ የተገለጸውን ምርት መጠን አወዳድሮ ልዩነቱን በመቶኛ ወይም ባለይዞታው ይህን ልዩነት ሊገልጽ በሚችልበት የአካባቢ መለኪያ ለምሳሌ በእጅ፣ በአሥረኛ ...ወዘተ አወዳድሮ እንዲገልጽ በማበረታታት በመረጃ ሰብሳቢው በሚደረግ ተደጋጋሚ ጥረት መረጃዎችን ከራሱ ከባለይዞታው ማግኘት ይቻላል።

መረጃ ሰብሳቢው ተደጋጋሚ ጥረት አድርጎ ከመልስ ሰጭው አመርቂ መልስ ማግኘት ካልቻለ ከላይ በቅደም ተከተል ከባለይዞታው ያገኛቸው መረጃዎችን የሚከተለውን ቀመር (ፎርሙላ) በመጠቀም የምርታማነት ለውጥ በመቶኛ

የሚገልጽ መረጃዎችን በማግኘት በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/2 ክፍል 2 በተገቢው ዓምድ ማስፈር ይጠበቅበታል።

$$\text{የምርታማነት ለውጥ በ መቶኛ} = \frac{\left(\text{በዘንድሮው ዓመት (በ1996 ዓ.ም) ከአንድ የአካባቢ/ ስታንዳርድ መለኪያ ስፋት ካለው መሬት ሊገኝ የሚችለው ምርት መጠን አካባቢ/ ስታንዳርድ መለኪያ}\right) - \left(\text{ዓምና (በ1995 ዓ.ም) ከአንድ የአካባቢ ስታንዳርድ መለኪያ ስፋት ካለው መሬት የተገኘ ምርት መጠን በአካባቢ/ ስታንዳርድ መለኪያ}\right)}{\left(\text{ዓምና (በ1995 ዓ.ም) ከአንድ የአካባቢ/ስታንዳርድ መለኪያ ስፋት መሬት የተገኘ የምርት መጠን በአካባቢ/ስታንዳርድ መለኪያ}\right)} \times 100$$

*ማስታወሻ:-*

1. በዘንድሮው (በ1996 ዓ.ም) እና በዓምናው (በ1995 ዓ.ም) የስፋት መጠኑ አንድ በሆነ የአካባቢ/ስታንዳርድ መለኪያ የሚገለፀው በሰብሉ የተሸፈነ መሬት ስፋት በሁለቱም ዓመት በተመሳሳይ መለኪያ ስም የተገለፀ መሆን አለበት ይህም ማለት ዓምና በጥማድ የተገለፀ ከሆነ ዘንድሮም በጥማድ መገለጽ ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ በቀመሩ የሚገኘው መረጃ ፍጹም የተሳሳተ ይሆናል።

2. በተመሳሳይ በዘንድሮው ዓመት (በ1996 ዓ.ም) ከላይ በተራ ቁጥር 1 በተጠቀሰው የአካባቢ/የስታንዳርድ መለኪያ ስፋቱ፡ አንድ ከሆነ መሬት ሊገኝ እንደሚችል የተገመተው የምርት መጠን አምና (በ1995 ዓ.ም) ተመሳሳይ ስፋት ካለው መሬት የተገኘው የምርት መጠን ከተገለጸበት የሚገልጽበት የአካባቢ/ስታንዳርም መለኪያ ተመሳሳይ መሆን ይኖርበታል። ይህም ማለት በዘንድሮው ዓመት መጠኑ አንድ ከሆነ የመሬት ስፋት ሊገኝ እንደሚችል የተገመተው ምርት በቁና የተገለፀ ከሆነ የዓምናውም በቁና መገለጽ ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ በቀመሩ የሚገኘው መረጃ ፍፁም የተሳሳተ ይሆናል።

ከላይ የቀረበውን ቀመር (ፎርሙላ) በመጠቀም የቀረበው ምሳሌ የምርታማነት ለውጥ በመቶኛ እንደሚከተለው ይሰላል።

የምርትማነት ለውጥ በመቶኛ=<u>10 ቁና/ጥማድ-6ቁና/ጥማድ</u>x100=<u>400=</u> 66.67 %

በዚህ ስሌት መሠረት ምርታማነት 66.67 በመቶ አደገ ማለት ነው:: ስለሆነም ለዚህ ባለይዞታ በዓምድ 6 ኮድ «1» በዓምድ 7 ደግሞ 067 መፃፍ ይኖርበታል ማለት ነው::

3. ከላይ 1-6 የተሰጡት ዝርዝር የአሠራር ዘዴዎች የቀረቡት መረጃ ሰብሳቢው በምርታማነት ጽንሰ-ሃሳብ ላይ ሰፋ ያለ ግንዛቤ ለማግኘት እንዲረዳው እንጂ በቅደም ተከተል የቀረቡትን አሠራሮች ለባለይዞታው በማቅረብ መረጃ ይሰበሰባል ለማለት አይደለም::

<u>ዓምድ 8-9</u> - <u>የሚቀንስ ከሆነ</u>

<u>ዓምድ 8</u> - <u>የሚቀንሰው መጠን በመቶኛ</u>

ይህ ዓምድ የሚሞላው በዓምድ 6 ኮድ «3» የተሞላ ከሆነ ብቻ ነው:: ካለፈው ዓመት ምርታማነት ጋር በማነፃጸር ባለይዞታው የዘንድሮ የሰብል ምርታማነት ይቀንሳል የሚል ከሆነ ባለይዞታው ለአንድ የሰብል ዓይነት የዚህ ዓመት ምርታማነት ካለፈው ዓመት ምርታማነት ጋር ሲነፃጸር በሲሦ ይቀንሳል ቢል በዚህ ዓምድ ውስጥ «033» ይሞላል ማለት ነው::

<u>ዓምድ 9</u> - የምርታማነት መቀነስ አንድ ዋና ምክንያት

ይህ ዓምድ የሚሞላው በዓምድ 6 ኮድ «3» የተሞላ ከሆነ ብቻ ነው:: በዚህ መሠረት ባለይዞታው ለሰብሉ ምርታማነት መቀነስ አንድ ዋና ምክንያት ነው የሚለው ተጠይቆ በዚህ ዓምድ ሥር ባለው ክፍት ቦታ ውስጥ ይፃፋል:: ለአንድ የሰብል ዓይነት ምርታማነት መቀነስ ከአንድ በላይ የሆኑ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ:: የሰብል ምርታማነት እንዲቀንስ የሚያደርጉ ዋና ዋና ምክንያቶችን በገጽ_ --70------በሠንጠረዥ 2 የቀረበውን ይመልከቱ::

<u>*ማስታወሻ:-*</u>

በዚህ ክፍል ዓምድ 6 ይቀንሳል ተብሎ ከተሞላ የምርታማነቱ መቀነስ ምክንያት በዚህ ዓምድ ሥር የግድ መሞላት ይኖርበታል::

<u>ዓምድ 10</u> - የተገኘው ለውጥ መጠን በመቶኛ

ይህ ዓምድ በዓምድ 6 ኮድ «1» ከተሞላ በዓምድ 7 በተሞላው መጠን ላይ መቶ በመደመር የተገኘው ውጤት የሚመዘገብበት ሲሆን በዓምድ 6 ኮድ «2» ከተሞላ ደግሞ በዚሁ ዓምድ 100 ይመዘገባል:: እንዲሁም በዓምድ 6 ኮድ «3» ከተሞላ ዓምድ 8 የተገለጸውን መጠን ከመቶ ላይ በመቀነስ የተገኘውን ውጤት በዚሁ ዓምድ ይመዘገባል::

ኮድ «3» ከተሞላ ዓምድ 8 የተገለጸውን መጠን ከመቶ ላይ በመቀነስ የተገኘውን ውጤት በዚሁ ዓምድ ይመዘገባል።

<u>ዓምድ 11</u> - <u>አስተያየት</u>

የዚህን ክፍል አሞላል በሚመለከት የገጠመ ችግር ወይም ለመረጃው ጥራት ጠቃሚ የሆነ አስተያየት ካለ በተሰጠው ክፍት ቦታ መግለጽ ይቻላል።

*<u>ማስታወሻ፡-</u>* የሰብል ትንበያ ናሙና ጥናት የሰብል ሁኔታ ግመገማ (የቅጽ 96/2) መረጃ የሚሰበሰበው ከመስከረም 20 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ መሆን እንዳለበት ማስታወስ ተገቢ ነው።

## የቅጽ ግ.ና.ፕ 96/5 - ለሰብል አጨዳ የማሣዎች መምረጫ አሞላል

በዚህ ቅጽ የሚሞላው ባለይዞታው ካሉት የሰብል ዓይነቶች ውስጥ አጨዳ በሚመለከታቸው ሰብሎች የተያዙ ማሣዎች ብቻ ከቅጽ ግ.ና.ፕ 96/3ሀ፣ ና 96/3ሐ በማስተላለፍ ይመዘገባሉ:: ምዝገባውም ከተከናወነ በኋላ ከእያንዳንዱ የሰብል ዓይነት አንድ ማሣ ለሰብል አጨዳ በራንደም የመምረጥ ተግባር በዚሁ ቅጽ ይከናወናል:: አጨዳ የሚከናወንላቸው ጊዜያዊ ሰብሎች በገጽ ተዘርዝረዋል:: በተጨማሪም በዚህ ቅጽ ላይ ምርጫ ከተደረገ በኋላ የተመረጠው ማሣ የሰብል አጨዳ ተደርጎለት ውጤቱ በቅጽ ግ.ና.ፕ 96/6 ይሞላል::

ክፍል 1. የአካባቢ መለያ

ዓምድ 1 - ክልል

ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 2 - ዞን

ጥናቱ የሚካሄድበት ዞን ስም ወይም ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 3 - ወረዳ

ጥናቱ የሚካሄድበት ወረዳ ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 4 - ገበሬ ማህበር

ጥናቱ የሚካሄድበት ገበሬ ማህበር ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 5 - ቆጠራ ቦታ

ጥናቱ የሚካሄድበት ቆጠራ ቦታ ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 6 - የቤተሰብ መለያ ቁጥር

የተመረጠው ቤተሰብ መለያ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ፕ 96/3ሀ ወይም 96/3ሐ በመውሰድ ይሞላል::

ዓምድ 7 - የባለይዞታው መለያ ቁጥር

የባለይዞታው መለያ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ፕ 96/3ሀ ወይም 96/3ሐ በመውሰድ ይሞላል::

ዓምድ 8 - የባለይዞታው ስም

ለ ጥናቱ የተመረጠው ባለይዞታ ስም ከቅጽ ግ.ና.ፕ 96/3ሀ ወይም 96/3ሐ በመውሰድ በዚህ ዓምድ ይመዘገባል::

ዓምድ 9 - ዕድሜ

የባለይዞታው ዕድሜ ተጠይቆ በሙሉ ዓመት በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 10 - ፆታ (ወንድ = 1 ሴት = 2)

የባለይዞታው ፆታ ወንድ ከሆነ ኮድ «1» ሴት ከሆነች ኮድ «2» በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 11 - የትምህርት ሁኔታ (የፈጸሙት ከፍተኛ ክፍል)

በዚህ ዓምድ የባለይዞታው የትምህርት ሁኔታ (የፈፀሙት ከፍተኛ ክፍል) ተጠይቆ ይሞላል:: ማብራሪያውን በገጽ 29 እና 30 ይመልከቱ

ዓምድ 12 - የባለይዞታው የቤተሰብ አባላት ብዛት

የባለይዞታው የቤተሰብ አባላት ብዛት ተጠይቶ በዚህ ዓምድ ውስጥ ይሞላል:: በተጨማሪም በተመረጠው ቤተሰብ ውስጥ ከአንድ በላይ ባለይዞታ ካለ የቤተሰብ አባላት ብዛት በሚጠየቅበት ጊዜ ብዛት ለእያንዳንድ ባለይዞታ ተደጋግም ይሞላል::

ዓምድ 13 - የግብርናው ዓይነት

ይህ ዓምድ ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሀ ወይም 96/3ሐ ክፍል 1 ዓምድ 13 በመውሰድ ይመዘገባል::

## ክፍል 2. ለሰብል አጨዳ የማሣዎች መምረጫ

ዓምድ 1 - የፓርሰል ቁጥር

ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሆ ና 96/3ሐ የተመዘገቡትና የሰብል አጨዳ የሚመለከታቸው የሰብል ዓይነቶች የሚገኙባቸው ማሣዎችን የያዙት ፓርሰሎች በሙሉ ቁጥራቸው በትክክል ወደዚህ ቅጽ ይገለበጣል:: ወደዚህ ቅጽ የሚተላለፉ የፓርሰል ቁጥሮች የሰብል አጨዳ እንደሚደረግላቸው በዚህ መመሪያ በገጽ 16 የተዘረዘሩትን ሆ:ሸ:ሐ ሰብሎችን ብቻ ይመለከታል::

ዓምድ 2 - የማሣ ቁጥር

በተመሣሣይ ሁኔታም ከላይ በተገለጸው መሠረት አጨዳ የሚካሄድላቸው የሰብል ዓይነቶች የሚገኙባቸው ማሣዎች ቁጥር ከ ግ.ና.ጥ 96/3ሆ ና 96/3ሐ በቀጥታ በማስተላለፍ ይመዘገባሉ::

ዓምድ 3 - ማሣው የያዘው

በዓምድ 2 ላይ የተመዘገበው ማሣ የያዘው ጊዜያዊ ሰብል ብቻ ከሆነ ኮድ «1» ፣ ድብልቅ ከሆነ ኮድ «2» ፣ ይሞላል::

ዓምድ 4 - የሰብሉ ስም

ባለይዞታው ካስመዘገባቸውና በሰብል ከተያዙ ማሣዎች ውስጥ በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሀ ና 96/3ሐ የሰብል አጨዳ የሚመለከታቸው ሰብሎች (ጊዜያዊና ድብልቅ ሰብሎች) በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ስማቸው ይሞላል:: በዚህ ዓምድ ለኮድ የተተወው ቦታ ምንም አይሞላበትም::

ዓምድ 5-24 - የሰብሉ ስም

በእነዚህ ዓምዶች ውስጥ ጊዜያዊ ለሆኑት የሰብል ዓይነቶች ስም መጻፊያ ክፍት ቦታዎች ተዘጋጅተዋል:: በተሰጡት ክፍት ቦታዎች በዓምድ 4 የሰብል ዓይነቶች አመዘጋገብ ቅደም ተከተል መሠረት የሰብሎች ስም ከዓምድ 5-24 ባለው ክፍት ቦታ ይዘረዘራል:: ቀጥሎም የማሣው ተራ ቁጥር በሚለው ዓምድ በተሰጠው ቦታ በዓምድ 4 ከተዘረዘሩት በአንድ ዓይነት ሰብል የተያዙ ማሳዎች ከ01 በመጀመር ተራ ቁጥር ይሰጣቸዋል:: ከላይ በተሰጠው ክፍት ቦታ መጻፍ ያለበት የአንድ ሰብል ስም ብቻ መሆኑ መዘንጋት የለበትም ማሣዎች በሰብል ዓይነት ተለይተው ተራ ቁጥር ከተሰጣቸው በኋላ የራንደም ቁጥሮች ሠንጠረዥ /Random Table/ በመጠቀም ከእያንዳንዱ የሰብል ዓይነት አንድ ማሣ ብቻ ለሰብል አጨዳ ይመረጣል የተመረጠው የማሣ ቁጥርም በተገቢው ቦታ ላይ ይሞላል:: በዓምድ 5፣ 7፣ 9፣ 11፣ 13፣ 15፣ 17፣ 19፣ 21 ና 23 የተመረጡ ማሣ ተራ ቁጥሮች ይከበባሉ:: በአንጻሩም በእነዚህ በተከበቡት ቁጥሮች አኳያ በዓምድ 2 የተዘረዘሩት የማሣ ቁጥሮችም ይከበባሉ:: ዓምድ 6፣ 8፣ 10፣ 12፣ 14፣ 16፣ 18፣ 20፣ 22 ና 24 ደግሞ በዓምድ 2 የተከበቡት ቁጥሮች በቀጥታ ይተላለፋሉ /ይጻፋሉ:: አንድ የሰብል ዓይነት ያለው አንድ ማሣ ብቻ ከሆነ ይኸው ማሣ ለሰብል አጨዳ በቀጥታ ይመረጣል::

*ማስታወሻ:*

1. *በዚህ ቅጽ በክፍል 2 ለሰብል አጨዳ ለተመረጡ ማሣዎች የሰብል አጨዳ ውጤታቸው በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/6 ክፍል 2 ይመዘገባል::*
2. *የአመራረጡን ሁኔታ በይበልጥ ለመረዳት በሚቀጥለው ገጽ የቀረበውን ምሳሌ እንዲሁም ዝርዝር ማብራሪያውን መመልከትና ማጥናት ያስፈልጋል::*

ለሰብል አጨዳ የማሣ አመራረጥ

ለግብርና ናሙና ጥናት ከተመረጡት በግብርና የሚተዳደሩ ቤተሰቦች ውስጥ ባሉት ባለይዞታዎች ሥር ካሉት ማሣዎች ከእያንዳንዱ ጊዜያዊ የሰብል ዓይነት አትክልትና ሥራ ሥርን ሣይጨምር ለሰብል አጨዳ አንዳንድ ማሣ ይመረጣል::

የማሣ አመራረጡ ሁኔታ በዝርዝር እንደሚከተለው ይሆናል

ሀ. በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/5 በክፍል 2 በዓምድ 4 አጨዳ የሚመለከታቸው ጊዜያዊና ድብልቅ ሰብሎች በሙሉ በዓምድ 1 እና 2 የፓርሰልና የማሣ ተራ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሆ፣ ና 96/3ሐ ተላልፎ ይመዘገባል::

ለ. ከዓምድ 5 እስከ 24 «የሰብሉ ስም» በሚለው ርዕስ ሥር አስር ክፍት ቦታዎች ተሰጥተዋል። በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/5 ክፍል 2 ዓምድ 4 የተዘረዘሩት የሰብል ዓይነቶች በሙሉ በእነዚህ ክፍት ቦታዎች ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ይመዘገባሉ። የተሰጡት ክፍት ቦታዎች አስር የተለያዩ የሰብል ስሞችን ብቻ ለመጻፍ የሚያስችሉ ስለሆነ ከዚህ ቁጥር በላይ በዓምድ 4 የተመዘገቡ የሰብል ዓይነቶች ካሉ የቅጹን ጀርባ መጠቀም ያስፈልጋል።

ሐ. በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/5 በዓምድ 5፣ 7፣ 9፣ 11፣ 13፣ 15፣ 17፣ 19፣ 21ና 23 በተጻፉት የሰብል ዓይነቶች ለተያዙ ማሣዎች ለእያንዳንዳቸው ከ01 በመጀመር ተራ ቁጥር ከተሰጠ በኋላ ለሰብል አጨዳ በሚከተለው ሁኔታ ማሣ ይመረጣል።

1. ባለይዞታው በአንድ የሰብል ዓይነት የተያዙ ከአንድ በላይ ማሣዎች ካሉት ባለአንድ ቤት የራንደም ሠንጠረዥ በመጠቀም ከአንድ በላይ ከሆኑት ማሣዎች ውስጥ አንድ ማሣ ብቻ ለሰብል አጨዳ ይመረጣል።

2. ባለይዞታው በአንድ የሰብል ዓይነት የተያዘ አንድ ማሣ ብቻ ካለው ይህ ማሣ <u>በቀጥታ</u> ለሰብል አጨዳ ይመረጣል።

3. በተሰጠው *መመሪያ መሠረት* ለሰብል አጨዳ የተመረጡ ማሣዎች ተራ ቁጥር በዓምድ 5፣ 7፣ 9፣ 11፣ 13፣ 15፣ 17፣ 19፣ 21 ና 23 መከበብ አለበት። በእነዚህ በተከበቡት ማሣዎች ተራ ቁጥር አኳያ በዓምድ 2 የሚገኘው የማሣ ቁጥር በተመሳሳይ ሁኔታ ተከቦ ወደ ዓምድ 6፣ 8፣ 10፣ 12፣ 14፣ 16፣ 18፣ 20፣ 22 ና 24 ይተላለፋል። በአቅጣጫው የሚገኘው የፓርሰል፣ ማሣ ቁጥርና የሰብል ስም በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/6 በተገቢው ዓምድ መሞላት አለበት።

## <u>ለሰብል አጨዳ የማሣዎች አመራረጥ ምሣሌ</u>

በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሀ እና 96/3ሐ ላይ ክፍል 2 ከዓምድ 3 - 10 ምሳሌ ሆነው እንዲያገለግሉ የጊዜያዊ፣ የጊዜያዊና የጊዜያዊ፣ የጊዜያዊና ቋሚ ሰብሎች የሚገኙባቸው ድብልቅ ማሣዎች ተሰጥተዋል። ስለዚህ ለማሣዎች አመዘጋገብና ለሰብል አጨዳ ማሣዎች አመራረጥ እንዲረዳ ከዚህ በታች የተሰጠውን ማብራሪያ በደንብ ማጥናት ያስፈልጋል።

ሀ. ከዓምድ 5-24 ያለው ቦታ በአንድ ቅጽ አሥር የሰብል ዓይነቶች መፃፊያ ስለሆነ ከአስር በላይ የሰብል ዓይነት ሲያጋጥም በጀርባው ያለውን መጠቀም ያስፈልጋል። በምሣሌው እንደሚታየው በገጽ ባለይዞታው ያሉት 12 የሰብል

ዓይነቶች ስለሆነ አሥሩን የሰብል ዓይነቶች (በቆሎ፣ ሽንኩርት፣ ጤፍ፣ ቡና፣ ማሽላ፣ ቲማቲም፣ ብርቱካን፣ ገብስ፣ ስንዴ፣ ጫት፣) በመጀመሪያ ቅጽ ከዓምድ 5-24 በቅደም ተከተል የተሞሉ ሲሆን የተቀሩት ሁለቱ (ኅመንና ቃሪያ) በቅጹ ጀርባ ከዓምድ 25-28 ባለው ቦታ እንደቅደም ተከተላቸው ተሞልተዋል።

ለ. በምሳሌ እንደሚታየው በበቆሎ የተያዙ 3 ማሣዎች አሉ። ከእነዚህም ውስጥ ባለ አንድ ቤት የራንደም ሠንጠረዥ /Random Table/ በመጠቀም ከሦስቱ ማሣዎች አንደኛው በራንደም ለሰብል አጨዳ ይመረጣል። በዚህ ምሣሌ ራንደሙ በሦስተኛው ተራ ቁጥር ባለው የድብልቅ ማሳ ላይ ቢወድቅ ራንደሙን በመቀየር ከድብልቅ ካልተያዙት ሁለቱ ማሳዎች አንዱን መምረጥ ያስፈልጋል። ስለዚህም በአንደኛ ተራ ቁጥር የተመዘገበው ቢደርሰው በፓርሰል 01 ማሳ 01 የተመዘገበው ማሳ ተመረጠ ማለት ነው።

ሐ: ጤፍን አስመልክቶ ሁለት ማሳዎች ስላሉ ከሁለቱ አንዱን በራንደም መምረጥ ያስፈልጋል። ስለዚህም ራንደሙ በተራ ቁጥር ሁለት ላይ ቢወድቅ ፓርሰል 03 ማሳ 02 ተመረጠ ማለት ነው።

መ. በቡናና ማሽላ እንዲሁም በበቆሎና ማሽላ ድብልቅ ሰብሎች ከተያዙት ማሳዎች በማሽላ የተያዘ ሌላ ማሳ ባለመኖሩ በቡናና በማሽላ ድብልቅ የተያዘው ማሳ በቀጥታ በማሽላው ይመረጣል።

ሠ. በገብስና በስንዴ ድብልቅ የተያዘው ማሳ ለገብሱ ተመርጧል። ይህ ሊሆን የሚችለው ድብልቆቹ ከያዙት የመሬት ስፋት በአብዛኛው የቱ ሰብል እንደያዘ በመጠየቅ ለአብላጫ ለያዘው ሰብል ምርጫው በመስጠቱ ነው። ሆኖም ግን ሁለቱም ስፋታቸው እኩል ከሆነ በአካባቢው በአብዛኛው ለሚመረተው ሰብል ምርጫው ይወሰዳል።

ረ. ዓምድ 5፣ 7፣ 9፣ 11፣ 13፣ 15፣ 17፣ 19፣ 21ና 23 ለአጨዳ የተመረጡት የተለያዩ ማሳዎች ይከበቡና በእነዚህ ዓምዶች ከተከበቡት ማሳዎች አኳያ በዓምድ 2 የሚገኙት የማሳ ቁጥሮች ይከበባሉ። ወደ ዓምድ 6፣ 8፣ 10፣ 12፣ 14፣ 16፣ 18፣ 20፣ 22 ና 24 ደግሞ በዓምድ 2 የተከበቡት ቁጥሮች በቀጥታ ይተላለፋሉ። ከዚያ በኋላ በዓምድ 2 የማሳ ቁጥራቸው ለተከበቡት ማሳዎች የሰብል አጨዳ በተሰጠው መመሪያ መሠረት ተካሂዶ ውጤቱ ለየሰብሉ ዓይነት በተዘጋጁት ቅጾች ውስጥ ይሞላል።

ቅጽ ግ.ና.ጥ 96/5

# የኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ጥናት
## የአጨዳ ውጤት ዝርዝር - ለጊዜያዊ ሰብሎች /1996 ዓ.ም/

ክፍል - 1 የአካባቢ መለያ

| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ክልል | ዞን | ወረዳ | ገበሬ ማህበር | ቆጠራ ቦታ | የቤተሰብ መለያ ቁጥር | የባለይዞታ መለያ ቁጥር | የባለይዞታው ስም | ዕድሜ | ፆታ ወንድ → 1 ሴት → 2 | የትምህርት ሁኔታ የፈጸሙት ከፍተኛ ክፍል ኮድ | የባለይዞታው የቤተሰብ አባላት ብዛት | የግብርናው ዓይነት ሰብል → 1 ከብት → 2 ሁለቱም → 3 |
| አማራ | ሰሜን ሸዋ | ቀወት | [illegible] | 02 | 002 | 01 | [illegible] | 43 | 1 | 03 | 05 | 3 |

ክፍል 2 - የማሳዎች ዝርዝር፤ ለሰብል አጨዳ የማሳዎች መምረጫ

| 1 | 2 | 3 | 4 | | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | 24 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | የ ሰ ብ ሉ ስ ም | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | በቆሎ | | ጤፍ | | ማሽላ | | ገብስ | | ስንዴ | | | | | | | | | | | |
| የፓርስል ቁጥር | የማሳው ቁጥር | ማሳው የያዘው ** | የሰብሉ ስም * | ኮድ | የማሳው ተ/ቁጥር | የተመረጠው ማሳ ቁጥር | የማሳው ተ/ቁጥር | የተመረጠው ማሳ ቁጥር | የማሳው ተ/ቁጥር | የተመረጠው ማሳ ቁጥር | የማሳው ተ/ቁጥር | የተመረጠው ማሳ ቁጥር | የማሳው ተ/ቁጥር | የተመረጠው ማሳ ቁጥር | የማሳው ተ/ቁጥ | የተመረጠው ማሳ ቁጥር | የማሳው ተ/ቁጥር | የተመረጠው ማሳ ቁጥር | የማሳው ተ/ቁጥር | የተመረጠው ማሳ ቁጥር | የማሳው ተ/ቁጥር | የተመረጠው ማሳ ቁጥር | የማሳው ተ/ቁጥ | የተመረጠው ማሳ ቁጥር |
| 01 | 01 | 1 | በቆሎ | | (01) | 01 | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 01 | 03 | 1 | ጤፍ | | | | 01 | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 01 | 04 | 2 | ቡናና ማሽላ | | | | | | 01 | | | | | | | | | | | | | | | |
| 02 | 04 | 1 | በቆሎ | | 02 | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 03 | 01 | 2 | ገብስና ስንዴ | | | | | | | | (01) | 01 | 01 | | | | | | | | | | | |
| 03 | 02 | 1 | ጤፍ | | | | (02) | 02 | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 04 | 01 | 2 | በቆሎና ማሽላ | | 03 | | | | (02) | 01 | | | | | | | | | | | | | | |

* ኂሊያዊ → 1
ድብልቅ → 2

ድብልቅ ሰብሎች ሲያጋጥም

1. ሁለት ሰብሎች አማራጭ ማሣዎች ካላቸው የጋራቸው የሆነውን የድብልቁን ማሣ ከምርጫ አስወግደን ለሁለቱ ሰብሎች ምርጫ በተቀሩት ማሣዎች እናካሂዳለን። ለምሳሌ ባለይዞታው አንድ የጤፍ ማሣ፣ ሁለት የበቆሎ ማሣዎች፣ አንድ የጤፍና የበቆሎ ድብልቅ ማሣ ቢኖረው ለጤፍ በጤፍ ብቻ የተያዘው ማሣ በቀጥታ ለሰብል አጨዳ ይመረጣል በቆሎ ደግሞ ከሁለቱ በበቆሎ ብቻ ከተያዙ ማሣዎች አንዱ በራንደም ተመርጦ የሰብል አጨዳ ይካሂድለታል። በዚህም መሠረት በጤፍና በበቆሎ ድብልቅ የተያዘው ከምርጫው ተወገደ ማለት ነው።

2. ከሁለት ሰብሎች አንደኛው ሰብል ከድብልቁ ማሣ የተለየ አማራጭ ማሣ ካለውና ሌላው ሰብል ድብልቁን ማሣ ብቻ ከያዘ ለአንደኛው ሰብል አማራጩ ማሣ ተመርጦ ለሌላው የድብልቁ ማሣ ይመረጣል። ምሣሌ ባለይዞታው አንድ የገብስ ማሣና አንድ ሌላ በገብስና በስንዴ ድብልቅ የተያዘ ማሣ ቢኖረው እነዚህን ሰብሎች በተመለከተ ለገብስ፣ በገብስ ብቻ የተያዘው ማሣ ለስንዴ ደግሞ በድብልቁ የተያዘው ማሣ በቀጥታ ለሰብል አጨዳ ይመረጣሉ።

3. ሁለቱም ሰብሎች የድብልቅ ማሣ ብቻ ካላቸው ከሁለቱ ሰብሎች የያዘው የመሬት ስፋት በበለጠው ሰብል ስም ምረጫው ይደረጋል። እኩል በእኩል ከሆኑ ግን በቆጠራ ቦታው በአብዛኛው በሚመረተው ሰብል ስም ምርጫው ይደረጋል። ለምሳሌ ባለይዞታው ገብስና ስንዴን በተመለከተ አንድ የሁለቱ ሰብሎች ድብልቅ ማሣ ብቻ ካለው ከሁለቱ ሰብሎች የያዘው የመሬት ስፋት በዛ ባለበት ሰብል ምርጫው ይደረጋል። ሆኖም የማሳ ድርሻው እኩል ከሆነ በቆጠራ ቦታው በብዛት በሚመረተው ሰብል ስም ማሣው ለሰብል አጨዳ ይመረጣል።

ማሳሰቢያ:-

ሀ. በግብርና ናሙና ጥናት መጀመሪያ ወቅት በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሀ፣ 96/3ለ፣ 96/3ሐ እና 96/3መ ላይ ማሣዎች ከተመዘገቡ በኋላ ባለይዞታዎች በተለያየ ምክንያት በማሣዎቻቸው ላይ የሰብል ዓይነት ወይም የማሣ ስፋት /መጠን/ ለውጥ የሚያደርጉበት ሁኔታ ሊያጋጥም ስለሚችል ለውጡን እየተከታተሉ አስፈላጊውን መረጃ መሙላት ያስፈልጋል።

ምሣሌ:- ባለይዞታው በመጀመሪያው የዘር ወቅት በአንድ ማሣ ላይ ጤፍ ዘርቶ መረጃ ሰብሳቢውም ማሣውን ከለካና አንዳንድ ተፈላጊ መረጃዎችን ከሰበሰበ በኋላ በተለያየ ምክንያት /በተባይ፣ በዝናብ ... ወዘተ/ ጤፉ ቢጠፋ ወይም ቢበላሽ ይህን ማሣ ገልብጦ እንደገና በማረስ ሌላ የሰብል ዓይነት ወይም ከአንድ በላይ

የሆነ የሰብል ዓይነት ማሣውን በመከፋፈል ሊዘራበት ይችላል:: በመሆኑም መረጃ ሰብሳቢው ለሰብል አጨዳ ሲሄድ በጤፍ ፈንታ ሌላ የሰብል ዓይነት ወይም ዓይነቶች በማሣው ላይ ሊያገኝ ይችላል:: በዚህን ጊዜ ለጤፍ የተሞላው እንዳለ ሆኖ አዲስ ለተዘራው/ሩት ሰብሎች አስፈላጊው መረጃ በተገቢ ቅጾች ተከታታይ የማሳ ቁጥር በመስጠት እንደሚሞሉ መገንዘብ ያስፈልጋል::

ለ. በግብርና ናሙና ጥናት ወቅት በአንዳንድ አካባቢ በመኸር ሰብል መሰብሰቢያ ወቅት በአንድ ማሣ ከአንድ ጊዜ በላይ ምርት መሰብሰብ ሊያጋጥም ይችላል:: ይህ ሁኔታ ባለበት አካባቢ መረጃ ሰብሳቢው ተከታታይ የማሣ መለያ ቁጥር በመስጠትና ተገቢውን አስተያየት በመግለጽ የሰብል አጨዳውንና የማሣ ልኪውን ይህ ሁኔታ ባጋጠመበት ማሣ ላይ ወቅቱን እየጠበቀ ማከናወን ይኖርበታል: በሌላ አነጋገር ይህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም የማሣ ልክቶሽም ሆነ የሰብል አጨዳው ከአንድ ጊዜ በላይ መካሄድ አለበት ማለት ነው::

ሐ. ለሰብል አጨዳ ከተመረጠው ማሣ ላይ የሚገኘው ሰብል በአንዳንድ ምክንያቶች ጠፍቶ የሰብል አጨዳ ሳይካሄድ ቢቀር ማሣው በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/5 ክፍል 2 ብቻ ተመዝግቦ መቅረት አይኖርበትም:: ለሰብል አጨዳ ውጤት መመዝገቢያ በተዘጋጀው ቅጽ ማለትም በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/6 አስፈላጊው መረጃ ተመዝግቦ በውጤት መመዝገቢያው ቦታ /0/ መሞላት ይኖርበታል:: በተጨማሪም በአስተያየት ዓምድ ላይ የሰብል መበላሸት ደርሷል ወይ በሚለው ዓምድ ውስጥ የብልሽቱ ምክንያትና መጠን መገለጽ ይኖርበታል::

መ. ለሰብል አጨዳ የተመረጠ ሰብል ቀድሞ ከታጨደ ወይም በእሸትነቱ ከተበላ ለሰብል አጨዳ ውጤት መመዝገቢያ በተዘጋጁት ቅጾች አስፈላጊው መረጃ ተመዝግቦ የምርት ውጤት መመዝገቢያ ቦታ በሠረዝ (-) ይታለፋል::

## ለሰብል አጨዳ የማሣ አካል /Plot/ አዘገጃጀትና የአጨዳ ውጤት አመዘጋገብ መመሪያ

4 ሜትር x 4 ሜትር የሆነ የማሳ አካል በተመረጠው ማሣ ላይ ስለማዘጋጀት (በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሀ ና 96/3ሐ ለተመዘገቡት ጊዜያዊና ድብልቅ ሰብሎች ብቻ

በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/3ሀ ና 96/3ሐ ከተመዘገቡት በጊዜያዊ ሰብሎችና ድብልቃቸው ከቲያዙ ማሳዎች ውስጥ በሰብል ዓይነት አንድ ማሳ በመምረጥና 4 ሜትር x 4

ሜትር የሆነ የማሳ አካል /Plot/ በራንደም በማዘጋጀት ሰብሉን በማጨድ፣ በመውቃት፣ በማድረቅና በመመዘን የተገኘውን ውጤት በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/6 ክፍል 2 ላይ በትክክል መመዝገብ ያስፈልጋል:: የሰብል አጨዳ የሚካሄድበት የማሳ አካል /Plot/ በሚከተለው አኳኋን በማሣው ላይ ይዘጋጃል::

ሀ/ መረጃ ሰብሳቢው በመጀመሪያ በተመረጠው ማሣ ዙሪያውን በመዞርና ዋና ዋና የማሳው ማዕዘናትን ይለያል:: በመቀጠልም ወደ ማሳው እንብርት በመግባት ኮምፓስ ተጠቅሞ ወደ ሰሜናዊ ምዕራብ የሚቀርበውን የማሣውን ማዕዘን ይመረጣል:: ይህም በምሳሌው ማዕዘን "A" ተብሎ የተሰየመወውን ማለት ነው::

ለ. መረጃ ሰብሳቢው ማዕዘን "A" ላይ በመቆም ከዚህ ማዕዘን የሚነሱ ሁለት የማሣው ጎኖችን ይለያል:: ይህም በምሳሌው AB እና AF ተብለው የተሰየሙት የማሣው ጎኖች ይሆናሉ:: ቀጥሎ ከሁለቱ ጎኖች ረጅሙ AB መሆኑንና አጭሩ ደግሞ AF መሆኑን በማየት ወይም በመለካት ያረጋግጣል::

ሐ. ከ "A" ማዕዘን በመነሳት ረጅሙን የማሣ ጎን ማለትም የAB ን ርዝመት በሜትር ይለካል:: በምሳሌው እንደሚታየው የAB ርዝመት 40 ሜትር ነው:: ይህንኑ ርዝመት በማስታወሻ ከመዘገበ በኋላ የራንደም ቁጥሮች ሠንጠረዥ በመጠቀም የAB ርዝመትን ማለትም ከ40 ሜትር እኩል የሆነ ወይም ያነሰ ቁጥርን በመፈለግ በመጀመሪያ የተገኘውን ቁጥር ይመዘግባል:: በምሳሌው መሠረት ከራንደም ቁጥሮች ሠንጠረዥ የተገኘው ቁጥር 10 ነው::

መ. ከላይ በ "ሐ" በሜትር ተለክቶ የተገኘውን የማሳውን ረጅምና አጭር ጎን መሠረት በማድረግ ወደማሳው ለመግባት የሚያስችለውን ቦታ ለማግኘት የራንደም ቁጥሮች ሠንጠረዥ (Random Number Table) መጠቀም ያስፈልጋል:: ባለስንት ቤት ራንደም ሠንጠረዥ መጠቀም እንደሚያስፈልግ የሚወስኑት ከላይ በሐ በሜትር ተለክተው የተገኙት የረጅምና አጭር ጎን መጠኖች ናቸው:: ስለዚህ የራንደም ሠንጠረዥን በመጠቀም አንድ የራንደም ቁጥር ለረጅሙና አንድ ሌላ የራንደም ቁጥር ደግሞ ለአጭሩ ጎን ከላይ በሜትር ተለክቶ ከተገኘው መጠን ያልበለጠ መምረጥ ያስፈልጋል::


ሠ./ በመቀጠልም ለሰብል አጨዳ የማሳ አካል /Plot/ መነሻ ነጥብ ለማግኘት የሚከተሉትን በቅደም ተከተል ማከናወን ያስፈልጋል::

በማሣው መነሻ ማዕዘን (Corner Point "A") ላይ በመቆምና ፊትን ወደ ረጅሙ ጎን በማዞር በራንደም የተገኘውን ቁጥር መጠን ያህል በሜትር መለካትና ችካል መትከል ከዚያም ከዚሁ ቦታ ላይ ሆኖ ፊትን ወደ ማሳው ውስጥ በማዞር በኮምፓስ የአጭሩን ጎን ቤሪንግ በማንበብ ለአጭሩ ጎን በራንደም የተገኘውን ቁጥር መጠን ያህል በሜትር ወደ ማሣው ውስጥ መግባትና ቦታው ላይ ችካል መትከል ይህንንም «a» ብሎ መሰየም።

<u>*ማስታወሻ:*</u>


*በራንደም ሠንጠረዥ የተገኙትን ሁለት የረጅሙና አጭሩ ጎን ራንደም ቁጥሮች ተጠቅመን ያገኘነው ራንደም ነጥብ በማሣው ቅርጽ ምክንያት በማሣ ውስጥ ካልወደቀ በራንደም የተገኙት የርዝመትና የወርድ ራንደም ቁጥሮች በመተው ሌላ ሁለት አዲስ የረጅሙና አጭሩ ጎን ቁጥሮች እንደገና በራንደም መምረጥ ያስፈልጋል። እነዚህንም የረጅሙና አጭሩ ጎን ቁጥሮች በመጠቀም አዲስ የፕሎት መነሻ የሚሆን የራንደም ነጥብ ይገኛል።*

<u>ለሰብል አጨዳ የማሣ አካል / PLOT/ አዘገጃጀት ምሣሌ</u>



ሜትር x 4 ሜትር የማሣ አካል /Plot/ አዘገጃጀት

4 ሜትር x 4 ሜትር የሆነውን የማሣ አካል በማሳው ላይ ለማዘጋጀት 16 ሜትር የሆነ ገመድና አራት ችካሎች ያስፈልጋሉ:: በገመዱም ሁለት ጫፎች ላይ ቀለበቶች መኖር አለባቸው:: ቀጥሎ የቀረበውን 4ሜ x 4ሜ የሆነውን ምስል ለመጠቀም ይቻላል::




ሀ. ማሣው ውስጥ «a» ተብሎ ችካል ከተተከለበት ቦታ ላይ ፊትን ወደ ምሥራቅ አዙሮ በመቆም በኮምፓስ 90 ዲግሪ በማንበብ በዚሁ አቅጣጫ ከ«a» 4 ሜትር መለካትና ችካል መትከል:: ይህም በምሣሌው መሠረት «b» ይባላል::

ለ. «b» ላይ ፊትን ወደ ሰሜን አዙሮ በመቆም በኮምፓስ 360 ወይም 0 ዲግሪ ይነበባል:: በዚሁ አቅጣጫ ከ«b» በመነሳት 4 ሜትር ለክቶ ሁለተኛውን ችካል መትከል:: ይህም በምሣሌው መሠረት «c» ይባላል::

ሐ. «c» ላይ ፊትን ወደ ምዕራብ አዙሮ በመቆም በኮምፓስ 270 ዲግሪ ይነበባል:: በዚሁ አቅጣጫ ከ«c» በመነሳት 4 ሜትር ለክቶ ሌላ ሦስተኛ ችካል መትከል:: ይህም በምሣሌው መሠረት «d» ይባላል::

መ. «d» ላይ ፊትን ወደ ደቡብ አዙሮ በመቆም በኮምፓስ 180 ዲግሪ ይነበባል:: በዚሁ አቅጣጫ ከ«d» በመነሳት 4 ሜትር ይለካና በገመድ ጫፍ ላይ ያለው ቀለበት በትክክል መነሻ ከነበረው ከ«a» ላይ ካለው ችካል መግጠም አለበት:: ይህ ካልሆነ የቤሪንግ ወይም የርዝመት ልኪ ስህተት ሊኖር ስለሚችል እንደገና መለካት ያስፈልጋል::

የማሣው አካል /Plot/ በትክክል 4 ሜትር x 4 ሜትር መሆኑን ለማወቅ የማሣው አካል አግዳሚ ጎን /Diagonal /ac/ በምሳሌው መሠረት/ በመለካት 5.66 ሜትር መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: አጨዳው በዚህ 4 ሜትር x 4 ሜትር በሆነው የማሣ አካል ውስጥ መሆን ይኖርበታል:: ሰብሉ ታጭዶ ከተወቃ በኋላ በትክክል መመዘን አለበት:: ትክክለኛውን መረጃ ለማስፈር እንዲረዳ ልዩ መለያዎች ማለትም የባለይዞታው ስም የፓርስልና የማሣ መለያ ቁጥሮችን እንዲሁም የሰብሉን ስም በአንድ ወረቀት ላይ በመፃፍ በከረጢቱ ውስጥ መቀመጥ አለበት:: የታጨደው ሰብል ከተመዘነ በኋላ ክብደቱ በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/6 በክፍል 2 ዓምድ 5 ውስጥ መመዝገብ ይኖርበታል:: ከማሣው ላይ ታጭዶና ተወቅቶ ወዲያው የተመዘነ ሰብል እርጥበት ስለሚኖረው የሰብሉን ትክክለኛ ክብደት ለማግኘት ቢያንስ ለ15 ቀናት በፀሐይ መድረቅ አለበት:: ሰብሉ በትክክል መድረቁን ለማረጋገጥ ከ15 ቀን በኋላ ክብደቱ ተደጋግሞ ከተመዘገበ በኋላ ለውጥ ሳያሳይ ሲቀር የተገኘው ውጤት በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/6 ክፍል 2 ዓምድ 7 ይመዘገባል::

*ማስታወሻ፡-*

*የታጨደውና የተወቃው ሰብል እንዳይፋሰስ አይጥና ወፍ እንዳይበላው በጥንቃቄ መያዝ እንዳለበት እንዲሁም አስፈላጊው መረጃ ተሞልቶ ከተጠናቀቀ በኋላ ሰብሉ ለባለይዞታው መመለስ እንዳለበት ማስታወስ ያስፈልጋል::*

## የቅጽ ግ.ና.ጥ 96/6 - የአጨዳ ውጤት ዝርዝር፡ ለጊዜያዊ ሰብል አሞላል

ይህ ቅጽ በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/5 ለሰብል አጨዳ የተመረጡ የጊዜያዊ ሰብል (አትክልትና ሥራሥር ሰብሎችን አይጨምርም) ማሣዎች ዝርዝር የሚተላለፍበትና የአጨዳ ውጤት የሚመዘገብበት ነው:: በዚህ ቅጽ የአጨዳ ውጤት የሚመዘገበው ለጊዜያዊ ሰብል ማለትም ብርዕና አገዳ፣ ጥራጥሬና የቅባት ሰብሎች ብቻ መሆኑን መገንዘብ ይገባል::

ክፍል 1. የአካባቢ መለያ

ዓምድ 1 - ክልል

ጥናቱ ቆጠራው የሚካሄድበት ክልል ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 2 - ዞን

ጥናቱ የሚካሄድበት ዞን ስም ወይንም ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 3 - ወረዳ

ጥናቱ የሚካሄድበት ወረዳ ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 4 - ገበሬ ማህበር

ጥናቱ የሚካሄድበት ገበሬ ማህበር ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 5 - የቆጠራ ቦታ

ጥናቱ የሚካሄድበት ቆጠራ ቦታ ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 6 - የቤተሰብ መለያ ቁጥር

የተመረጠው ቤተሰብ መለያ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/5፡ ክፍል 1 ዓምድ 6 በመውሰድ ይሞላል::

ዓምድ 7 - የባለይዞታው መለያ ቁጥር

የባለይዞታው መለያ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/5፡ ክፍል 1 ዓምድ 7 በመውሰድ ይሞላል::

ዓምድ 8 - የባለይዞታው ስም

የባለይዞታው ስም ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/5፡ ክፍል 1 ዓምድ 8 በመውሰድ በዚህ ዓምድ ይመዘገባል::

ዓምድ 9 - ዕድሜ

የባለይዞታው ዕድሜ ተጠይቆ በሙሉ ዓመት በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 10 - ፆታ (ወንድ = 1 ሴት = 2)

የባለይዞታው ፆታ ወንድ ከሆነ ኮድ «1» ሴት ከሆነች ደግሞ ኮድ «2» ይሞላል::

ዓምድ 11 - የትምህርት ሁኔታ (የፈጸሙት ከፍተኛ ክፍል)

በዚህ ዓምድ የባለይዞታው የትምህርት ሁኔታ (የፈፀሙት ከፍተኛ ክፍል) ተጠይቆ ይሞላል:: ማብራሪያውን በገጽ 29 እና 30 ይመልከቱ

ዓምድ 12 - የባለይዞታው የቤተሰብ አባላት ብዛት

የባለይዞታው የቤተሰብ አባላት ብዛት ተጠይቶ በዚህ ዓምድ ውስጥ ይሞላል:: በተጨማሪም በተመረጠው ቤተሰብ ውስጥ ከአንድ በላይ ባለይዞታ ከለ የቤተሰብ አባላት ብዛት በሚጠየቅበት ጊዜ ብዛት ለእያንዳንድ ባለይዞታ ተደጋግም ይሞላል::

ዓምድ 13 - የግብርና ዓይነት (ሰብል = 1 ከብት = 2 ሁለቱም = 3)

ባለይዞታው የግብርናውን ዓይነት ተጠይቆ ሰብል ማምረት ከሆነ ኮድ 1 ከብት ማርባት ከሆነ ኮድ 2 ሁለቱም ከሆነ ኮድ 3 በዓምድ 13 ይሞላል::

## ክፍል 2. የሰብል አጨዳ ውጤት ዝርዝር - ለጊዜያዊ ሰብሎች (አትክልትና ሥራሥር ሰብሎችን አይጨምርም)

ይህ ክፍል የሚያገለግለው አትክልትና ሥራሥርን ሳይጨምር ለጊዜያዊ ሰብሎች ብቻ የሰብል አጨዳ ውጤት በሰብል ዓይነት ለመመዝገብ ነው:: በቅጽ ግ.ና.ጥ 96/5 ክፍል 2 ለሰብል አጨዳ የማሣ ምርጫ ከተጠናቀቀ በኋላ የተመረጡ በጊዜያዊ ሰብል የተያዙ ማሳዎች የየራሳቸውን መለያ ማለትም የፓርስልና የማሣ ቁጥር እንዲሁም ማሣው የያዘውን ሰብል ስም በመያዝ በቀጥታ ወደዚህ ክፍል ይተላለፋሉ:: አጨዳ የሚካሄደውም በተመረጠው ማሣ ላይ በአንድ 4 ሜትር በ4 ሜትር በሆነ የማሣው አካል /Plot/ ላይ ነው::

ዓምድ 1 - የፓርስል ቁጥር

የፓርስሉ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/5 ክፍል 2 ዓምድ 1 በማወራረስ ይሞላል::

ዓምድ 2 - የማሣ ቁጥር

የማሣው ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/5 ክፍል 2 ዓምድ 2 በማወራረስ ይሞላል::

ዓምድ 3 - የሰብሉ ስም

ለሰብል አጨዳ በተመረጠው ማሣ ላይ የሚገኘው ሰብል ስም ከቅጽ 96/5 ክፍል 2 ዓምድ 4 ተወስዶ ይሞላል:: ለኮድ የተተወው ቦታ ለቢሮ ሥራ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም::

ዓምድ 4 - አጨዳ የተካሄደበት ቀንና ወር

16 ስኴየር ሜትር በሆነው የማሣው አካል ላይ የሰብል አጨዳ የተካሄደበት ቀንና ወር ይመዘገባል::

ዓምድ 5 - ሰብሉ እንደታጨደ ተወቅቶ /ተፈልፍሎና ተመዝኖ ክብደቱ

4ሜትር በ4ሜትር (16 ስኴየር ሜትር) ከሆነው የማሣ አካል ላይ የታጨደው ሰብል እንደተወቃ/እንደተፈለፈለ ተመዝኖ ክብደቱ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ውስጥ ይሞላል። እንደተወቃ ሲባል ለምሳሌ እንደ ባቄላና አተር ዓይነት ሰብሎች ገለባው ከፍሬው ከተለየ በኋላ ሲሆን እንደ በቆሎና አቾሎኒ ያሉ ደግሞ ከተፈለፈሉ በኋላ መሆኑ መታወቅ አለበት።

ዓምድ 6 - ሰብሉ ደርቆ የተመዘነበትና የተመዘገበበት ቀንና ወር

ሰብሉ ከደረቀ በኋላ የተመዘነበት ቀንና ወር ይሞላል።

ዓምድ 7 - የደረቀው ሰብል ተመዝኖ ክብደቱ

የደረቀው ሰብል ተመዝኖ ክብደቱ በኪሎ ግራምና በግራም ማለት የመጀመሪያው ክብደት ከተወሰደ ከሁለት ሳምንት በኋላ በየጊዜው ተመዝኖ ምንም ለውጥ ሳያሳይ ሲቀር የተገኘው ክብደት ይመዘገባል።

ዓምድ 8-10 - የሰብል መበላሸት ደርሷል ወይ?

ዓምድ 8 - አዎ = 1 የለም = 2

የሰብል መበላሸት መድረስ አለመድረሱ ባለይዞታው ተጠይቆ ብልሽት ካለ ኮድ «1» ሲሞላ ከሌለ ደግሞ ኮድ «2» ይሞላል። ይህ ዓምድ በአጨዳ ወቅት ለአጨዳ በተመረጠው ማሣ ላይ የሚገኘው ሰብል የደረሰበትን የብልሽት መጠንና ዓይነት በተመለከተ የሚጠየቅበት ነው።

*ማሳሰቢያ:-*

*የሰብል ብልሽት የሚጠየቀው በአጠቃላይ በማሣው ላይ ላለው /ለነበረው/ሰብል መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።*

ዓምድ 9 - መልሱ አዎን ከሆነ ለብልሽቱ አንድ ዋና ምክንያት

ይህ ዓምድ የሚሞላው በዓምድ 8 ብልሽት አለ ተብሎ ኮድ «1» የተሞላ እንደሆነ ብቻ ነው። ስለዚህ በዓምድ 8 ኮድ «1» ከተሞላ በዓምድ 9 በተሰጠው ክፍት ቦታ አንድ ዋና የሰብል ብልሽት ምክንያት ይጻፋል። ለሰብል ብልሽት ዋና ዋና ምክንያቶችን በገጽ 19 ይመልከቱ። ለኮድ የተተወው ቦታ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም።

ዓምድ 10 - የተበላሸው መጠን በመቶኛ

ይህ ዓምድ የሚሞላው በዓምድ 8 አዎ ተብሎ ኮድ «1» ተሞልቶ ከሆነ ብቻ ነው። በዚህ ዓምድ በብልሽት የጠፋው ሰብል መጠን በመቶኛ ባለይዞታው ተጠይቆ መገለጽ አለበት።

ዓምድ 11 - ማሣው የያዘው ሰብል (አንድ ዓይነት = 1፣ ድብልቅ = 2)

በዚህ ቅጽ ክፍል 2 ዓምድ 2 የሰብል አጨዳ የተካሄደበት ማሣ ላይ የነበረው ሰብል አንድ ዓይነት ከነበረ ኮድ «1»፣ ድብልቅ ሰብል ከነበረ ኮድ «2» ይሞላል።

## የቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/7 የቤት እንስሳት፡ ንብ የያዙ ቀፎዎች ብዛትና የተዋጽዖ ምርት አሞላል

ይህ ቅጽ በቆጠራ ቦታው ለጥናቱ በተመረጡ ቤተሰቦች ውስጥ ለሚገኙ ባለይዞታዎች በሙሉ የቤት እንስሳት፡ ንብ የያዙ ቀፎዎች፡ የወተት የዕንቁላል የማር ምርት መጠን የቤት እንስሳትን በሽታና የመኖ አጠቃቀምን አስመልክቶ የሚሞላ ነው:: የቤት እንስሳትና ዶሮዎች ጥናት የሚደረገው የካቲት 2/1996 ጀምሮ እስከ የካቲት 8/1996 ባለው ጊዜ ውስጥ ሲሆን ጥናቱ የሚመለከታቸው የካቲት 1/1996 የነበሩትን የቤት እንስሳት ነው:: በተጨማሪም በባለይዞታው ቁጥጥር ሥር ሆነው በጥናቱ ወቅት በተለያዩ ምክንያቶች ከቤት የሌሉ (በመንገድ ላይ ያሉ ወይም ለምግብ ፍለጋ ወደ ሌላ የሄዱ) የቤት እንስሳት በባለይዞታው ስም ጥናት ይደረግላቸዋል:: አንድ የቤት እንስሳ በጋራ ከአንድ በላይ በሆኑ ባለይዞታዎች ቁጥጥር ሥር ከሆነ የቤት እንስሳው በሚገኝበት/በሚኖርበት ባለይዞታ ይመዘገባል:: የቤት እንስሳትን ብዛት አስመልክቶ መረጃ ሰብሳቢው ባለይዞታውን በሚጠይቅበት ጊዜ ከጠቅላላ ብዛታቸው በመጀመር መጠየቅ ይኖርበታል::

ክፍል 1. የአካባቢ መለያ

ዓምድ 1 - ክልል

ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 2 - ዞን

ጥናቱ የሚካሄድበት ዞን ስም ወይንም ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 3 - ወረዳ

ጥናቱ የሚካሄድበት ወረዳ ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 4 - ገበሬ ማህበር

ጥናቱ የሚካሄድበት ገበሬ ማህበር ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 5 - የቆጠራ ቦታ

ጥናቱ የሚካሄድበት ቆጠራ ቦታ ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 6 - የቤተሰብ መለያ ቁጥር

የተመረጠው ቤተሰብ መለያ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ጥ. 96/1 ክፍል 2 ዓምድ 1 በመውሰድ በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 7 - የባለይዞታው መለያ ቁጥር

በቤተሰቡ ውስጥ የሚገኘው የባለይዞታው መለያ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ፐ. 96/1 ክፍል 2 ዓምድ 3 በመውሰድ በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 8 - የባለይዞታው ስም

የባለይዞታው ስም ከቅጽ ግ.ና.ፐ. 96/1 ክፍል 2 ዓምድ 4 በመውሰድ በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 9 - ዕድሜ

የባለይዞታው ዕድሜ ተጠይቆ በሙሉ ዓመት ይሞላል።

ዓምድ 10 - ፆታ (ወንድ = 1 ሴት = 2)

የባለይዞታው ፆታ ወንድ ከሆነ ኮድ«1» ሴት ከሆነች ደግሞ ኮድ «2» በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 11 - የትምህርት ሁኔታ የፈፀሙት ከፍተኛ ክፍል (አምስት ዓመትና በላይ ለሆኑ ባለይዞታዎች)

በዚህ ዓምድ ዕድሜያቸው 5 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ ባለይዞታዎች የትምህርት ሁኔታ (የፈፀሙት ከፍተኛ ክፍል) ተጠይቆ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ኮዶች ትክክለኛው ተመርጦ ይሞላል። በመጀመሪያ ባለይዞታው ማንበብና መፃፍ የሚችል መሆኑ ከተጠየቀ በኋላ የሚችል ከሆነ ተምሮ የጨረሰው ከፍተኛ ክፍል ይጠየቃል። አንድ ግለሰብ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ አለው የሚባለው በማንኛውም ግለሰቡ በሚያውቀው ቋንቋ አንብቦ መረዳትና መፃፍ ሲችል ብቻ ነው። የራሳቸውን ስም ወይንም ቁጥሮችን ብቻ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ግለሰቦች እንደተማሩ አይቆጠሩም። በተጨማሪም የፈፀመው ክፍል ሲባል በጥናቱ ወቅት የሚገኝበት ክፍል ሳይሆን ተምሮ የጨረሰው ከፍተኛ ክፍል ማለት ነው።

ለትምህርት ደረጃ የተሰጡ ኮዶች:-

| | | |
|---|---|---|
| መፃፍና ማንበብ የማይችሉ | ኮድ | 01 |
| መደበኛ ያለሆነ ትምህርት | » | 02 |
| 1ኛ ክፍል ያጠናቀቀ | » | 03 |
| 2ኛ ክፍል ያጠናቀቀ | » | 04 |
| 3ኛ ክፍል ያጠናቀቀ | » | 05 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 4ኛ | ክፍል ያጠናቀቀ | » | 06 |
| 5ኛ | ክፍል ያጠናቀቀ | » | 07 |
| 6ኛ | ክፍል ያጠናቀቀ | » | 08 |
| 7ኛ | ክፍል ያጠናቀቀ | » | 09 |
| 8ኛ | ክፍል ያጠናቀቀ | » | 10 |
| 9ኛ | ክፍል ያጠናቀቀ | » | 11 |
| 10ኛ | ክፍል ያጠናቀቀ | » | 12 |
| 11ኛ | ክፍል ያጠናቀቀ | » | 13 |
| 12ኛ | ክፍል ያጠናቀቀ | » | 14 |
| ከ12ኛ | ክፍል በላይ | » | 15 |

*ማስታወሻ:-*

*አንዳንድ ጊዜ ባለይዞታው የልጆች ወይም የእናቶች ናቸው በሚል በቤተሰቡ ውስጥ ያሉትን የቤት እንስሳት፣ ዶሮዎች ወይም ንብ የያዙ ቀፎዎችን በትክክል ላያስመዘግብ ይችልና በቆጠራው ላይካተቱ ይችላሉ:: ስለዚህ ይህ ሁኔታ እንዳይጋጥም ግልፅ አድርጎ በመጠየቅ በቤተሰቡ ውስጥ ያሉት የቤት እንስሳት ዶሮዎችና ንብ የያዙ ቀፎዎች በሙሉ መቁጠር ያስፈልጋል::*

ዓምድ 12 - የባለይዞታው የቤተሰብ አባላት ብዛት

የቤተሰብ አባላት ብዛት ምን ያህል እንደሆነ ተጠይቆ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ውስጥ ይሞላል::

ዓምድ 13 - የግብርና ዓይነት (ሰብል = 1 ከብት = 2 ሁለቱም = 3)

ባለይዞታው የሚያካሂደው የግብርና ዓይነት ተጠይቆ ሰብል ማምረት ከሆነ ኮድ «1» ከብት ማርባት ከሆነ ኮድ «2» ሁለቱም ከሆነ ኮድ «3» በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ውስጥ ይሞላል::

## ክፍል 2:- የቤት እንስሳት፣ ንብ የያዙ ቀፎዎችና የተዋጽዖ ምርት መጠን

ጥያቄ I:- የካቲት 1 /1996 የቤት እንስሳት ነበረዎት?

(አዎን = 1 አልነበረኝም = 2)

የባለይዞታው መልስ አዎን ከሆነ በተሰጠው ሣጥን ውስጥ ኮድ «1» በመሙላት መጠይቁን ማጠናቀቅ ያስፈልጋል:: አልነበረኝም ከሆነ ግን በተሰጠው ሣጥን ውስጥ ኮድ «2» በመሙላት ወደ ገጽ 4 በማለፍ ጥያቄ «II» ይጠየቃል::

### የዳልጋ ከብቶች ብዛት በጾታ ፣ በዕድሜና በአገልግሎት (የካቲት 1/1996 የነበሩትን )

ጥያቄ 1:- ጠቅላላ የዳልጋ ከብቶች ብዛት

የካቲት 1/1996 ዓ.ም ባለይዞታው የነበሩት ጠቅላላ የዳልጋ ከብቶች እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ለየብቻ በመጠየቅ በአንፃሩ ባሉት ባዶ ቦታዎች ውስጥ ይሞላሉ::

ሀ) ከ6 ወር በታች

በጥያቄ 1 ከተመዘገቡት ጠቅላላ የዳልጋ ከብቶች ውስጥ ዕድሜያቸው ከ6 ወር በታች የሆኑት ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴትን ብዛት ለየብቻ ባለይዞታውን በመጠየቅ ባሉት ባዶ ቦታዎች ይመዘገባሉ::

ለ) 6 ወርና ከ1 ዓመት በታች

በጥያቄ 1 ከተመዘገቡት ጠቅላላ የዳልጋ ከብቶች ውስጥ ዕድሜያቸው 6 ወርና ከ1 ዓመት በታች የሆኑትን ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴትን ብዛት ለየብቻ ባለይዞታውን በመጠየቅ በአንፃሩ ባሉት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ::

ሐ) 1 ዓመትና ከ3 ዓመት በታች

በጥያቄ 1 ከተመዘገቡት ጠቅላላ የዳልጋ ከብቶች ውስጥ ዕድሜያቸው 1 ዓመትና ከ3 ዓመት በታች የሆኑትን ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴትን ብዛት ለየብቻ ባለይዞታውን በመጠየቅ በአንፃሩ ባሉት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ::

መ) 3 ዓመትና ከ10 ዓመት በታች

በጥያቄ 1 ከተመዘገቡት ጠቅላላ የዳልጋ ከብቶች ውስጥ ዕድሜያቸው 3 ዓመትና ከ10 ዓመት በታች የሆኑትን ጠቅላላ ብዛት እንዲሁም የወንድና የሴትን ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በአንጻሩ በተሰጡት ቦታዎች ይመዘገባሉ:: በተጨማሪም በ'' መ '' የተመዘገበው የቀንድ ከብቶች ብዛት የ''መ1 '' የ''መ2'' የ''መ3'' የ''መ5 '' እና የ''መ6 '' ድምር መሆኑን ማገናዘብ ያስፈልጋል::

መ1) የሥጋ

በ''መ'' ከተመዘገቡት ዕድሜያቸው 3 ዓመትና ከ10 ዓመት በታች ከሆኑት የዳልጋ ከብቶች ውስጥ ለዕርድ /ለሥጋ/ የሚውሉት ጠቅላላና በፆታ በመለየት ብዛታቸው በተሰጡት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ:: የሥጋ ከብቶች ሲባል ባለይዞታው ለራሱ የሥጋ ፍጆታም ሆነ የሥጋ ከብት ነው ብሎ በማሰብ ለሽያጭ ያዘጋጀውን ወይም የሚያቀርበውን የሚያጠቃልል ነው::

መ2) የእርባታ

በ" መ " ከተመዘገቡት ዕድሜያቸው 3 ዓመትና ከ10 ዓመት በታች ከሆኑት የዳልጋ ከብቶች ውስጥ ለእርባታ የሚውሉ ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ:: እርባታ ሲባል ባለይዞታው እንዲባዙለት በማሰብ ያስቀመጣቸው ሴትም ሆነ ወንድ የዳልጋ ከብቶችን ያጠቃልላል::

መ3) የወተት ላሞች

በ''መ'' ከተመዘገቡት ዕድሜያቸው 3 ዓመትና ከ10 ዓመት በታች ከሆኑት የዳልጋ ከብቶች ውስጥ የወተት ላሞች ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ ይሞላል:: የወተት ላሞች በጥናቱ ወቅት ወተት እየሰጡ የነበሩትንː ወደፊት ሊሰጡ የሚችሉትንና ክበድ /እርጉዝ የሆኑትን ጊደሮች ያጠቃልላል::

መ4) <u>ባለፉት 12 ወራት ወተት የሰጡ ላሞች ብዛት</u>

በ"መ3" ከተመዘገቡት ውስጥ ባለፉት 12 ወራት (ከየካቲት 2/1995 - የካቲት 1/1996 ድረስ) ስንት ላሞች ወተት እንደሰጡ ተጠይቆ ይመዘገባል።

መ5) <u>የእርሻ</u>

በ"መ" ከተመዘገቡት ዕድሜያቸው 3 ዓመትና ከ10 ዓመት በታች ከሆኑት የዳልጋ ከብቶች ውስጥ ባለይዞታው በአብዛኛው ለእርሻ ሥራ የሚጠቀምባቸው በጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ ባሉት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ። በእርሻ ሥራ ላይ ሴት የዳልጋ ከብቶችም ሊሰማሩ ስለሚችሉ ለሁለቱም ፆታዎች መረጃው መጠየቅ ይኖርበታል። በተጨማሪም የእርሻ ሥራ ማረስን፣ መጠቅጠቅን፣ መውቃትን፣ ሌሎች ለእርሻ አጋዥ ሥራዎችን እንደሚያጠቃልል መገንዘብ ያስፈልጋል።

መ6) <u>ለሌላ አገልግሎት</u>

በ"መ" ከተመዘገቡት ዕድሜያቸው 3 ዓመትና ከ10 ዓመት በታች ከሆኑት የዳልጋ ከብቶች ውስጥ ከላይ ከተገለፁት / ለሥጋ ÷ለእርባታ÷ ለወተትና ለእርሻ ሥራ/ ከሚውሉት ውጭ ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ ካሉ ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ ይመዘገባል።

*<u>ማስታወሻ:-</u>*

*ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ ተብለው ከሚመዘገቡት ውስጥ ክበድ ወይም እርጉዝ ያልሆኑ ጊደሮች ይጠቃለላሉ። ለሌላ አገልግሎት የሚውሉት ግልጋሎታቸው መገለጽ ይኖርበታል።*

ሠ) 10 ዓመትና  በላይ

በጥያቄ 1 ከተመዘገቡት ጠቅላላ የዳልጋ ከብቶች ውስጥ ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ የሆኑት ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጡት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ::

ረ) ጠቅላላ ብዛት

ባለይዞታው ያለው ጠቅላላ የዳልጋ ከብት እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በአንጻሩ በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይሞላል:: ይህም ጠቅላላ ብዛት የ"ሀ" የ"ለ"፣ የ"ሐ" ፥ የ"መ" ና የ"ሠ" ወይም የ"ረ1" ፥ የ "ረ2" ና የ"ረ3" ድምር ውጤት መሆኑንና በጥያቄ 1 ላይ ከተሞላው ጋር እኩል መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ረ1) ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ዝርያ

ባለይዞታው ብዛታቸውን በ"ረ" ካስመዘገባቸው የዳልጋ ከብቶች ውስጥ ያልተዳቀሉ ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በአንጻሩ በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ውስጥ ይሞላሉ::

ረ2) ጠቅላላ የውጭ ዝርያ

ባለይዞታው ቁጥራቸውን በ"ረ" ካስመዘገባቸው የዳልጋ ከብቶች ውስጥ የውጭ ዝርያ የሆኑ ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴትን ብዛት በመለየት ባለይዞታው ተጠይቆ በአንጻሩ በተሰጡት ቦታዎች ውስጥ ይሞላሉ::

ረ3) ጠቅላላ የተዳቀሉ

ባለይዞታው ቁጥራቸውን በ"ረ" ካስመዘገባቸው የዳልጋ ከብቶች ውስጥ የተዳቀሉ ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በአንጻሩ በተሰጡት ቦታዎች ውስጥ ይሞላሉ::

*ማስታወሻ:-*

1) *የወንድና የሴት ድምሩ በአንጻራቸው ከተመዘገበው ጠቅላላ ብዛት ጋር እኩል መሆን ይኖርበታል።*

2) *ጥያቄ 1= ሀ + ለ + ሐ + መ + ሠ*

3) *መ = መ1 + መ2 + መ3 + መ5 + መ6*

4) *ረ = ሀ + ለ + ሐ + መ + ሠ = ረ1 + ረ2 + ረ3 መሆኑን ማገናዘብ ያስፈልጋል።*

## የበጎች ብዛት በጾታ ፣ በዕድሜና በአገልግሎት (የካቲት 1/1996 የነበሩትን)

### ጥያቄ 2:- ጠቅላላ የበጎች ብዛት

የካቲት 1/1996 ዓ.ም ባለይዞታው የነበሩት ጠቅላላ የበጎች እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በአንጻሩ ባሉት ባዶ ቦታዎች ውስጥ ይሞላሉ።

#### ሀ) ከ6 ወር በታች

በጥያቄ 2 ከተመዘገቡት ጠቅላላ በጎች ውስጥ ዕድሜያቸው ከ6 ወር በታች የሆኑት ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በአንጻሩ በተሰጡት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

#### ለ) 6ወርና ከ1ዓመት በታች

በጥያቄ 2 ከተመዘገቡት ጠቅላላ በጎች ውስጥ ዕድሜያቸው 6 ወርና ከ1 ዓመት በታች የሆኑት ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

#### ሐ) 1 ዓመትና ከ2 ዓመት በታች

በጥያቄ 2 ከተመዘገቡት ጠቅላላ በጎች ውስጥ ዕድሜያቸው 1 ዓመትና ከ2 ዓመት በታች የሆኑት ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

መ) 2 ዓመትና በላይ

በጥያቄ 2 ከተመዘገቡት ጠቅላላ በጎች ውስጥ ዕድሜያቸው 2ዓመትና በላይ የሆኑት ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል:: በተጨማሪም በ«መ» የተመዘገበው የበጎች ብዛት የ«መ1» ÷ የ«መ2» ÷ የ«መ3» እና የ«መ4» ድምር መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

መ1) የሥጋ

ዕድሜያቸው 2 ዓመትና በላይ ከሆኑት ውስጥ ለሥጋ የሚውሉ በጎች ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ::

መ2) የፀጉር

ዕድሜያቸው 2 ዓመትና በላይ ከሆኑት ውስጥ ለፀጉር ምርት የሚውሉ በጎች ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ውስጥ ይሞላሉ::

መ3) የእርባታ

ዕድሜያቸው 2 ዓመትና በላይ ከሆኑት ውስጥ ለእርባታ የሚውሉ በጎች ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ውስጥ ይሞላል:: እርባታ ሲባል ባለይዞታው እንዲራቡ በማሰብ ያስቀመጣቸውን ሴትም ሆነ ወንድ በጎች ያጠቃልላል::

መ4) ለሌላ አገልግሎት

2 ዓመትና በላይ ከሆኑት በጎች ውስጥ ከላይ ከተጠቀሱት ውጭ ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ ካሉ ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ውስጥ ይሞላል:: የአገልግሎቱ ዓይነት መገለጽ እንደሚገባው ማስታወስ ያስፈልጋል::

ሠ) <u>ጠቅላላ የበጎች ብዛት</u>

ባለይዞታው ያለው ጠቅላላ የበጎች እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ተጠይቆ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ውስጥ ይሞላል:: ይህም ጠቅላላ ብዛት የ«ሀ» የ «ለ» የ «ሐ» ና የ"መ" ወይም የ"ሠ1" የ"ሠ2" ና የ"ሠ3" ድምር ውጤት መሆኑንና በጥያቄ 2 ላይ ከተሞላው ጋር እኩል መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ሠ1) <u>ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ዝርያ</u>

ባለይዞታው ቁጥራቸውን በ«ሠ» ካስመዘገባቸው በጎች ውስጥ የሀገር ውስጥ ዝርያ የሆኑ ጠቅላላ በጎች እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጠው ባዶ ቦታ ውስጥ ይመዘገባል::

ሠ2) <u>ጠቅላላ የውጭ ዝርያ</u>

ባለይዞታው ቁጥራቸውን በ«ሠ» ካስመዘገባቸው በጎች ውስጥ የውጭ ዝርያ የሆኑ በጎች ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጠው ባዶ ቦታ ውስጥ ይመዘገባል።

ሠ3) <u>ጠቅላላ የተዳቀሉ</u>

ባለይዞታው ቁጥራቸውን በ«ሠ» ካስመዘገባቸው በጎች ውስጥ የተዳቀሉ ጠቅላላ የበጎች እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይመዘገባል::

<u>*ማስታወሻ:-*</u>

*1) የወንድና የሴት ድምር በአንጻሩ ከተመዘገበው ጠቅላላው ብዛት ጋር እኩል መሆን ይኖርበታል::*

*2) ጥያቄ 2= ሀ + ለ + ሐ + መ*

*3) መ = መ1 + መ2 + መ3 + መ4*

*4) ሠ = ሀ + ለ + ሐ + መ = ሠ1 + ሠ2 + ሠ3*

*መሆኑን ማገናዘብ ያስፈልጋል::*

## የፍየሎች ብዛት በጾታ ፣ በዕድሜና በአገልግሎት (የካቲት 1/1996 የነበሩትን)

ጥያቄ 3፡- ጠቅላላ የፍየሎች ብዛት

የካቲት 1/1996 ዓ.ም ባለይዞታው የነበሩት ጠቅላላ የፍየሎች እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይመዘገባል፡፡

ሀ) ከ6 ወር በታች

በጥያቄ 3 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ፍየሎች ውስጥ ዕድሜያቸው ከ6 ወር በታች የሆኑት ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይመዘገባል፡፡

ለ) 6 ወርና ከ1 ዓመት በታች

በጥያቄ 3 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ፍየሎች ውስጥ ዕድሜያቸው 6 ወርና ከ1 ዓመት በታች የሆኑት ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይመዘገባል፡፡

ሐ) 1 ዓመትና ከ2 ዓመት በታች

በጥያቄ 3 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ፍየሎች ውስጥ ዕድሜያቸው 1 ዓመትና ከ2 ዓመት በታች የሆኑት ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይመዘገባል፡፡

መ) 2 ዓመትና በላይ

በጥያቄ 3 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ፍየሎች ውስጥ ዕድሜያቸው 2 ዓመትና በላይ የሆኑት ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይመዘገባል፡፡ በተጨማሪም በ«መ» የተመዘገበው የፍየሎች ቁጥር የ«መ1»፡ የ«መ2»፡ የ«መ3» ና የ«መ4» ድምር መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

መ1) <u>የሥጋ</u>

ዕድሜያቸው 2 ዓመትና በላይ ከሆኑት ውስጥ ለሥጋ የሚውሉ ፍየሎች ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይመዘገባል::

መ2) <u>የወተት</u>

ዕድሜያቸው 2 ዓመትና በላይ ከሆኑት ውስጥ ባለይዞታው ወተት ይሰጡኛል ብሎ ያስቀመጣቸው ፍየሎች ብዛት በተሰጠው ባዶ ቦታ ይመዘገባል::

መ3) <u>የእርባታ</u>

ዕድሜያቸው 2 ዓመትና በላይ ከሆኑት ውስጥ ለእርባታ የሚውሉ ፍየሎች ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይመዘገባል:: እርባታ ሲባል ባለይዞታው እንዲባዙለት በማሰብ ያስቀመጣቸውን ሴትም ሆነ ወንድ ፍየሎችን ያጠቃልላል::

መ4) <u>ለሌላ አገልግሎት</u>

2 ዓመትና በላይ ከሆኑት ፍየሎች ውስጥ ከላይ ከተጠቀሱት ውጭ ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ ካሉ ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ:: የአገልግሎቱም ዓይነት በአስተያየት መልክ መገለጽ ይኖርበታል::

ሠ) <u>ጠቅላላ የፍየሎች ብዛት</u>

ባለይዞታው ያለው ጠቅላላ የፍየሎች እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ተጠይቆ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይመዘገባል:: ይህም ጠቅላላ ብዛት የ"ሀ" "የ" ለ "የ" "ሐ" ና የ "መ" ወይም የ"ሠ1" የ"ሠ2" እና የ"ሠ3" ድምር ውጤት መሆኑንና በተራ ቁጥር 3 ላይ ከተሞላው ጋር እኩል መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ሠ1) <u>ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ዝርያ</u>

ባለይዞታው ብዛታቸውን በ"ሠ" ካስመዘገባቸው ፍየሎች ውስጥ የሀገር ውስጥ ዝርያ የሆኑ ያልተዳቀሉ ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

ሠ2) <u>ጠቅላላ የውጭ ዝርያ</u>

ባለይዛታው ብዛታቸውን በ"ሠ" ካስመዘገባቸው ፍየሎች ውስጥ የውጭ ዝርያ የሆኑ ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት በተሰጠው ክፍት ቦታ ውስጥ ይሞላል።

ሠ3) <u>ጠቅላላ የተዳቀሉ ዝርያ</u>

ባለይዞታው ቁጥራቸውን በ"ሠ" ካስመዘገባቸው ፍየሎች ውስጥ የተዳቀሉ ጠቅላላ እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ውስጥ ይሞላል።

*<u>ማስታወሻ:</u>*

*1) የወንድና የሴት ድምር በአንጻሩ ከተመዘገበው ጠቅላላ ብዛት ጋር እኩል መሆን ይኖርበታል።*

*2) ጥያቄ 3 = ሀ + ለ + ሐ + መ*

*3) መ = መ1 + መ2 + መ3 + መ4*

*4) ሠ = ሀ + ለ + ሐ + መ = ሠ1 + ሠ2 + ሠ3 መሆኑን ማገናዘብ ያስፈልጋል።*

<u>የፈረሶች፣አህዮች፣ በቅሎዎችና ግመሎች ብዛት በጾታ ፣ በዕድሜና በአገልግሎት (የካቲት 1/1996 የነበሩትን)</u>

<u>ጥያቄ 4:-</u> <u>የፈረሶች ብዛት</u>

የካቲት 1/1996 ዓ.ም ባለይዞታው የነበሩት ጠቅላላ የፈረሶች ብዛት እንዲሁም በፆታ በመለየት በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

ሀ) ከ3 ዓመት በታች

በጥያቄ 4 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ፈረሶች ውስጥ ዕድሜያቸው ከሶስት ዓመት በታች የሆኑት ጠቅላላ ብዛት እንዲሁም በፆታ ተለይተው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

ለ) 3 ዓመትና በላይ

በጥያቄ 4 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ፈረሶች ውስጥ ዕድሜያቸው ሦስት ዓመትና በላይ የሆኑት ጠቅላላ ብዛት እንዲሁም በፆታ በመለየት በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

ለ1) የእርሻ

ብዛታቸው በ«ለ» ከተመዘገበው ፈረሶች ውስጥ ባለይዞታው አብዛኛውን ጊዜ ለእርሻ ሥራ የሚጠቀምባቸው ጠቅላላ ብዛትና እንዲሁም በፆታ ተለይተው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

ለ2) የትራንስፖርት

ብዛታቸው በ«ለ» ከተመዘገበው ፈረሶች ውስጥ ባለይዞታው አብዛኛውን ጊዜ ለትራንስፖርት የሚጠቀምባቸው ጠቅላላ ብዛት እንዲሁም በፆታ ተለይተው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

ለ3) ለሌላ አገልግሎት

ብዛታቸው በ«ለ» ከተመዘገበው ፈረሶች ውስጥ ባለይዞታው ከላይ ከተጠቀሱት ውጭ ለሌላ አገልግሎት የሚያውላቸው ጠቅላላ ብዛት እንዲሁም በፆታ ተለይተው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

ጥያቄ 5:- ጠቅላላ የበቅሎዎች ብዛት

የካቲት 1/1996 ዓ.ም ባለይዞታው የነበሩት ጠቅላላ በቅሎዎች እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጠው ክፍት ቦታ ውስጥ ይመዘገባል።

ሀ) ከ3 ዓመት በታች

በጥያቄ 5 ከተመዘገቡት ጠቅላላ በቅሎዎች ውስጥ ዕድሜያቸው ከ3 ዓመት በታች የሆኑት ጠቅላላ ብዛት እንዲሁም በፆታ ተለይተው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

ለ) 3 ዓመትና በላይ

በጥያቄ 5 ከተመዘገቡት ጠቅላላ በቅሎዎች ውስጥ ዕድሜያቸው 3 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑት ጠቅላላ ብዛት እንዲሁም በፆታ ተለይተው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

ለ1) የእርሻ

ብዛታቸው በ«ለ» ከተመዘገቡት በቅሎዎች ውስጥ ባለይዞታው አብዛኛውን ጊዜ ለእርሻ ሥራ የሚጠቀምባቸው ጠቅላላ ብዛትና እንዲሁም በፆታ ተለይተው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

ለ2) የትራንስፖርት

ቁጥራቸው በ«ለ» ከተመዘገቡት በቅሎዎች ውስጥ ባለይዞታው አብዛኛውን ጊዜ ለትራንስፖርት የሚጠቀምባቸውን ጠቅላላ ብዛትና እንዲሁም በፆታ ተለይተው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

ለ3) ለሌላ አገልግሎት

ቁጥራቸው በ«ለ» ከተመዘገቡት በቅሎዎች ውስጥ ባለይዞታው ለሌላ አገልግሎት የሚያውላቸው ጠቅላላ ብዛት እንዲሁም በፆታ ተለይተው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

ጥያቄ 6:- ጠቅላላ የአህዮች ብዛት

የካቲት 1/1996 ዓ.ም ባለይዞታው የነበሩት ጠቅላላ አህዮች እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጠው ክፍት ቦታ ውስጥ ይመዘገባል።

ሀ) ከ3 ዓመት በታች

በጥያቄ 6 ከተመዘገቡት ጠቅላላ አህዮች ውስጥ ዕድሜያቸው ከሶስት ዓመት በታች የሆኑት ጠቅላላ ብዛት እንዲሁም በፆታ ተለይቶ በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

ለ) 3 ዓመትና በላይ

በጥያቄ 6 ከተመዘገቡት ጠቅላላ አህዮች ውስጥ ዕድሜያቸው ሦስት ዓመትና በላይ የሆኑት ጠቅላላ ብዛት እንዲሁም በፆታ ተለይተው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

ለ1) የእርሻ

ብዛታቸው በ«ለ» ከተመዘገቡት አህዮች ውስጥ ባለይዞታው አብዛኛውን ጊዜ ለእርሻ ሥራ የሚጠቀምባቸው ጠቅላላ ብዛት እንዲሁም በፆታ ተለይተው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

ለ2) የትራንስፖርት

ባለይዞታው ብዛታቸውን በ«ለ» ካስመዘገባቸው አህዮች ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ለትራንስፖርት የሚጠቀምባቸውን አህዮች ጠቅላላ ብዛት እንዲሁም በፆታ ተለይተው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

ለ3) <u>ለሌላ አገልግሎት</u>

ብዛታቸው በ«ለ» ከተመዘገቡት አህዮች ውስጥ ባለይዞታው ለሌላ አገልግሎት የሚጠቀምባቸውን ጠቅላላ ብዛት እንዲሁም በፆታ ተለይተው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

ጥያቄ 7- <u>ጠቅላላ የግመሎች ብዛት</u>

የካቲት 1/1996 ዓ.ም ባለይዞታው የነበሩት ጠቅላላ ግመሎች እንዲሁም የወንድና የሴት ብዛት ባለይዞታውን በመጠየቅ በተሰጠው ክፍት ቦታ ውስጥ ይመዘገባል።

ሀ) <u>ከ4 ዓመት በታች</u>

በጥያቄ 7 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ግመሎች ውስጥ ዕድሜያቸው ከ4 ዓመት በታች የሆኑት ጠቅላላ ብዛት እንዲሁም በፆታ ተለይተው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

ለ) <u>4 ዓመትና በላይ</u>

በጥያቄ 7 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ግመሎች ውስጥ ዕድሜያቸው 4 ዓመትና በላይ የሆኑ ጠቅላላ ብዛት እንዲሁም በፆታ ተለይተው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

ለ1) <u>የሥጋ</u>

ብዛታቸው በ«ለ» ከተመዘገቡት ግመሎች ውስጥ ለሥጋ የሚውሉ ግመሎች ጠቅላላ ብዛት እንዲሁም በፆታ ተለይተው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

ለ2) <u>የእርሻ</u>

ብዛታቸው በ«ለ» ከተመዘገቡት ግመሎች ውስጥ ባለይዞታው አብዛኛውን ጊዜ ለእርሻ ሥራ የሚጠቀምባቸው ጠቅላላ ብዛት እንዲሁም በፆታ ተለይተው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

ለ3) <u>የወተት</u>

ብዛታቸው በ«ለ» ከተመዘገቡት ግመሎች ውስጥ ባለይዞታው ለወተት የሚጠቀምባቸውን ግመሎች ብዛት በተሰጠው ክፍት ቦታ ውስጥ ይመዘገባል።

ለ4) <u>የትራንስፖርት</u>

ባለይዞታው ብዛታቸውን በ«ለ» ካስመዘገባቸው ግመሎች ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ለትራንስፖርት የሚጠቀምባቸው ጠቅላላ ብዛትና እንዲሁም በፆታ ተለይተው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

ለ5) <u>ለሌላ አገልግሎት</u>

ብዛታቸው በ«ለ» ከተመዘገቡት ግመሎች ውስጥ ባለይዞታው ከላይ ከተጠቀሱት ውጭ ለሌላ አገልግሎት የሚያውላቸውን ጠቅላላ ብዛት እንዲሁም በፆታ ተለይተው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ።

<u>ማስታወሻ:-</u> <u>ፈረሶችን፥ በቅሎዎችኝ፣ አህዮችንና ግመሎችን በሚመለከት</u>

<u>ለፈረሶች:-</u>

ጥያቄ 4= ሀ + ለ

ለ = ለ1 + ለ2 + ለ3

መሆኑን ማገናዘብ ያስፈልጋል።

<u>ለበቅሎዎች:-</u>

ጥያቄ 5 = ሀ + ለ

ለ = ለ1 + ለ2 + ለ3

መሆኑን ማገናዘብ ያስፈልጋል።

<u>ለአህዮች:-</u>

ጥያቄ 6 = ሀ + ለ

ለ = ለ1 + ለ2 + ለ3

መሆኑን ማገናዘብ ያስፈልጋል።

ለማመሉች:-

ጥያቄ 7 = ሀ + ለ

ለ = ለ1 + ለ2 + ለ3 + ለ4 + ለ5

መሆኑን ማገናዘብ ያስፈልጋል::

ዶሮዎች

ጥያቄ 8 :- የካቲት 1/1996 የነበሩ ጠቅላላ ዶሮዎች ብዛት

የካቲት 1/1996 ዓ.ም ባለይዞታው የነበሩት ጠቅላላ የዶሮዎች ብዛት ተጠይቆ ይሞላል::

ሀ) ዕድሜያቸው ከ20 ሳምንት በላይ የሆነ ዕንቁላል የሚጥሉ እናት ዶሮዎች

በጥያቄ 8 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ዶሮዎች ውስጥ ዕድሜያቸው ከ20 ሳምንት በላይ ሆኖ እንቁላል የሚጥሉ እናት ዶሮዎች (በጥናቱ ቀን ዕንቁላል ባይጥሉም) ብዛት ተጠይቆ ይሞላል::

ለ) ዕድሜያቸው ከ20 ሳምንት በላይ የሆነ ዕንቁላል የማይጥሉ እናት ዶሮዎች

በጥያቄ 8 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ዶሮዎች ውስጥ ዕድሜያቸው ከ20 ሳምንት በላይ ሆኖ ዕንቁላል የማይጥሉ እናት ዶሮዎች ብዛት ተጠይቆ ይሞላል:: ዕንቁላል የማይጥሉ እናት ዶሮዎች ሲባል ዕንቁላል መጣል ያቆሙና ለእናትነት ደርሰው ዕንቁላል ጥለው የማያውቁትን መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል::

ሐ) ዕድሜያቸው ከ20 ሣምንት በላይ የሆነ አውራ ዶሮዎች

በጥያቄ 8 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ዶሮዎች ውስጥ ዕድሜያቸው ከ20 ሳምንት በላይ የሆነ አውራ ዶሮዎች ብዛት ተጠይቆ ይሞላል::

መ) ዕድሜያቸው ከ8-20 ሣምንት የሆነ ለአውራነት ያልደረሱ ዶሮዎች

በጥያቄ 8 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ዶሮዎች ውስጥ ዕድሜያቸው ከ8-20 ሳምንታት የሆነ ለአውራነት ያልደረሱ ዶሮዎች ብዛት ተጠይቆ ይሞላል::

ሠ) *ዕድሜያቸው ከ8-20 ሣምንት የሆነ ቂብ ዶሮዎች*

በጥያቄ 8 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ዶሮዎች ውስጥ ዕድሜያቸው ከ8-20 ሳምንታት የሆነ ቂብ ዶሮዎች ብዛት ተጠይቆ ይሞላል።

ረ) ዕድሜያቸው ከ8 ሳምንት በታች የሆነ ጫጩቶች

በጥያቄ 8 ከተመዘገቡት ጠቅላላ ዶሮዎች ውስጥ ዕድሜያቸው ከ8 ሳምንት በታች የሆነ ጫጩቶች ብዛት ተጠይቆ ይሞላል።

*ማስታወሻ:-*

*ጥያቄ 8 = ሀ + ለ + ሐ + መ + ሠ + ረ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።*

ጥያቄ II:- ባለፉት 12 ወራት (ከየካቲት 2/1995 - የካቲት 1ቀን 1996) የቤት እንስሳት፣ ወይም ንብ የያዙ ቀፎዎች ነበረዎት?

| | | |
|---|---|---|
| አዎን | = | 1 |
| አልነበረኝም | = | 2 |

የባለይዞታው መልስ አዎን ከሆነ በተሰጠው ቦታ ኮድ «1» በመሙላት በዚህ ክፍል ያሉትን ጥያቄዎች ማጠናቀቅ ያስፈልጋል። አልነበረኝም ካለ ኮድ «2» በመሙላት በጥያቄ 11 «ሐ» ና «ሰ» ብቻ በመጠየቅና መልሱን በመመዝገብ ጥያቄው ያቆማል።

ጥያቄ 9:- ባለፉት 12 ወራት (ከየካቲት 2/1995 - የካቲት 1/1996 ቢያንስ አንድ ጊዜ የማር ምርት የሰጡ ቀፎዎች ብዛት)

ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ከየካቲት 2/1995 - የካቲት 1/1996 ቢያንስ አንድ ጊዜ ማር የተመረተባቸው ቀፎዎች ጠቅላላ ብዛት ባለይዞታው ተጠይቆ ይሞላል።

ሀ) ባህላዊ ቀፎዎች

ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ማር የተመረተባቸው ባህላዊ ቀፎዎች ብዛት ተጠይቆ ይሞላል።

ለ) <u>የሽግግር ወይም ባለመረባረብ ቀፎዎች (መለስተኛ ዘመናዊ ቀፎዎች)</u>
ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ማር የተመረተባቸው የሽግግር ወይም ባለመረባረብ ቀፎዎች ብዛት ተጠይቆ ይሞላል::

ሐ) <u>ዘመናዊ ቀፎዎች፡-</u>
ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ማር የተመረተባቸው ዘመናዊ ቀፎዎች ብዛት ተጠይቆ ይሞላል::

*<u>ማስታወሻ፡-</u>*

*<u>ባህላዊ ቀፎ</u> ማለት ከተለያዩ ነገሮች (ለምሣሌ፡- ከሸንበቆ፣ ከቀርከሃ፣ እንጨት፣ ከተቦረቦረ ዛፍ፣ ከእንሥራ ... ወዘተ) የተሰራና ማር የሚመረትበት ማለት ነው::*

*<u>የሽግግር ወይም ባለመረባርብ /መለስተኛ ዘመናዊ ቀፎ/</u> ማለት በግብርና ሚኒስቴር ወይም አግባብ ባላቸው መሥሪያ ቤቶች የሙያ ድጋፍ ተሠርቶ ከባህላዊ ቀፎ የተሻለ ምርት የሚሰጥ ማለት ነው:: ከዚህ በተጨማሪ*

- *ገበሬው በቀላሉ ሊሰራው የሚችል*
- *በሳጥን መልክ የተሠራ አንድ ቀፎ ብቻ የሆነ*
- *በአንድ ዘንግ ጠርዝ ሰም በማጣበቅ በንቦች እንጀራው ተጋግሮ ለእንቁላል መጣያና ማር መስሪያ እንዲገለገሉበት ወደ ቀፎ በመጨመር የሚዘጋጅ የቀፎ ዓይነት ነው::*

*<u>ዘመናዊ ቀፎ</u> ማለት በግብርና ሚኒስቴር ወይም አግባብ ባላቸው መሥሪያ ቤቶች ባለሙያ ተሰርቶ ከፍ ያለ ምርት የሚሰጥ ማለት ሲሆን በሳጥን መልክ የተሠራና ከ3-5 ቀፎዎች አደራርቦ ማስቀመጥ የሚቻልበት ነው:: በተጨማሪም የራሱ የሆነ በሽቦ የተሠራ የእንጀራ መጋገሪያ ፍሬም ያለውና እንጀራው በባለሙያ ከተሠራ በኋላ ወደ ቀፎው በመጨመር በቀጥታ ንቦች እንቁላልና ማር እንዲሠሩበት ተደርጎ የተዘጋጀ የንብ ቀፎ ነው::*

ባለፉት 12 ወራት (ከየካቲት 2/1995 - የካቲት 1/1996) የተገኘ የወተት፡ የዕንቁላልና የማር ምርት

ጥያቄ 10 :- የወተት ላሞችና ግመሎች

ሀ) በዓመቱ ውስጥ ወተት የሰጡ ላሞች ብዛት

ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ወተት ሲሰጡ የነበሩ ላሞች ብዛት ባለይዞታው ተጠይቆ ይመዘገባል።

ለ) በ«ሀ» ከተመዘገቡት ላሞች ውስጥ አንድ ላም በአማካይ በዓመቱ ውስጥ ለስንት ወራት ወተት ሰጠች?

ከላይ በተጠቀሰው ዓመት በ«ሀ» ከተመዘገቡት ላሞች ውስጥ አንድ ላም በአማካይ ለስንት ወራት ወተት እንደሰጠች ባለይዞታው ተጠይቆ በተሰጠው ቦታ ይመዘገባል። በዚሁ ዓመት ውስጥ ከአንድ ላም በላይ ወተት የሰጡ እንዳሉ ባለይዞታው ቢገልጽ እያንዳንዳቸው ለስንት ወራት ወተት እንደሰጡ በመጠየቅ ከተደመረ በኋላ ለብዛታቸው ተካፍሎ የሚገኘው አማካይ ውጤት ይሞላል።

ሐ) በተለምዶ አንድ ላም በአማካይ ለስንት ወራት ትታለባለች?

አንድ ላም በአማካይ ለስንት ወራት እንደምትታለብ ማለትም ወተት መስጠት ከጀመረችበት እስከ ምትነጥፍበት ያለውን ጊዜ የባለይዞታውን ልምድ በመጠየቅ በዚህ ጥያቄ አቅጣጫ ባለው ቦታ ይመዘገባል።

መ) የወተት ምርት በቀን ÷ በላም (በሊትር)

አንድ ላም በአማካይ በቀን ስንት ሊትር ወተት እንደምትሰጥ ባለይዞታው ተጠይቆ መጠኑ በሊትር ይመዘገባል።

ሠ) ወተት የሰጡ ግመሎች ብዛት

ባለፉት 12 ወራት ወተት ሲሰጡ የነበሩ ግመሎች ብዛት ባለይዞታው ተጠይቆ ይመዘገባል።

ረ) በ«ሠ» ከተመዘገቡት ግመሎች ውስጥ አንድ ግመል በአማካይ ለስንት ወራት ወተት ሰጠች?

ከላይ በተጠቀሰው ዓመት ውስጥ በ«ሠ» ከተመዘገቡት ግመሎች ውስጥ አንድ ግመል በአማካይ ለስንት ወራት ወተት እንደሰጠች ተጠይቆ ይመዘገባል:: ከአንድ ግመል በላይ ወተት የሰጡ መኖራቸውን ባለይዞታው ከገለጸ አማካዩን በመውሰድ ይሞላል::

ሰ) በተለምዶ አንድ ግመል ለስንት ወራት ትታለባለች?

አንድ ግመል በአማካይ ለስንት ወራት እንደምትታለብ ወይም ወተት መስጠት ከጀመረችበት እስከምትነጥፍበት ያለውን ጊዜ የባለይዞታውን ልምድ በመጠየቅ ይሞላል::

ሸ) የወተት ምርት በቀን ÷ በግመል (በሊትር)

አንድ ግመል በአማካይ በቀን ስንት ሊትር ወተት እንደምትሰጥ ባለይዞታው ተጠይቆ መጠኑ በሊትር ይመዘገባል::

*ማስታወሻ :- ባለይዞታው የወተቱን መጠን በአካባቢ መለኪያ የሰጠ እንደሆን ወተት ከተገኘ በወተት ካልተገኘ ደግሞ ውሀ በሊትር ተለክቶ ወይንም በሚዛን ተመዝኖ መሞላት አለበት:: (አንድ ሊትር = አንድ ኪሎ ግራም መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል::)*

ጥያቄ 11:- የዕንቁላል ምርት /ብዛት/ በዶሮ (በአንድ መጣያ ወቅት)

አንድ ዶሮ በአማካይ በአንድ የዕንቁላል መጣያ ወቅት ስንት ዕንቁላል እንደምትጥል ባለይዞታው ተጠይቆ ይሞላል::

ጥያቄ 12:- አማካይ የዕንቁላል መጣያ ወቅት (በቀን)

የአንድ ዶሮ አማካይ የዕንቁላል መጣያ ወቅት ምን ያህል ቀኖች እንደሆነ ባለይዞታው ተጠይቆ ይመዘገባል::

ጥያቄ 13 :- ባለፉት 12 ወራት በአማካይ የአንድ ዶሮ የእንቁላል መጣያ ወቅት ብዛት

ባለፉት 12 ወራት (ከየካቲት 2/1995 - የካቲት 1/1996) በአማካይ

የአንድ ዶሮ የእንቁላል መጣያ ወቅት ብዛት ምንያህል እንደሆነ ባለይዞታው ተጠይቆ ይመዘገባል።

*ማስታወሻ :-*

*የሚጠየቀው የዕንቁላል ብዛት በአንድ የዕንቁላል መጣያ ወቅት ተጥሎ ቤተሰቡ የተመገበውን ፣ የተሸጠውን ፣ የተበላሸውን /የተሰበረውንና ወደ ጫጩትነት የተቀየረውን በሙሉ ያጠቃልላል።*

ጥያቄ 14:- የማር ምርት መጠን (በኪሎ ግራም) በቀፎ በዓመት

ሀ) በአማካይ በአንድ ቆረጣ ወቅት ከአንድ ባህላዊ ቀፎ የተገኘ የማር ምርት

ባለይዞታው በአንድ ቆረጣ ወቅት ከአንድ ባህላዊ ቀፎ በዓመት በአማካይ የሚያገኘው የማር ምርት መጠን በኪሎ ግራም ቀጥሎም በዓመቱ ውስጥ በአማካይ ከአንድ ባህላዊ ቀፎ ምን ያህል ጊዜ ምርት እንደሚያገኝ ተጠይቆ ይሞላል።

ለ) በአማካይ በአንድ ቆረጣ ወቅት ከአንድ መለስተኛ ዘመናዊ) ቀፎ የተገኘ የማር ምርት

ባለይዞታው በአንድ ቆረጣ ወቅት ከአንድ መለስተኛ ዘመናዊ ቀፎ በዓመት በአማካይ የሚያገኘው የማር ምርት መጠን በኪሎ ግራምና በዓመቱ ውስጥ በአማካይ ከአንድ መለስተኛ ዘመናዊ ቀፎ ምን ያህል ጊዜ ምርት እንደሚያገኝ ተጠይቆ በተሰጠው ቦታ ይመዘገባል።

ሐ) በአማካይ በአንድ ቆረጣ ወቅት ከአንድ ዘመናዊ ቀፎ የተገኘ የማር ምርት:-

ባለይዞታው በአንድ ቆረጣ ወቅት ከአንድ ዘመናዊ ቀፎ በዓመት በአማካይ የሚያገኘው የማር ምርት መጠን በኪሎ ግራምና በዓመቱ ውስጥ በአማካይ ከአንድ ዘመናዊ ቀፎ ምን ያህል ጊዜ ምርት እንደሚያገኝ ተጠይቆ በተሰጠው ቦታ ይመዘገባል።

ጥያቄ 15:- የቤት እንስሳት በሽታና ሕክምናን በተመለከተ (ከየካቲት 2/1995 - የካቲት 1/1996 ዓ.ም)

ዓምድ 1 - ተራ ቁጥር

ተራ ቁጥር ተሰጥቷል።

ዓምድ 2 - የቤት እንስሳት ዓይነት

በዚህ ዓምድ የቤት እንስሳት ዓይነት የዳልጋ ከብቶች፣ በጎች፣ ፍየሎች፣ ፈረሶች፣ አህዮች ፣ በቅሎዎች ፣ ግመሎችና ዶሮዎች ተዘርዝረዋል።

ዓምድ 3 - ክትባት የተደረገላቸው ብዛት

በዚህ ዓምድ ባለይዞታው በዓመቱ ውስጥ ያስከተባቸው የቤት እንስሳት ብዛት በየዓይነታቸው ተጠይቆ ይሞላል።

ዓምድ 4 - በበሽታ የተጠቁ ብዛት

ባለይዞታው ካሉት የቤት እንስሳት ውስጥ በበሽታ የተጠቁ ካሉ ብዛታቸው በየዓይነታቸው ተጠይቆ ይሞላል።

ዓምድ 5 - ሕክምና የተደረገላቸው ብዛት

ባለይዞታው በዓምድ 4 በበሽታ የተጠቁ ናቸው ብሎ ካስመዘገባቸው የቤት እንስሳት ውስጥ ሕክምና የተደረገላቸው ካሉ ብዛታቸው በየዓይነታቸው ተጠይቆ ይሞላል።

ዓምድ 6 - በበሽታ የሞቱ ብዛት

በበሽታ ተጠቅተው የሞቱ የቤት እንስሳት ብዛት በየዓይነታቸው ተጠይቆ ይሞላል።

ዓምድ 7 - አስተያየት

ይህን ክፍል በተመለከተ የሚሰጥ ማንኛውም ዓይነት አስተያየት ካለ በተሰጠው ቦታ መሙላት ይቻላል።

ጥያቄ 16:- የቤት እንስሳት መኖ አጠቃቀም ሁኔታ (ከየካቲት 2/1995 - የካቲት 1/1996 ዓ.ም)

ዓምድ 1 - ተራ ቁጥር

ተራ ቁጥር ተሰጥቷል።

ዓምድ 2 - የመኖ ዓይነት

በዚህ ዓምድ የተለያዩ የመኖ ዓይነቶችና ኮዳቸው ተሰጥተዋል።

ዓምድ 3 - ተጠቅመዋል? (አዎን = 1 የለም = 2)

ባለይዞታው በዓምድ 2 የተጠቀሰውን የመኖ ዓይነት መጠቀም አለመጠቀሙ ተጠይቆ መልሱ አዎን ከሆነ ኮድ «1»፣ ካልተጠቀመ ደግሞ ኮድ «2» ይሞላል።

ዓምድ 4 - አዎን ከሆነ ድርሻ በመቶኛ

በዓምድ 3 ኮድ «1» ለተሞላለት የእያንዳንዱ መኖ ዓይነት ከጠቅላላው የመኖ አጠቃቀም ምን ያህል ድርሻ እንዳለው በመጠየቅና በመቶኛ በማስላት ይመዘገባል። በዓምድ 3 ኮድ «1» የተሞላላቸው የመቶኛ ድርሻዎቻቸው ተደምረው 100 መምጣት እንዳለባቸው ማስታወስ ያስፈልጋል።

## የቅጽ ግ.ና.ፕ 96/8ሀ በጊዜያዊ ሰብሎች (አትክልትና ሥራሥርን ጨምሮ) የተያዙ ማሣዎች ዝርዝርና የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ (በበልግ ወቅት) አሞላል

ይህ ቅጽ በቆጠራ ቦታው በተመረጡ ቤተሰቦች ውስጥ ለሚገኙ ባለይዞታዎች በሙሉ የሚሞላ ነው። በዚህ ቅጽ በበልግ ወቅት በጊዜያዊ ሰብሎች ብቻ (አትክልትና ሥራሥርን ጨምሮ) የተያዙ ማሣዎች የሚዘረዘሩበትና አጠቃላይ የእርሻ ሥራ ሁኔታው ክትትል የሚደረግበት ነው።

ክፍል 1. የአካባቢ መለያ

ዓምድ 1 - ክልል

ቆጠራው የሚካሄድበት ክልል ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 2 - ዞን

ቆጠራው የሚካሄድበት ዞን ስም ወይንም ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 3 - ወረዳ

ቆጠራው የሚካሄድበት ወረዳ ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 4 - ገበሬ ማህበር

ቆጠራው የሚካሄድበት የገበሬ ማህበር ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 5 - ቆጠራ ቦታ

ቆጠራው የሚካሄድበት ቆጠራ ቦታ ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 6 - የቤተሰብ መለያ ቁጥር

የተመረጠው ቤተሰብ መለያ ቁጥር ከቅጽ 94/1 ክፍል 2 ዓምድ 1 በመውሰድ ይሞላል።

ዓምድ 7 - የባለይዞታው መለያ ቁጥር

ለባለይዞታው የተሰጠውን መለያ ቁጥር ከቅጽ 94/1 ክፍል 2 ዓምድ 3 በመውሰድ ይሞላል።

ዓምድ 8 - የባለይዞታው ስም

የባለይዞታው ስም ከቅጽ 961 ክፍል 2 ዓምድ 4 በመውሰድ ይሞላል።

ዓምድ 9 - ዕድሜ

የባለይዞታው ዕድሜ ተጠይቆ በሙሉ ዓመት በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 10 - ፆታ (ወንድ = 1 ሴት = 2)

የባለይዞታው ፆታ ወንድ ከሆነ ኮድ «1» ሴት ከሆነች ኮድ «2» በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 11 - የትምህርት ሁኔታ የፈፀሙት ከፍተኛ ክፍል (አምስት ዓመትና በላይ ለሆኑ ባለይዞታዎች)

በዚህ ዓምድ ዕድሜያቸው 5 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ ባለይዞታዎች የትምህርት ሁኔታ (የፈፀሙት ከፍተኛ ክፍል) ተጠይቆ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ኮዶች ትክክለኛው ተመርጦ ይሞላል:: በመጀመሪያ ባለይዞታው ማንበብና መፃፍ የሚችል መሆኑ ከተጠየቀ በኋላ የሚችል ከሆነ ተምሮ የጨረሰው ከፍተኛ ክፍል ይጠየቃል:: አንድ ግለሰብ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ አለው የሚባለው በማንኛውም ግለሰብ በሚያውቀው ቋንቋ አንብቦ መረዳትና መፃፍ ሲችል ብቻ ነው:: የራሳቸውን ስም ወይንም ቁጥሮችን ብቻ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ግለሰቦች እንደተማሩ አይቆጠሩም:: በተጨማሪም የፈፀመው ክፍል ሲባል በቆጠራው ወቅት የሚገኝበት ክፍል ሳይሆን ተምሮ የጨረሰው ከፍተኛ ክፍል ማለት ነው:: (የትምህርት ሁኔታ ኮድ ከገጽ 25 ይመልከቱ)

ዓምድ 12 - የቤተሰብ አባላት ብዛት

በዓምድ 7 መለያ ቁጥሩ የተመዘገበው እያንዳንዱ ባለይዞታ ተጠይቆ መደበኛ የቤተሰብ አባላት ብዛት በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 13 - የግብርናው ዓይነት /ሰብል = 1 ከብት = 2 ሁለቱም = 3/

በዓምድ 7 መለያ ቁጥሩ የተመዘገበው እያንዳንዱ ባለይዞታ የተሠማራበት የግብርና ዓይነት ተጠይቆ ሰብል ማምረት ብቻ ከሆነ ኮድ «1» ከብት ማርባት /ማደለብ/ ብቻ ከሆነ ኮድ «2» ሁለቱም ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ይመልከቱ)

## ክፍል 2. በጊዜያዊ ሰብሎች (አትክልትና ሥራሥርን ጨምሮ) የተያዙ ማሣዎች ስፋትና የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ

ይህ ክፍል የሚያገለግለው ባለይዞታው በ1996 ዓ.ም በልግ ወቅት ያለውን በጊዜያዊ ሰብሎች (አትክልትና ሥራሥርን ጨምሮ) የተያዘ ማሣ ስፋትና የተገኘ/የሚገኝ ምርት መጠንና የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ለመከታተል ነው:: በዚህ ቅጽ ስምንት ማሣዎችን ለመመዝገብና ሌሎች የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታን የሚመለከቱ መረጃዎች ለመሰብሰብ የሚያስችል ቦታ (ከዓምድ 3 - 6 በፊት ለፊት ከዓምድ 7 - 10 በጀርባ ተሰጥቷል::) ከስምንት በላይ የሆኑ በጊዜያዊ ሰብል የተያዙ ማሣዎች ሲያጋጥም ተጨማሪ ቅጽ መጠቀም ያስፈልጋል::

ዓምድ 1 - ተራ ቁጥር

ተራ ቁጥር ከ«01» በመጀመር በቅደም ተከተል ተሞልቷል።

ዓምድ 3-6 - የፓርሰል ቁጥር ፣ የማሣ ቁጥርና የጊዜያዊ ሰብል ስም

መረጃ የሚሰበሰብላቸው ጊዜያዊ ሰብሎች የሚገኙባቸው ፓርሰሎች በሙሉ የፓርሰል ቁጥር ይሰጣቸዋል። እንዲሁም በእያንዳንዱ ፓርሰል ለሚገኙ ማሣዎች ተከታታይ የማሣ ቁጥር ይሰጣቸውና የሰብሉ ስም ደግሞ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል። ለኮድ የተሰጠው ቦታ ለቢሮ ሥራ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም። የፓርሰልና ማሣ ቁጥር አሰጣጥን በተመለከተ ከገጽ ___ እስከ ገጽ ___ የቀረበውን ምሳሌ ይመልከቱ።

*ማስታወሻ፦*

*በአንድ ባለይዞታ የተያዘ የተለያዩ ፓርሰሎችና ማሣዎችን በተመለከተ የሚሰጡ የፓርሰልና ማሣ ቁጥሮች ተከታታይነት ባለው መንገድ በቅጽ ግ.ና.ፐ. 96/8ለ የተሰጠውን ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል።*

ዓምድ 2 - ለባለይዞታዎች የሚቀርቡ ጥያቄዎች

ጥያቄ 1፦የይዞታው ዓይነት፦ ባለይዞታው ያስመዘገበው እያንዳንዱ ማሣ የባለይዞታው የራሱ ከሆነ ኮድ «1»፣ በኪራይ ወይም በኮንትራት የተገኘ ከሆነ ኮድ «2»፣ ከእነዚህ ውጭ በሆነ መንገድ የተገኘ ከሆነ ኮድ «3» በጥያቄ ትይዩ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል።

ጥያቄ 2፦ የማሳው ስፋት /በስታንዳርድ/ በአካባቢ መለኪያ

ባለይዞታው ያስመዘገበው ማሣ ስፋቱ በስታንደርድ ወይም በአካባቢ መለኪያ ተጠይቆ የስታንደርድ /የአካባቢው መለኪያ ስምና የእያንዳንዱ ማሣ ስፋት መጠን በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል ለኮድ በተሰጠው ቦታ ምንም አይሞላበትም።

ጥያቄ 3፦ የምርት መጠን በስታንደርድ /በአካባቢ መለኪያ፣

ባለይዞታው ካስመዘገበው ከእያንዳንዱ ማሣ ያመረተው /የሚያመርተው የምርት መጠን በስታንደርድ /በአካባቢ መለኪያ ምን ያህል እንደሆነ ተጠይቆ የስታንደርድ /የአካባቢው መለኪያ ስምና ከእያንዳንዱ ማሣ የተመረተው ምርት መጠን በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

ጥያቄ 4፦ ማሳው በኤክስቴንሽን መርሐ-ግብር ታቅፏል? (አዎ = 1 የለም = 2)

ባለይዞታው ያስመዘገበው እያንዳንዱን ማሣ አስመልክቶ በኤክስቴንሽን መርሐ-ግብር መታቀፉን አለመታቀፉን ተጠይቆ ከታቀፉ ኮድ «1»

ካልታቀፈ ደግሞ ኮድ «2» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

*ማስታወሻ:-*

*በኤክስቴንሽን መርሀ-ግብር የታቀፈ ገበሬ ማለት በዘመናዊ አስተራረስ የሚጠቀምና ለዚህም በአካባቢው በሚገኘው የልማት ሠራተኛ የቅርብ እገዛ፣ ትምህርትና ምክር የሚያገኝ ነው። ዘመናዊ አስተራረስ ሲባልም በጥናት የተደረሰበት አሠራርን መሠረት በማድረግ ለእያንዳንዱ የሰብል ዓይነት:-*

- *የማሣ አዘገጃጀት*
- *በጥቅም ላይ መዋል የሚገባው የማዳበሪያ ዓይነት፣ አጠቃቀምና መጠን ... ወዘተ በመመሪያው መሠረት ተግባራዊ ማድረግ ነው።*

ጥያቄ 5:- የመስኖ ዘዴ ተጠቅመዋል? (አዎ = 1 የለም = 2)

ባለይዞታው እያንዳንዱን ያስመዘገበውን ማሣ በማስመልከት በማሣው ላይ ያለውን ሰብል ለማምረትም ሆነ ምርትን ለማሻሻል የመስኖ ዘዴ መጠቀሙ ተጠይቆ ተጠቅሞ ከሆነ ኮድ «1» ፣ ያልተጠቀመ ከሆነ ደግሞ ኮድ «2» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

ጥያቄ 6:- የዘር ዓይነት (ምርጥ ዘር = 1 ምርጥ ዘር ያልሆነ = 2)

ባለይዞታው በእያንዳንዱ ባስመዘገበው ማሣ ላይ የተጠቀመው የዘር አይነት ተጠይቆ ምርጥ ዘር ከሆነ ኮድ «1» ምርጥ ዘር ካልሆነ ደግሞ ኮድ «2» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

ጥያቄ 7:- የተጠቀሙት ምርጥ ዘር ካልሆነ መጠን በኪሎ ግራም (በጥያቄ 6 ኮድ 2 ለተሞላላቸው)

ይህ ጥያቄ የሚጠየቀው ለብርዕ፣ አገዳ፣ ጥራጥሬና ቅባት ሰብሎች ብቻ ሲሆን ባለይዞታው ያስመዘገበው እያንዳንዱ ማሣ ላይ የሚገኘውን ሰብል አስመልክቶ ለዘር የተጠቀመው የአካባቢ ዘር ከሆነ መጠኑ በኪሎ ግራም ተጠይቆ የተገኘው መልስ በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

ጥያቄ 8:- የተጠቀሙት ምርጥ ዘር ከሆነ መጠን በኪሎ ግራም (በጥያቄ 6 ኮድ «1» ለተሞላላቸው)

ይህ ጥያቄ የሚጠየቀው ለብርዕ፣ አገዳ፣ ጥራጥሬና ቅባት ሰብሎች ብቻ ሲሆን ባለይዞታው ባስመዘገበው እያንዳንዱ ማሣ ላይ የሚገኘውን ሰብል አስመልክቶ ለዘር የተጠቀመው ምርጥ ዘር ከሆነ መጠኑ በኪሎ ግራም ተጠይቆ የተገኘው መልስ በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

ጥያቄ 9:- የተጠቀሙት ምርጥ ዘር ከሆነ ዋጋ (በጥያቄ 6 ኮድ «1» ለተሞላላቸው)

በጥያቄ 6 ኮድ «1» ተሞልቶ መጠኑ የተጠቀሰው ምርጥ ዘር ዋጋው ምን ያህል እንደሆነ ተጠይቆ የተገኘው መልስ በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ጥያቄ 10:- የሰብል ብልሽት ደርሷል ወይ? (አዎን = 1 የለም = 2)

በእያንዳንዱ ማሣ ላይ ያለውን ሰብል አስመልክቶ የሰብል መበላሸት መድረሱን ባለይዞታው ተጠይቆ ደርሶ ከሆነ ኮድ «1» ካልደረሰ ደግሞ ኮድ «2» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ጥያቄ 11:- የሰብል ብልሽት ደርሶ ከሆነ ለብልሽቱ አንድ ዋና ምክንያት

ይህ ጥያቄ የሚጠየቀው በጥያቄ 10 የሰብል መበላሸት ደርሷል ተብሎ ኮድ «1» የተሞላ እንደሆነ ብቻ ነው:: ስለዚህ የሰብል መበላሸት ደርሶ ከሆነ በዚህ የመረጃ ሰብሳቢዎች መመሪያ ገጽ 19 ከተዘረዘሩት የሰብል መበላሸት ምክንያቶች ውስጥ ዋንኛ የሆነው ምክንያት ተወስዶ በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይመዘገባል:: ለኮድ የተሰጠው ቦታ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም::

ጥያቄ 12:- የብልሽቱ መጠን በመቶኛ

በጥያቄ 11 በተገለፀው ምክንያት በሰብል ላይ ጉዳት የደረሰ ከሆነ የተበላሸው ወይም ጉዳት የደረሰበት ሰብል ከማሣው ጠቅላላ ስፋት ምን ያህሉን እንደሚሸፍን በመቶኛ ባለይዞታው ተጠይቆ የተገኘው መልስ በዚህ ጥያቄ አቅጣጫ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል:: ለምሣሌ:- ባለይዞታው ማሣውን ላይ ከሚገኘው ሰብል ከጠቅላላው ማሣ ስፋት ሩብ ያህሉን የሸፈነው ተበላሽቷል ቢል "25" መሞላት አለበት::

ጥያቄ 13:- ብልሽቱን ለመከላከል /ለጥንቃቄ/ የተወሰደ እርምጃ (አለ = 1 የለም = 2)

በዚህ ጥያቄ አቅጣጫ ብልሽት የደረሰበትን እያንዳንዱን ማሣ አስመልክቶ ባለይዞታው የደረሰውን የሰብል ብልሽት ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ ወይም አስቀድሞ ለመከላከል የወሰደው እርምጃ ካለ ኮድ «1» ፣ ከሌለ ደግሞ ኮድ «2» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ጥያቄ 14:- የተወሰደው እርምጃ ዓይነት (ኬሚካል = 1 ኬሚካል ያልሆነ = 2 ሁለቱም = 3)

ባለይዞታው የሰብሉን ብልሽት ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ ወይም አስቀድሞ ለመከላከል የተጠቀመው መድኃኒት ኬሚካል ከሆነ ኮድ «1» ፣ ኬሚካል ያልሆነ ከሆነ ኮድ «2» ሁለቱም ዓይነት ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ቦታ ይሞላል::

ጥያቄ 15:- ለጥያቄ 14 ኮድ «1» ወይም ኮድ «3» ከተሞላ ኬሚካል /የኢንዱስትሪ ውጤት/ የሆነ ከተጠቀሙ ዓይነቱ (ፀረ-ተባይ = 1 ፀረ-አረም = 2 ፀረ-በሽታ = 3 1ና2 = 4 1ና3 = 5 2ና3 = 6 ሁሉም = 7 )

ባለይዞታው በጥያቄ 14 የወሰደው እርምጃ ዓይነት ኬሚካል /የኢንዱስትሪ ውጤት/ ከሆነ ማለትም (በጥያቄ 14 ኮድ «1» ወይም ኮድ «3» ከተሞላ) ለእያንዳንዱ ማሣ ምን አይነት ኬሚካል እንደተጠቀመ ተጠይቆ ፀረ-ተባይ ከሆነ ኮድ «1» ፣ ፀረ-አረም ከሆነ ኮድ «2» ፣ ፀረ-በሽታ ከሆነ ኮድ «3» ፣ ፀረ-ተባይና ፀረ-አረም ከሆነ ኮድ «4»፣ ፀረ-ተባይ እና ፀረ-በሽታ ከሆነ ኮድ «5» ፣ ፀረ-አረም እና ፀረ-በሽታ ከሆነ ኮድ «6» ፣ ሁሉንም ዓይነት ከሆነ ደግሞ ኮድ «7» ይሞላል::

ጥያቄ 16:- የተፈጥሮ /ኬሚካል ማዳበሪያ ተጠቅመዋል? (አዎን = 1 የለም = 2)

ባለይዞታው ባስመዘገበው በሰብል በተያዘ በእያንዳንዱ ማሣ ላይ ሊገኝ የሚችለውን ምርት ለማሻሻል ማዳበሪያ መጠቀም አለመጠቀሙ ተጠይቆ ተጠቅሞ ከሆነ ኮድ «1» ፣ ያልተጠቀመ ከሆነ ደግሞ ኮድ «2» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ባታ ይሞላል::

ጥያቄ 17:- ከተጠቀሙ የማዳበሪያው ዓይነት (የተፈጥሮ = 1 ኬሚካል = 2 ሁለቱም = 3)

ባለይዞታው ማዳበሪያ ተጠቅሞ በጥያቄ 16 ኮድ «1» ተሞልቶ ከሆነ በዚህ ጥያቄ የማዳበሪያው አይነት ይጠየቃል:: ጥቅም ላይ የዋለው ማዳበሪያ ዓይነት የተፈጥሮ ከሆነ ኮድ «1» ኬሚካል ከሆነ ኮድ «2» ፣ ሁለቱም ዓይነት ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ባታ ይሞላል::

ጥያቄ 18:- ኬሚካል ማዳበሪያ ካልተጠቀሙ አንድ ዋና ምክንያት (በጥያቄ 16 ኮድ «2» ወይም በጥያቄ 17 ኮድ «1» ከተሞላ)

ባለይዞታው ማዳበሪያ መጠቀም አለመጠቀሙ በጥያቄ 16 ላይ ተጠይቆ ኮድ «2» ከተሞላ ወይም ማዳበሪያ ተጠቅሞ በጥያቄ 17 ኮድ «1» ከተሞላ ኬሚካል ማዳበሪያ ያልተጠቀመበትን ምክንያት ተጠይቆ ምክንያቱ በጥያቄ ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል:: ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ምክንያቶች በመምረጥ ትክክለኛውን ምክንያትና ኮድ ይሞላል::

ምክንያቶቹም የሚከተሉት ናቸው:-

| | | |
|---|---|---|
| - ጥቅሙን ካለማወቅ | = | 1 |
| - ውድ ስለሆነ | = | 2 |
| - የገንዘብ እጥረት | = | 3 |
| - የአቅርቦት እጥረት | = | 4 |
| - የብድር አገልግሎት አለመኖር | = | 5 |
| - ውጤታማነቱ አጠራጣሪ ስለሆነ | = | 6 |
| - ሌላ ካለ ይገለጽ | = | 7 |

*ማሳሰቢያ:- ባለይዞታው በተለያዩ ሰብሎች የተያዙ ማሳዎችን በተመለከተ ኬሚካል ማዳበሪያ ለምን እንደተጠቀመ ተጠይቆ የሰጠው መልስ ከኮድ 2-6 ቢያንስ አንዱን ከመለሰ ሌሎች ሰብሎችን ግን ኮድ 1 «ጥቅሙን ካለማወቅ» የሚል መልስ መሞላት የለበትም:: መልስ ሰጪው ይህንን መልስ ከሰጠ ግን መረጃ ሰብሳቢው ተጨማሪ የማውጣጣት ጥያቄዎችን ለባለይዞታው በማቅረብ ተገቢውን ኮድ መሙላት ይኖርበታል::*

ጥያቄ 19 - ኬሚካል ማዳበሪያ ከተጠቀሙ (በጥያቄ 17 ኮድ «2» ወይም «3» ከተሞላ)

ጥያቄ 19.1:- ዓይነት

ባለይዞታው የተጠቀመው ኬሚካል ማዳበሪያ ዓይነቱ ተጠይቆ ዩሪያ ከሆነ ኮድ «1» ፣ ዳፕ ከሆነ ኮድ «2» ፣ ሁለቱም ዓይነት ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» እያንዳንዱን ማሣ አስመልክቶ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ጥያቄ 19.2:- መጠን በኪሎ ግራም

በጥያቄ 19.1 ዓይነቱ የተገለጸው ማዳበሪያ መጠን ባለይዞታው ተጠይቆ መልሱ በኪሎ ግራም በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል:: ሆኖም ባለይዞታው የማዳበሪያውን መጠን በኪሎ ግራም መግለጽ ካልቻለ

ማዳበሪያውን ሲገዛ ወይም ጥቅም ላይ ሲያውል መጠኑን ለመለካት የተጠቀመበትን የመለኪያ ዕቃ (ጣሳ ፣ ቁና ፣ ሳህን ፣ ...ወዘተ) በመጠቀም ባለይዞታው ማዳበሪያ ካለው የራሱን በመውሰድ ከሌለው ደግሞ በአካባቢው ማዳበሪያ ያለውን ቤተሰብ በማፈላለግ ይህም ካልሆነ ማዳበሪያ ሊገኝ ከሚችልበት ማለትም ከገበያ፣ ከልማት ወኪሎች ከግብርና መ/ቤቶች ... ወዘተ ለጊዜው በመውሰድ መጀመሪያ ባዶውን ዕቃ ቀጥሎ ደግሞ ማዳበሪያውን አስይዞ ከመዘነ በኋላ የዕቃውን ክብደት በመቀነስ የሚገኘው ክብደት በጥቅም ላይ የዋለውን ማዳበሪያ መጠን ስለሚገልጽ ውጤቱን በጥያቄው በተሰጠው ትይዩ ባዶ ቦታ ይሞላል::

ለበለጠ ማብራሪያ የሚከተለውን ምሣሌ ይመልከቱ :-

ምሣሌ:-

ባለይዞታው አንድ ሣህን ማዳበሪያ በጤፍ ማሳው ላይ እንደተጠቀመና በኪሎ ግራም ምን ያህል እንደሆነ የማያውቅ መሆኑን ቢገልጽ መረጃ ሰብሳቢው በጥቅም ላይ የዋለውን ማዳበሪያ መጠን በኪሎ ግራም በጥያቄ 19.2 ማስፈር ስለሚገባው መጠኑን በኪሎ ግራም ለማግኘት የሚከተለውን አሠራር መከተል ይኖርበታል::

1. ባለይዞታው በጥቅም ላይ ያዋለውን ማዳበሪያ መጠን የለካበትን ዕቃ ባዶውን ይመዝናል:: በዚህ መሠረት የዕቃው ክብደት 500 ግራም ቢሆን፣

2. በመቀጠልም ከባለይዞታው ወይም ከሌሎች ቤተሰቦች ወይም ደግሞ ከገበያ ፣ ከልማት ወኪሎች ... ወዘተ ያገኘውን ማዳበሪያ በዕቃው ወስጦ በማድረግ መዝኖ የተገኘው ክብደት 9.500 ኪሎ ግራም ቢሆን፣

3. በመጨረሻም ማዳበሪያውን ከእነዕቃው መዝኖ ካገኘው ክብደት ዕቃው ባዶውን ተመዝኖ ያገኘውን ክብደት ይቀንሳል:: በዚህም መሠረት 9.500 ኪሎ ግራም ላይ 500 ግራም ሲቀነስ 9 ኪሎ ግራም ይሆናል:: (9.500 - 0.500 = 9.00) ይህ መጠን በጥቅም ላይ የዋለውን የማዳበሪያ መጠን ስለሚገለጽ በጥያቄ 19.2 በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል::

*ማስታወሻ:-*

*ነጭ የማዳበሪያ ዓይነት «ዩሪያ» ሲሆን ቡኒ (ግራይ) ደግሞ «ዳፕ» ነው::*

ጥያቄ 20: - <u>የተፈጥሮ ማዳበሪያ ከተጠቀሙ (በጥያቄ 17 ኮድ «1» ወይም ኮድ «3» ከተሞላ) ዓይነት:-</u>

ባለይዞታው በጥያቄ 17 የተፈጥሮ ማዳበሪያ መጠቀሙን ገልጾ ኮድ «1» ወይም «3» ከተሞላ በዚህ ዓምድ የተጠቀመው የማዳበሪያ ዓይነት ተጠይቆ

የከብቶች ፍግ ከሆነ ኮድ «1»፣ የተለያየ ብስባሽ ከሆነ ኮድ «2»፣ ሁለቱንም ዓይነት የተጠቀመ ከሆነ ኮድ «3» ከእነዚህ ውጪ ሌላ ከሆነ በዚህ ጥያቄ ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ስሙን መዝግቦ ኮድ «4» ይሞላል።

## የቅጽ ግ.ና.ፕ 96/8ለ - በጊዜያዊና ጊዜያዊ፣ በጊዜያዊና ቋሚ፣ ድብልቅ ሰብሎች የተያዙ ማሣዎች ዝርዝርና የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ (በልግ ወቅት) አሞላል

በዚህ ቅጽ በባለይዞታው ቁጥጥር ሥር ያሉ በጊዜያዊና ጊዜያዊ እንዲሁም በጊዜያዊና ቋሚ ድብልቅ ሰብሎች ብቻ የተያዙ ማሣዎች በሙሉ ይመዘገባሉ:: የአመዘጋገቡም ሁኔታ በቦታው ተገኝቶ ማሣዎችን ተዘዋውሮ በማየት የፓርሰልና ማሣ ቁጥሮችን አሰጣጥ ተከታታይነት በቅጽ 96/5ሀ ክፍል 2 ዓምድ 3 ከተሰጡት ጋር በማገናዘብ በድብልቅ ሰብል የተያዙ ማሣዎችን ብቻ ለይቶ ይሆናል::

ክፍል 1. የአካባቢ መለያ

ዓምድ 1 - ክልል

ቆጠራው የሚካሄድበት ክልል ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 2 - ዞን

ቆጠራው የሚካሄድበት ዞን ስም ወይንም ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 3 - ወረዳ

ቆጠራው የሚካሄድበት ወረዳ በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 4 - ገበሬ ማህበር

ቆጠራው የሚካሄድበት የገበሬ ማህበር ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 5 - ቆጠራ ቦታ

ቆጠራው የሚካሄድበት ቆጠራ ቦታ ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 6 - የቤተሰብ መለያ ቁጥር

የተመረጠው ቤተሰብ መለያ ቁጥር ከቅጽ 96/1 ክፍል 2 ዓምድ 1 በመውሰድ ይሞላል::

ዓምድ 7 - የባለይዞታው መለያ ቁጥር

የባለይዞታው መለያ ቁጥር ከቅጽ 96/1 ክፍል 2 ዓምድ 3 በመውሰድ ይሞላል::

ዓምድ 8 - የባለይዞታው ስም

የባለይዞታው ስም ከቅጽ 96/1 ክፍል 2 ዓምድ 4 በመውሰድ ይሞላል::

ዓምድ 9 - ዕድሜ

የባለይዞታው ዕድሜ ተጠይቆ በሙሉ ዓመት በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 10 - ፆታ (ወንድ = 1 ሴት = 2)

የባለይዞታው ፆታ ወንድ ከሆነ ኮድ «1» ሴት ከሆነች ኮድ «2» በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 11 - የትምህርት ሁኔታ የፈፀሙት ከፍተኛ ክፍል (አምስት ዓመትና በላይ ለሆኑ ባለይዞታዎች)

በዚህ ዓምድ ዕድሜያቸው 5 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ ባለይዞታዎች የትምህርት ሁኔታ (የፈፀሙት ከፍተኛ ክፍል) ተጠይቆ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ኮዶች ትክክለኛው ተመርጦ ይሞላል። በመጀመሪያ ባለይዞታው ማንበብና መፃፍ የሚችል መሆኑ ከተጠየቀ በኋላ የሚችል ከሆነ ተምሮ የጨረሰው ከፍተኛ ክፍል ይጠየቃል። አንድ ግለሰብ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ አለው የሚባለው በማንኛውም ግለሰብ በሚያውቀው ቋንቋ አንብቦ መረዳትና መፃፍ ሲችል ብቻ ነው። የራሳቸውን ስም ወይንም ቁጥሮችን ብቻ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ግለሰቦች እንደተማሩ አይቆጠሩም። በተጨማሪም የፈፀመው ክፍል ሲባል በቆጠራው ወቅት የሚገኝበት ክፍል ሳይሆን ተምሮ የጨረሰው ከፍተኛ ክፍል ማለት ነው። (የትምህርት ሁኔታ ኮድ ከገጽ 32 ይመልከቱ)

ዓምድ 12 - የቤተሰብ አባላት ብዛት

በዓምድ 7 መለያ ቁጥሩ የተመዘገበው እያንዳንዱ ባለይዞታ ተጠይቆ መደበኛ የቤተሰብ አባላት ብዛት በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 13 - የግብርናው ዓይነት /ሰብል = 1 ከብት = 2 ሁለቱም = 3/

በዓምድ 7 መለያ ቁጥሩ የተመዘገበው እያንዳንዱ ባለይዞታ የተሠማራበት የግብርና ዓይነት ተጠይቆ ሰብል ማምረት ብቻ ከሆነ ኮድ «1» ከብት ማርባት /ማደለብ/ ብቻ ከሆነ ኮድ «2» ሁለቱም ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» በዚህ ዓምድ ይሞላል።

## ክፍል 2. በድብልቅ ሰብሎች (አትክልትና ሥራሥር ጨምሮ) የተያዙ ማሣዎች ስፋትና የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ

ይህ ክፍል የሚያገለግለው ባለይዞታው በ1996 ዓ.ም በልግ ወቅት ያለውን በድብልቅ ሰብል የተያዘ ማሣዎች ስፋትን ከጊዜያዊ ሰብሎች የተገኘውን /ሊገኝ የሚችለውን ምርት መጠን በሰብል ዓይነትና የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ መረጃዎችን ለመመዝገብ ነው:: በዚህ ክፍል 2 ድብልቅ ሰብል የተያዙ ማሣዎችን መረጃ ሊያሰበስብ የሚያስችል ቦታ በዓምድ 3ና4 ተሰጥቷል:: ከሁለት በላይ በድብልቅ ሰብል የተያዙ ማሣዎች ሲያጋጥም በቅጹ ጀርባ የሚገኘውን ቀጣይ ገጽ መጠቀም ያስፈልጋል::

ዓምድ 1 - ተራ ቁጥር

ተራ ቁጥር በቅደም ተከተል ተሞልቷል::

ዓምድ 3-4 - የፓርስል ቁጥር ፣ የማሣ ቁጥርና የሰብል ስም

የፓርስል ቁጥር

መረጃ የሚሰበስብላቸው በድብልቅ ሰብል የተያዙ ፓርስሎች በሙሉ የፓርስል ቁጥራቸው ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/8ሀ ከተመዘገበው ጋር በማገናዘብ ተከታታይነቱን በመጠበቅ ይሰጣል::

የማሣ ቁጥር

መረጃ የሚሰበሰብላቸው በድብልቅ ሰብል የተያዙ ማሣዎች በሙሉ የማሣ ቁጥራቸው ከቅጽ ግ.ና.ጥ 96/8ሀ የተሰጠውን መሠረት በማድረግና የማሣ ፍቺን በጠበቀ መልኩ ተከታታይ ቁጥር በመስጠት ይሞላል::

የሰብል ስም

የባለይዞታው በሆኑ በድብልቅ ሰብል በተያዙ ማሣዎች ላይ የሚገኙ ድብልቅ ሰብሎች ስማቸው ለየብቻ ተዘርዝሮ በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ይመዘገባል:: በድብልቅ ሰብሎች ለተያዘ አንድ ማሣ በማሣው ላይ ለ«3» የድብልቅ ሰብሎች ስም መመዝገቢያ የሚሆን ቦታ ተዘጋጅቷል:: ሆኖም ማሳው የያዘው ከ«3» በላይ የድብልቅ ሰብሎችን ከሆነ እያንዳንዱ ድብልቅ ሰብል ከጠቅላላው የማሣ ስፋት ያለውን ድርሻ በማወዳደር ከፍተኛውን የማሣ ድርሻ የያዙትን «3» ድብልቅ ሰብሎች ብቻ በመውሰድ በዚህ ዓምድ በተሰጡት ባዶ ቦታዎች የ«3»ቱ ድብልቅ ሰብሎች ስም ብቻ በዝርዝር ይመዘገባል:: በዚህ ዓምድ ለኮድ የተተወው ቦታ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም:: በዚህ ቅጽ ሁለት የድብልቅ ሰብል የተያዙ ማሣዎች መረጃን ሊያስሞላ የሚችል ቦታ (በዓምድ 3ና4) ተሰጥቷል:: ከሁለት በላይ በድብልቅ ሰብል የተያዙ ማሣዎች ሲያጋጥም

ጀርባውን መጠቀም ያስፈልጋል። ከአራት በላይ የድብልቅ ማሣዎች ሲያጋጥም ግን ተጨማሪ ቅጽ መጠቀም ያስፈልጋል።

ጥያቄ 1 - 21:- ለባለይዞታው የሚቀርቡ ጥያቄዎች

ጥያቄ 1:- የይዞታው ዓይነት:- ባለይዞታው ያስመዘገበው እያንዳንዱ ማሣ በማስመልከት ተጠይቆ ማሳው የባለይዞታው የራሱ ከሆነ ኮድ «1»፣ በኪራይ ወይም በኮንትራት የተያዘ ከሆነ ኮድ «2»፣ ከእነዚህ ከሁለቱ ውጭ የተገኘ ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

ጥያቄ 2:- ማሣው በኤክስቴንሽን መግሀ-ግብር ታቅፏል?

(አዎ = 1 አልታቀፉም = 2)

ባለይዞታው ያስመዘገበው እያንዳንዱ በድብልቅ ሰብል የተያዘ ማሣ በኤክስቴንሽን መርሀ-ግብር መታቀፍ አለመታቀፉ ተጠይቆ ከታቀፈ ኮድ «1» ካልታቀፈ ደግሞ ኮድ«2» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

ጥያቄ 3:- ድብልቅ ሰብሉ የያዘው ማሣ ስፋት በስታንደርድ/ በአካባቢ መለኪያ

ባለይዞታው ያስመዘገበው እያንዳንዱ በድብልቅ ሰብል የተያዘ ማሣ ስፋት በስታንደርድ ወይም በአካባቢ መለኪያ ተጠይቆ በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ የመለኪያው ስምና የስፋት መጠን ይሞላል።

ጥያቄ 4:- የምርት መጠን በስታንደርድ /በአካባቢ መለኪያ፡

ባለይዞታው ከእያንዳንዱ ድብልቅ ሰብል ያመረተው/ሊያመርት የሚችለው የምርት መጠን በስታንደርድ ወይም በአካባቢ መለኪያ ስንት እንደሆነ ተጠይቆ የመለኪያ ስምና የተመረተው ምርት መጠን በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል። ድብልቅ ሰብሉ የጊዜያዊና የቋሚ ሰብል ከሆነ ግን መረጃው ለጊዜያዊው ሰብል ብቻ ይሞላና ለቋሚው በሠረዝ ይታለፋል።

ጥያቄ 5:- ማሣው ላይ ያሉ ሰብሎች የያዙት ስፋት (በመቶኛ):-

በድብልቅ ሰብሎች የተያዘ ማሣን አስመልክቶ እያንዳንዱ ሰብል ከጠቅላላው የማሣ ስፋት የያዘው የመሬት ስፋት ድርሻ በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ባለይዞታው ተጠይቆ ይሞላል። ከ«3» በላይ ድብልቅ ካጋጠመ የማሣው ከፍተኛ ድርሻ ላላቸው «3» ሰብሎች ብቻ ድርሻቸው በመቶኛ ተጠይቆ

ይመዘገብላቸዋል፡፡ የቀሪዎቹም ድርሻ ለሦስቱ ዋና ዋና ሰብሎች ይከፋፈላል፡፡

ጥያቄ 6፡- የመስኖ ዘዴ ተጠቅመዋል? (አዎን = 1 የለም = 2)

ባለይዞታው በእያንዳንዱ ማሣ ላይ ያሉትን ድብልቅ ሰብሎች ለማምረትም ሆነ ምርትን ለማሻሻል የመስኖ ዘዴ የተጠቀመ ከሆነ ኮድ «1» ፥ በመስኖ ካልተጠቀመ ደግሞ ኮድ «2» ይሞላል፡፡

ጥያቄ 7፡- የዘር /የችግኝ/ ዓይነት (ምርጥ ዘር = 1 ምርጥ ዘር ያልሆነ = 2)

ባለይዞታው በድብልቅ ለዘራቸው /ለተከላቸው ሰብሎች ለእያንዳንዳቸው የተጠቀመው የዘር /የችግኝ/ ዓይነት ተጠይቆ ምርጥ ዘር ከሆነ ኮድ «1»፣ ምርጥ ዘር ካልተጠቀመ ደግሞ ኮድ «2» ይሞላል፡፡

ጥያቄ 8፡- ምርጥ ዘር ካልሆነ (መጠን በኪ.ግራም)

ባለይዞታው በጥያቄ 7 ላይ ምርጥ ያልሆነ ዘር ተጠቅሜአለሁ ብሎ ኮድ «2» ከተሞላ በዚህ ጥያቄ ደግሞ የተጠቀመው የአካባቢ ዘር መጠኑ በኪሎ ግራም ተጠይቆ በተሰጠው ቦታ ይሞላል፡፡ ጥያቄው የሚመለከተው የብርዕ፣ አገዳ፣ ጥራጥሬና ቅባት ሰብሎችን ብቻ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡

ጥያቄ 9፡- ምርጥ ዘር ከሆነ መጠን በኪ.ግራም

በጥያቄ 7 ባለይዞታው ምርጥ ዘር መጠቀሙን ገልጾ ኮድ «1» ከተሞላ በዚህ ጥያቄ ደግሞ የተጠቀመው የምርጥ ዘር መጠን ተጠይቆ መጠኑ በኪሎ ግራም በተሰጠው ቦታ ይሞላል፡፡ ጥያቄው የሚመለከተው የብርዕ፣ የአገዳ፣ የጥራጥሬና የቅባት ሰብሎችን ብቻ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡

ጥያቄ 10፡- ምርጥ ዘር ከሆነ ዋጋ

ባለይዞታው በጥያቄ 7 ምርጥ ዘር ተጠቅመዋል ተብሎ የዘሩ መጠን በጥያቄ 9 ከተሞላ የተጠቀመው ምርጥ ዘር ዋጋ ተጠይቆ በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል፡፡ ዋጋ ችግኝን አይመለከትም፡፡

ጥያቄ 11:- የሰብል ብልሽት ደርሷል ወይ? (አዎን = 1 የለም = 2)

በድብልቅ የሚገኙትን እያንዳንዱን ሰብል አስመልክቶ የሰብል መበላሸት ደርሶ ከሆነ ኮድ «1» ካልደረሰ ደግሞ ኮድ «2» ባለይዞታው ተጠይቆ ይሞላል።

ጥያቄ 12:- የሰብል መበላሸት ደርሶ ከሆነ የብልሽቱ አንድ ዋና ምክንያት

ይህ ጥያቄ የሚመለሰው በጥያቄ 11 የሰብል መበላሸት ደርሷል ተብሎ ኮድ «1» ከተሞላ ብቻ ነው። ለሰብሉ መበላሸት አንድ ዋና ምክንያት ብቻ በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ መገለጽ አለበት። ለሰብል መበላሸት ምክንያት በገጽ 19 የተዘረዘሩትን ይመልከቱ። ለኮድ የተተወው ቦታ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም።

ጥያቄ 13:- የብልሽት መጠን በመቶኛ

በጥያቄ 12 በተገለጸው ምክንያት በሰብል ላይ ጉዳት የደረሰ ከሆነ በማሳው ላይ የሚገኙትን እያንዳንዱን ሰብል አስመልክቶ የደረሰውን ጉዳት መጠን በመቶኛ በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይገለጻል።

ጥያቄ 14:- ብልሽቱን ለመከላከል /ለጥንቃቄ/ የተወሰደ እርምጃ?
(አለ = 1 የለም = 2)

ባለይዞታው የደረሰበትን የሰብል ብልሽት ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ ወይም ለጥንቃቄ አስቀድሞ የወሰደው እርምጃ ካለ ኮድ «1» ከሌለ ደግሞ ኮድ «2» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

ጥያቄ 15:- የተወሰደ እርምጃ ዓይነት (ኬሚካል /የኢንዱስትሪ ውጤት የሆነ/ = 1
ኬሚካል ያልሆነ = 2 ሁለቱም = 3)

ባለይዞታው የሰብሉን ብልሽት ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ ወይም ለጥንቃቄ አስቀድሞ እርምጃ ወስዶ በጥያቄ 14 ኮድ «1» ከተሞላ የወሰደው እርምጃ ዓይነት ኬሚካል መጠቀም ከሆነ ኮድ «1» ፣ ኬሚካል ካልሆነ ኮድ «2» ሁለቱንም ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

ጥያቄ 16:- ኬሚካል ከተጠቀሙ ዓይነቱ

ባለይዞታው በጥያቄ 15 የወሰደው የእርምጃ ዓይነት ኬሚካል ከሆነ (በጥያቄ 15 ኮድ «1» ወይም ኮድ «3» ከተሞላ) ዓይነቱ ተጠይቆ ፀረ-

ተባይ ከሆነ ኮድ «1» ፤ ፀረ-አረም ከሆነ ኮድ «2» ፤ ፀረ-በሽታ ከሆነ ኮድ «3»፣ ፀረ-ተባይና ፀረ-አረም ከሆነ ኮድ «4» ፀረ-ተባይና ፀረ-በሽታ ከሆነ ኮድ «5» ፤ ፀረ-አረምና ፀረ-በሽታ ከሆነ ኮድ «6» ፤ እንዲሁም ሁሉንም ዓይነት ከሆነ ኮድ «7» ይሞላል።

<u>ጥያቄ 17:-</u> <u>የተፈጥሮ /ኬሚካል ማዳበሪያ ተጠቅመዋል?</u>
<u>(አዎን = 1 የለም = 2)</u>

ባለይዞታው በድብልቅ ሰብል የተያዘ እያንዳንዱ ማሣ ላይ የሚገኘውን /የተገኘውን ምርት ለማሻሻል የተፈጥሮም ይሁን የኬሚካል ማዳበሪያ ተጠቅሞ ከሆነ ኮድ «1» ካልተጠቀመ ደግሞ ኮድ «2» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

<u>ጥያቄ 18:-</u> <u>ማዳበሪያ ከተጠቀሙ ዓይነቱ (የተፈጥሮ = 1 ኬሚካልና = 2 ሁለቱም = 3)</u>

በጥያቄ 16 ባለይዞታው ማዳበሪያ ተጠቅሞ ኮድ «1» ከተሞላ የማዳበሪያው ዓይነት ተጠይቆ ጥቅም ላይ የዋለው የማዳበሪያ ዓይነት የተፈጥሮ ከሆነ ኮድ «1» ኬሚካል ከሆነ ኮድ «2» ሁለቱም ዓይነት ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

<u>ጥያቄ 19:-</u> <u>ኬሚካል ማዳበሪያ ካልተጠቀሙ አንድ ዋና ምክንያት</u>
<u>(ጥያቄ 17 ኮድ «2» ወይም ጥያቄ 18 ኮድ «1» ከተሞላ</u>

ባለይዞታው ማዳበሪያ መጠቀም አለመጠቀሙ በጥያቄ 17 ላይ ተጠይቆ ኮድ «2» ከተሞላ ወይም ተጠቅሞ በጥያቄ 18 ኮድ «1» ከተሞላ ኬሚካል ማዳበሪያ ያልተጠቀመበት ምክንያት ተጠይቆ በጥያቄ ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይመዘገባል። የምክንያቶቹን ዝርዝር በገጽ 33 የቀረበ ሲሆን እነዚህን በመጠቀም ትክክለኛውን ኮድ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል።

*<u>ማሳሰቢያ:-</u> ባለይዞታው በተለያዩ ሰብሎች የተያዙ ማሳዎችን በተመለከተ ኬሚካል ማዳበሪያ ለምን እንደተጠቀመ ተጠይቆ የሰጠው መልስ ከኮድ 2-6 ቢያንስ አንዱን ከመለሰ ሌሎች ሰብሎችን ግን ኮድ 1 «ጥቅሙን ካለማወቅ» የሚል መልስ መሞላት የለበትም። መልስ ሰጪው ይህንን መልስ ከሰጠ ግን መረጃ ሰብሳቢው ተጨማሪ የማውጣጣት ጥያቄዎችን ለባለይዞታው በማቅረብ ተገቢውን ኮድ መሙላት ይኖርበታል።*

ጥያቄ 20:- ኬሚካል ማዳበሪያ ከተጠቀሙ (በጥያቄ 18 ኮድ «2» ወይም ኮድ «3» ከተሞላ)

ጥያቄ 20.1:- ዓይነት

ባለይዞታው የተጠቀመው ማዳበሪያ ኬሚካል ከሆነ የተጠቀመው ማዳበሪያ ዓይነት ተጠይቆ ዩሪያ ከሆነ ኮድ «1» ዳፕ ከሆነ ኮድ «2» ሁለቱም ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ጥያቄ 20.2:- መጠን

በጥያቄ 20.1 የተገለጸውና ባለይዞታው የተጠቀመው ማዳበሪያ ዓይነት መጠን ተጠይቆ በኪሎ ግራም በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል:: ባለይዞታው መጠኑን የማያውቅ ከሆነ በገጽ 45 እና 46 የተሰጠው የአሠራር ዘዴ መከተል ያስፈልጋል::

ጥያቄ 21:- የተፈጥሮ ማዳበሪያ ከተጠቀሙ (በጥያቄ 18 ኮድ «1» ወይም «3» ከተሞላ) ዓይነት

ባለይዞታው በጥያቄ 18 የተፈጥሮ ማዳበሪያ መጠቀሙን ገልጾ ኮድ «1» ወይም «3» ከተሞላ የተጠቀመው የማዳበሪያ ዓይነት ተጠይቆ የከብቶች ፍግ ከሆነ ኮድ «1» የተለያየ ብስባሽ ከሆነ ኮድ «2» ሁለቱም ዓይነት ከሆነ ኮድ «3» ከነዚህ ውጭ ሌላ ከሆነ ደግሞ ዓይነቱ ተገልጾ ኮድ «4» በጥያቄው ትይዩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል::

*ማስታወሻ:- በበልግ ወቅት በጊዜያዊ ሰብል (አትክልትና ሥራሥርን ጨምሮ) የተያዙ ማሣዎች በሙሉ ማለትም በቋሚ ሰብልና በሌላ መሬት አጠቃቀም የተያዙ መሬቶችን ሳይጨምር በገጽ እና የተገለጸውን የማሣ አለካክ መመሪያ በመጠቀም የማሣ ልኪ ይካሄድላቸዋል:: ከዚህ የተገኘ መረጃም በቅጽ 96/4 ላይ ይሞላል::*

## የቆጠራ ቦታ ካርታ አጠቃቀም

ለጥናቱ በተመረጠ ቆጠራ ቦታ የሚመደብ መረጃ ሰብሳቢ ጥናቱ ከመጀመሩ በፊት በተቆጣጣሪው አማካኝነት የተመደበበትን የቆጠራ ቦታ ካርታ እና ስለ ቆጠራው ቦታ የሚገልጽ የቆጠራ ቦታ መግለጫ ጽሁፍ ይደርሰዋል። በተጨማሪም ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መግለጫዎች መሠረት ስለቆጠራው ቦታ ካርታ በዝርዝር ማወቅ ይገባዋል።

1. መረጃ ሰብሳቢው የተመደበበትን የቆጠራ ቦታ በሚገባ ለማወቅ ይችል ዘንድ በመጀመሪያ የተሰጠውን የቆጠራ ቦታ ካርታ ማጥናት ይኖርበታል። ለዚህም የተመደበበት የቆጠራ ቦታ ካርታ ይዘት ምን እንደሆነ በሚቀጥለው ገጽ በፊደል «ሀ» ውስጥ የተዘረዘሩትን ማጥናት አለበት።

2. መረጃ ሰብሳቢው ከካርታው ጋር የተያያዘውን የካርታ መግለጫ ጽሁፍ በሰሜን፣ በምሥራቅ፣ በደቡብ እና በምዕራብ አቅጣጫዎች የቆጠራ ቦታውን የወሰን መግለጫ ደጋግሞ በማንበብ በካርታው የሚታዩትን ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ነገሮች መሬት ላይ ካሉት ጋር ማገናዘብ ይኖርበታል።

3. በቆጠራ ቦታ ካርታ ላይ ከሚገኙ ዓብይ ነጥቦች ውስጥ አንዱ የቆጠራ ቦታው ድንበር ነው። የድንበሩ ዓላማ ቆጣሪው ከተወሰነለት ክልል እንዳይወጣ እና በክልሉ ውስጥ ያሉትን ቤተሰቦችና ቤቶች ለመመዝገብ እንዲችል ነው። መረጃ ሰብሳቢው ይህን በመረዳት በቆጠራው ቦታ ካርታ ላይ የተገለጸውን ድንበር ጠንቅቆ በማወቅና በመሬት ላይም ለመለየት መቻል አለበት። በአንዳንድ የቆጠራ ቦታ ካርታ ላይ የተገለጸው ድንበር ምናልባት በአካባቢው ያሉትን ቋሚ ነገሮች ሳይጠቅስ ሊቀር ይችላል። ይህን እና ይህን የመሳሰሉ ችግሮች ለማስወገድ መረጃ ሰብሳቢው የቆጠራ ቦታውን እየተዘዋወረ በሚያጠናበት ወቅት የገበሬ ማህበሩ ሊቀመንበር ወይም ተወካይ አብሮ መዞርና ዳር ድንበሩን ማሳየትና ማረጋገጥ አለበት።

4. መረጃ ሰብሳቢው የቆጠራ ቦታውን ድንበር በአመቺ መንገድ ለማወቅ ይችል ዘንድ ከቆጠራ ቦታ ካርታው ጋር አብሮ ከሚሰጠው የካርታ መግለጫ ላይ በተገለጸው መሠረት ከሰሜን በመነሳት ጉዞውን ይጀምራል። ይህን ለማድረግ መረጃ ሰብሳቢው በካርታው ላይ የሰፈሩትን የመንደር ስሞች፣ የወንዝ ስም፣ ለምልክትነት የተጻፉ የግለሰቦች ቤት የቆጠራ ቦታውን የሚያዋስኑ ቀበሌ ገበሬ ማህበር፣ ወረዳ፣ ቆጠራ ቦታ ... ወዘተ እየጠየቀና እያገናዘበ ቦታዎቹን ለይቶ ማወቅ አለበት።

አንድ መረጃ ሰብሳቢ በተመደበበት የቆጠራ ክልል በሚዘዋወርበት ወቅት ልዩ ልዩ ችግሮች ሊያጋጥሙት ይችላሉ። ይኸውም የካርታው ሥራ በሚሠራበት ወቅት ምንም ያልተሸፈነ ቦታ ሳይተው ወይም ቦታዎች ሳይደራረቡ እንዲሠሩ ከፍተኛ ሙከራ ቢደረግም አንዳንድ ጊዜ በቆጠራው

ቦታ ወይም በአዋሳኝ የቆጠራ ቦታ መሀከል ያልተሸፈኑ ቦታዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም በሁለት የቆጠራ ቦታዎች መሀከል ያለ ቦታ በሁለት የቆጠራ ቦታዎች ውስጥ ሊደራረብ ይችላል፡፡

የዚህ ዓይነት ችግር በሁለት የቆጠራ ቦታዎች ድንበር ላይ በሚያጋጥም ወቅት መረጃ ሰብሳቢው ይህን ችግር ለተቆጣጣሪው በማስታወቅ እቦታው ድረስ በመሄድ ድንበሩን ማስተካከል ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ዓይነቱ ሥራ መረጃ ሰብሳቢው የቤተሰብ ምዝገባ ከማድረጉ በፊት መሆን አለበት፡፡ መረጃ ሰብሳቢው በሚሰጠው የቆጠራ ቦታ ካርታ በመጠቀም የቆጠራ ቦታዎችን ድንበር በሚገባ አውቆ ከለየ በኋላ የቤተሰብ ምዝገባ ሊጀምር ይችላል፡፡

ካርታው የጎላ ስህተት ከታየበት እርማት ማድረግ የሚቻለው ከተቆጣጣሪው ጋር በመወያየት ብቻ ነው፡፡ ስለ ቆጠራ ካርታ ይዘት በሚገባ ለመረዳት በሚከተሉት ገጾች ተያይዘው የቀረቡትን ካርታዎችና መግለጫዎች መመልከት ያስፈልጋል፡፡

<u>የቆጠራ ቦታ ካርታዎች ይዘት</u>

ሀ. <u>የገጠር ቆጠራ ቦታ ካርታዎች ይዘት</u>

1. በገጠር የሚገኝ የቆጠራ ቦታ ካርታ የሚከተሉት ነጥቦች ይገኙበታል፣

1.1 የቆጠራው ቦታ የሚገኝበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ እና ገበሬ ማህበር ስም

1.2 የቆጠራው ቦታ የሚገኝበት የገበሬ ማህበር ሊቀመንበር ስም

1.3 የቆጠራው ቦታ መለያ ቁጥር (ኮድ)

1.4 በቆጠራ ቦታ ክልል ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦች ብዛት

1.5 የቆጠራ ቦታ ግምታዊ ስፋት

1.6 የቆጠራ ቦታ ድንበርና ትክክለኛ ስምና አቀማመጥ

1.7 በቆጠራው ቦታ ክልል ውስጥ የሚገኙ መንደሮች ትክክለኛ አቀማመጥና ስማቸው

1.8 በቆጠራው ቦታ ክልል ውስጥ እና ድንበር አካባቢ የሚገኙ አንዳንድ ቤቶች፣ ወንዝ፣ መንገድ ... ወዘተ

1.9 የቆጠራውን ቦታ የሚያዋስኑ የክልል ወይም ዞን ወይም ወረዳ ወይም ገበሬ ማህበር ወይም ሌላ ቆጠራ ቦታ ስም

1.10 የቆጠራው ቦታ ሰሜናዊ አቅጣጫ


1.11 በቆጠራው ቦታ ክልል ውስጥ የሚገኙ ምልክቶች መግለጫ (ሌጀንድ)

1.12 የካርታው መስፈርት

መረጃ ሰብሳቢው ከላይ የተጠቀሱትን ዝርዝር ነጥቦች በተመደበበት የቆጠራ ቦታ ካርታ ላይ መኖራቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ለምሣሌነት እንዲያገለግል የገጠር የቆጠራ ቦታ ካርታ ከነመግለጫው ከዚህ በታች ተመልክቷል፡፡

| | |
|---|---|
| ክልል | 4 |
| ዞን | ጂማ |
| ወረዳ | ማና |
| የገበሬ ማህበር ስም | በበሳ ሸመጠሜ |

| | |
|---|---|
| የሊቀመንበር ስም | ከድር ማሞ አባገሮ |
| የቤተሰብ ብዛት | 195 |
| የቆጠራ ቦታ ቁጥር | 031-03 |
| የጥናቱ ሰዓት | 7.25 ሰ.ዓ.ም |



መስፈርት 1:50.000

መግለጫ

የወረዳ ወሰን
የገበሬ ማህበር ወሰን
የቆጠራ ቦታ ወሰን
የእግር መንገድ
የሚፈስስ ወንዝ
መንደር
ከተማ
ቤተ ክርስቲያን
ቆርቆሮ ቤት
ሣር ቤት

| | ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| ካርታ ሠራተኛ | ዓለማየሁ ሀይፍርጊስ | [signature] | 18-7-85 |
| ተቆጣጣሪ | ፕሰሁን ደምሴ | [signature] | 07-8-85 |

## CENTRAL STATISTICAL AUTHORITY

### DESCRIPTION FORM FOR RURAL ENUMERATION AREA

FORM R-8

**PART 1: AREA IDENTIFICATION**

| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|
| REGION [illegible] 4 | AWRAJA H3- [illegible] 09 | WEREDA 095 | PA/SO NAME [illegible] [redacted] | E.A CODE 03 |

**PART 2: E.A DESCRIPTION**

DESCRIBE THE IDENTIFIABLE BOUNDARIES FROM NORTH AND COMPLETE IN CLOCKWISE DIRECTION

ሰሜን፡- [illegible]

ምሥራቅ፡- [illegible]

ደቡብ፡- [illegible]

ምዕራብ፡- [illegible]

NB:- USE ADDITIONAL FORM IF NEEDED
ATTACH THIS FORM TO E.A MAP

NAME OF EA [illegible] SIGNATURE [illegible] DATE 18-07-85

NAME OF SUPERVISOR [illegible] SIGNATURE [illegible] DATE 18-7-85

# APPENDIX - III

## LEGEND

### A. BOUNDARIES

1 INTERNATIONAL BOUNDARY
2 ADMINISTRATIVE REGION BOUNDARY
3 AWRAJA BOUNDARY
4 WEREDA BOUNDARY
5 SUPERVISION AREA BOUNDARY
(Thick solid line in red)
6 F A / SUBDIVISION / KEBELE BOUNDARY
7 E.A. BOUNDARY

### B. CULTURAL FEATURES

1 LARGE SETTLEMENT
2 CIRCULAR HOUSE, RECTANGULAR HOUSE
3 CHURCH, MOSQUE, CHURCH WITH CEMETRY
4 SCHOOL, CHURCH AND SCHOOL (Joint use)
5 HOSPITAL, CLINIC, HEALTH CENTRE
6 MARKET PLACE
7 ALL WEATHER ROAD
8 DRY WEATHER ROAD
9 TRAIL / FOOT PATH
10 RAILWAY LINE
11 ANTIQUITY, RUIN
12 HISTORICAL SITE (Battle field)
13 MINERAL WORKING-QUARRY
14 CEMETRY: CHRISTIAN, MUSLEM
15 BRIDGE (Road)
16 FLOUR MILL (WATER OR OTHERS)
17 SAW MILL


N.B. Where two or more boundaries coincide only the symbol representing the higher ranking boundary is shown

18· A ADMINISTRATIVE OFFICE
19· H HOTEL
20· HA PERMANENT HIGHWAY CAMP
21· PO POST OFFICE
22· PS POLICE STATION
23· ■ ........................ ADMINISTRATIVE REGION CAPITAL
24· ◉ ........................ AWRAJA CAPITAL
25· ● ........................ WEREDA CAPITAL
26· • ........................ OTHER TOWN
27· PP POLICE POST
28· Tele TELE OFFICE
29· F·S FILLING STATION
30· AIRFIELD (airstrip)
31· FACTORY

## C. VEGETATION (ABBREVIATION USED)

1· DF DENSE FOREST
2· O·W OPEN WOODLAND
3· E EUCALYPTUS
4· G GRASS LAND
5· SC SCRUB
6· PLANTATION
- a. C COFFEE
- b. CN COTTON
- c. O ORANGE (citrus fruit)
- d. S SISAL
- e. SU SUGAR-CANE
- f. T TEA
- g. VY VINE YARD (grapes)
- h. CH CHAT
- i. ET ENSET
- j. OS OIL SEEDS

## D. NATURAL FEATURES



1· PERENNIAL STREAM
2· INTERMITTENT STREAM
3· DISAPPEARING STREAM
4· WELL, SPRING, WATER HOLE, WATER TANK
5· RESERVIOUR, DAM
6· SWAMP OR MARSH
7· AREA SUBJECT TO INUNDATION
8· WATER FALL
9· LAKE
10· MOUNTAIN
11· SINK OR DEPRESSION
12· LAVA
13· VALLEY

ዕዝል -1

## ዋና ዋና ታሪካዊ ድርጊቶች ዝርዝር

| ተራ ቁጥር | ታሪካዊ ድርጊቶች | ድርጊቱ የተፈፀመበት ዓመተ ምሕረት | ድርጊቱ ከተፈጸመበት እስከ 1996 ዓ.ም ያሉት ዓመታት ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | ቀዳማይ ኃይለ ሥላሴ የተወለዱበት | 1884 | 112 |
| 2 | ዝዋይ የተወረረበት/ ከጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ ያለው የባቡር መስመር የተዘረጋበት | 1886 | 110 |
| 3 | የወላሞ ዘመቻ የተደረገበት | 1887 | 109 |
| 4 | ራስ መንገሻና ራስ አሉላ ከኢጣሊያ ወታደር ጋር በኩዓቲት ላይ ጦርነት የገጠሙበት | 1887 | 109 |
| 5 | ራስ መንገሻ በኩዓቲትና በሰንዓፌ ላይ በኢጣሊያ ድል የሆኑበት | 1887 | 109 |
| 6 | የዓድዋ ድል የተገኘበት | 1888 | 108 |
| 7 | ንጉስ ተክለሃይማኖት ያረፉበት | 1893 | 103 |
| 8 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጋራ ሙለታ ደጃዝማች ተብለው የተሾሙበት | 1897 | 99 |
| 9 | ልዑል ራስ መኮንን ያረፉበት | 1898 | 98 |
| 10 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሲዳሞ የተሾሙበት | 1900 | 96 |
| 11 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐረርጌ የተሾሙበት | 1902 | 94 |
| 12 | አፄ ምኒሊክ ያረፉበት/ልጅ እያሱ የነገሱበት | 1906 | 90 |
| 13 | ራስ ሚካኤል በወሎ በትግራይና በጎጃም የነገሱበት | 1907 | 89 |
| 14 | ንግስት ዘውዲቱ የነገሱበት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አልጋ ወራሽ የሆኑበት | 1909 | 87 |
| 15 | የሰገሌ ጦርነት የተካሄደበት | 1909 | 87 |
| 16 | እቴጌ ጣይቱ ያረፉበት | 1910 | 86 |
| 17 | የኅዳር በሽታ የነበረበት | 1911 | 85 |
| 18 | ልጅ እያሱ የተያዙበት | 1913 | 83 |
| 19 | ኢትዮጵያ የዓለም መንግሥታት ማኅበር አባል የሆነችበት | 1916 | 80 |
| 20 | የባሪያ ነፃነት ደንብ የወጣበት | 1916 | 80 |
| 21 | ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት የተቋቋመበት | 1917 | 79 |

## ዋና ዋና ታሪካዊ ድርጊቶች ዝርዝር

| ተራ ቁጥር | ታሪካዊ ድርጊቶች | ድርጊቱ የተፈፀመበት ዓመተ ምሕረት | ድርጊቱ ከተፈፀመበት እስከ 1996 ዓ.ም. ያሉት ዓመታት ብዛት |
|---|---|---|---|
| 22 | ፊታውራሪ ኃብተ ጊዮርጊስ ማተሚያ ቤት የተቋቋመበት | 1918 | 78 |
| 23 | አቡነ ማቴዎስ ያረፉበት | 1919 | 77 |
| 24 | ንግስት ዘውዲቱ ያረፉበት | 1922 | 74 |
| 25 | ራስ ጉግሳ ወሌ በጎንደር የሞቱበት | 1922 | 74 |
| 26 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የነገሱበት | 1923 | 73 |
| 27 | የወልወል ግጭት የተደረገበት | 1927 | 69 |
| 28 | የማይጨው ጦርነት የተካሄደበት ኢጣልያ ወደ ኢትዮጵያ የገባችበት | 1928 | 68 |
| 29 | የኢትዮጵያ ሰማዕታት ቀን | 1929 | 67 |
| 30 | በጂማ ገነቴ ላይ የአርበኞች ውጊያ የተደረገበት | 1930 | 66 |
| 31 | እንግሊዝ ኢጣልያን ከኢትዮጵያ ለማስወጣት የመጣበት | 1933 | 63 |
| 32 | ኢጣልያን ድል የተመታችበት | 1933 | 63 |
| 33 | ለኢትዮጵያ ሰማዕታት ሀውልት የተሰራበት | 1937 | 59 |
| 34 | አቡነ ባስሊዎስ ሊቀ ጳጳስ የሆኑበት | 1943 | 53 |
| 35 | ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌደሬሽን የተዋሃደችበት | 1943 | 53 |
| 36 | የሸንቁጤ ረሃብ በቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ዘመን የገባበት | 1950 | 46 |
| 37 | እነጄኔራል መንግሥቱ ነዋይ የቀዳማዊ ኃ/ሥላሴን መንግሥት ለመገልበጥ ሙከራ ያደረጉበት | 1953 | 43 |
| 38 | ኤርትራ ከኢትዮጵያ የተዋሃደችበት | 1955 | 41 |
| 39 | የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተቋቋመበት | 1955 | 41 |
| 40 | ኮሌራ በሽታ የገባበት | 1963 | 33 |
| 41 | የኢትዮጵያ አብዮት የፈነዳበት | 1966 | 30 |
| 42 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን የወረዱበት | 1967 | 29 |

## ዋና ዋና ታሪካዊ ድርጊቶች ዝርዝር

| ተራ ቁጥር | ታሪካዊ ድርጊቶች | ድርጊቱ የተፈፀመበት ዓመተ ምሕረት | ድርጊቱ ከተፈፀመበት እስከ 1996 ዓ.ም. ያሉት ዓመታት ብዛት |
|---|---|---|---|
| 43 | የዕድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ በዓል የተከበረበት | 1967 | 29 |
| 44 | የገጠር መሬት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት | 1967 | 29 |
| 45 | የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት | 1967 | 29 |
| 46 | ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ያረፉበት | 1967 | 29 |
| 47 | የእናት አገር ጥሪ የተደረገበት | 1969 | 27 |
| 48 | ኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮ. የተመሰረተበት | 1972 | 24 |
| 49 | የመጀመሪያው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የተካሔደበት | 1976 | 20 |
| 50 | የኢ.ሠ.ፓ. ምሥረታና የ10ኛው የአብዮት በዓል የተከበረበት | 1977 | 19 |
| 51 | የግንቦት 8 መፈንቅለ መንግሥት | 1981 | 15 |
| 52 | ኢህአዴግ አዲስ አበባን የተቆጣጠረበት | 1983 | 13 |

## የ1996 ዓ.ም. የግብርና ናሙና ጥናት የተለያዩ የግብርና መረጃዎች መሰብሰቢያና መረጃ የተሞላባቸው ቅጾች ወደ ዋናው መ/ቤት መመለሻ ወቅት

| ተራ ቁጥር | የቅጽ ዓይነት | የሚጀምርበት | የሚጠናቀቅበት | መረጃ የተሞላባቸው ቅጾች ወደ ዋናው መ/ቤት መመለሻ ወቅት | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ግ.ና.ጥ 96/0 | ጳጉሜን 1/95 | ጳጉሜን 4/95 | መስከረም 20/96 | |
| 2 | ግ.ና.ጥ 96/1 | ጳጉሜን 4/95 | ጳጉሜን 4/95 | መስከረም 20/96 | |
| 3 | ግ.ና.ጥ 96/2 | መስከረም 20/95 | መስከረም 30/95 | ጥቅምት 5/96 | |
| 4 | ግ.ና.ጥ 96/2ሀ | መስከረም 2/96 | መስከረም 15/96 | መስከረም 20/96 | በወረዳ ደረጃ |
| 5 | ግ.ና.ጥ 96/3ሀ | መስረም 2/96 | መስከረም 15/96 | መስከረም 20/96 | ለ10 ቤተሰቦች የትንበያ ሰብሎችን የያዘ |
| 6 | ግ.ና.ጥ 96/3ሐ | መስከረም 2/96 | መስከረም 15/96 | መስከረም 20/96 | ለ10 ቤተሰቦች የትንበያ ሰብሎችን የያዘ |
| 7 | ግ.ና.ጥ 96/4 | መስከረም 2/96 | መስከረም 15/96 | መስከረም 20/96 | ለ10 ቤተሰቦች የትንበያ ሰብሎችን የያዘ |
| 8 | ግ.ና.ጥ 96/3ሀ-3መ | መስከረም 2/96 | ታህሳስ 20/96 | ታህሳስ 30/96 | የ15 ቤተሰቦችና የ10 ቤተሰቦች የተረፈውን |
| 9 | ግ.ና.ጥ 96/4 | መስከረም 2/96 | ታህሳስ 20/96 | ታህሳስ 30/96 | የ15 ቤተሰቦችና የ10 ቤተሰቦች የተረፈውን |
| 10 | ግ.ና.ጥ 96/5 | መስከረም 2/96 | የካቲት 10/96 | የካቲት 20/96 | |
| 11 | ግ.ና.ጥ 96/6 | መስረም 2/96 | የኮቲት 10/96 | የካቲት 20/96 | |
| 12 | ግ.ና.ጥ 96/7 | የካቲት 2/96 | የካቲት 8/96 | የካቲት 20/96 | |
| 13 | ግ.ና.ጥ 96/8ሀ-8ለ | መጋቢት 1/96 | ግንቦት 30/96 | ሰኔ 15/96 | የበልግ |
| 14 | ግ.ና.ጥ 1ሀ፤1ለ፤ 2ሀ፤2ለ፤ 3፤4 | ግንቦት 1/96 | ግንቦት 30/96 | ሰኔ 15/96 | የሰፋፊ እርሻዎች |